እፕድ

# አዲስ ዘመን

ሐሙስ

81ኛ ዓመት ቁጥር 230 ሚያዝያ 20 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ

# «የካቢኔ አባላት የሕዝብን ችግር ለመፍታት ወደ ክፍለ ከተማዎች ወርደው መሥራት አለባቸው»

\- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ



ፎቶ ፡- ፀሐይ ንጉሤ

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ካቢኔ አባላት የሕዝብን ችግር ለመፍታት ወደ ክፍለ ከተማዎች ወርደው መሥራት እንዳለባቸው የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ አሳሰቡ።

የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የ2014 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት አፈጻጸም ሪፖርት በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት አቅርቧል።

በወቅቱ ዶክተር ዐቢይ አሕመድ እንዳስታወቁት፤ በመሬት ጉዳይ፣ በአገልግሎት አሰጣጥ፤ በመኖሪያ ቤትና የደሃውን ኑሮ ለማቃለል በተለይም በምግብ እንዲሁም በአካባቢ ንጽህና በኩል ያሉትን ችግሮች ለመፍታት የአዲስ አበባ ካቢኔ አባላት ምድብ ተሰጥቷቸው ወደ ክፍለ ከተማዎች ወርደው መሥራት አለባቸው።

ከንቲባና ምክትል ከንቲባዎቹን ጨምሮ የአዲስ አበባ ሁሉም የካቢኔ አባላት ከሰኞ እስከ ሐሙስ ባሉት ቀናት በቢሯቸው ያለውን ሥራ መሥራት እንደሚችሉ የጠቆሙት ዶክተር ዐቢይ፤ ከዓርብ ጀምሮ ባሉት ቀናት ደግሞ በተመደቡበት ክፍለ ከተማዎች አንድ ቀን አንዱ ክፍለ ከተማ ጋር ሌላ ቀን ሌላው ጋር ወርደው ያለውን ችግር ሁሉ ማየትና ለማስተካከል መሥራት ይጠበቅባቸዋል ብለዋል።

«የካቢኔ አባላት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ ፡- ፀሐይ ንጉሤ

ረዳት ፕሮፌሰር ጌታ አስራደ

## በወልቃይት፣ ጠገዴና ጠለምት ሕዝብ ላይ የዘር ማጥፋት ወንጀል የፈጸሙ አካላት እንዲጠየቁ ዩኒቨርሲቲው አሳሰበ

ወርቁ ማሩ

ወልቃይት፡- በወልቃይት፣ ጠገዴና ጠለምት ሕዝብ ላይ የዘር ማጥፋት ወንጀል የፈፀሙ አካላትን በሕግ ተጠያቂ ማድረግና ለቀጣይም ትምህርት በሚሆን መልኩ ጉዳዩን የዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ እንዲያውቀው መሥራት እንደሚገባ የጎንደር ዩኒቨርስቲ አሳሰበ።

በወልቃይት፣ ጠገዴና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# «ኢትዮጵያ የተለያዩ እምነቶች ለዘመናት ተከባብረው የኖሩባት ናት»

\- አቶ ደመቀ መኮንን
ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የተለያዩ እምነቶች ለዘመናት ተከባብረው የኖሩባት ፤ በኢትዮጵያ የሃይማኖት መቻቻል ዘመናትን ያለፈ ታሪክ አለው ሲሉ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ተናገሩ።

አቶ ደመቀ ከኢድ እስከ ኢድ ወደ አገር ቤት ጉዞ የእንኳን ደህና መጣችሁ መርሐ ግብር በወዳጅነት አደባባይ ትናንት ሲካሄድ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ የተለያዩ እምነቶች ለዘመናት ተከባብረው የኖሩባት ናት ፤ በኢትዮጵያ የሃይማኖት መቻቻል ዘመናትን ያለፈ ታሪክ አለው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሃይማኖታዊ እሴትን የማይመጥኑ አስተሳሰቦች እየተስተዋሉ እንደሚገኙ አውስተው፤ በኢትዮጵያ የሃይማኖት መቻቻል ዘመናትን ያለፈ ታሪክ ያለው ቢሆንም ፤ ሰሞኑን በጎንደር የተከሰተው እኛን የማይገልጽ ነው ብለዋል።

እነዚህን ድርጊቶች ማረምና አብሮነትን ማጥበቅ አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመው፤ ከችግሩ ለመውጣትም ማስተዋል፣ አብሮነትን፣ መከባበርንና ሃይማኖታዊ

«ኢትዮጵያ የተለያዩ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ ፡- ገበበ ገብሬ






ዜና

# ተቋማቱ በትምህርት ዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮች በጥናት የተደገፈ መፍትሔ እንዲያገኙ እየሠሩ ነው

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በትምህርት ዘርፉ ያሉ ችግሮችን በመለየት በጥናት የተደገፉ መፍትሔ እንዲያገኙ እየሠሩ መሆኑን ቅድስተ ማርያም ዩኒቨርሲቲ አስታወቀ።ተቋማቱ በችግር የተተበተቡ በመሆኑም በሕዝቡ ላይ ለውጥ የሚያመጣ የምርምር ውጤት ማፍለቅ እንዳልቻሉም ተጠቁሟል።

የቅድስተ ማርያም ዩኒቨርሲቲ መሥራችና ፕሬዚዳንት ዶክተር ወንዶሰን ታምራት 20ኛው የአፍሪካ የግል ከፍተኛ ትምህርት ዓለም አቀፍ ጉባኤ ትናንት በአዲስ አበባ ሲካሄድ እንደገለጹት፤ የቅድስተ ማርያም ዩኒቨርሲቲ ላለፉት 20 ዓመታት በትምህርት ዘርፉ ውስጥ ያለውን ችግር በመለየት ወደፊት ኢትዮጵያ በለውጥ ጎዳና እንድትመራ ለማድረግ በጥናት የተደገፉ መፍትሔዎችን ፖሊሲ አውጭዎች እንደ ግብዓት እንዲጠቀሙባቸው እየሰጠ ይገኛል።

መንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ዘርፉን የድህነት ቅነሳና የኢኮኖሚ እድገት ቁልፍ መሣሪያ ነው ብሎ ለይቷል ያሉት ዶክተር ወንዶሰን፤ የግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በዘርፉ ያሉ ችግሮችን በመለየት ዘላቂ መፍትሔ እንዲያገኙ ሳይንሳዊ ጥናቶችን ለመንግሥት የማቅረብ ሥራ እንደሚሠሩና ከእነዚህ ተቋማት መካከልም አንዱ ቅድስተ ማርያም ዩኒቨርሲቲ መሆኑን ጠቅሰዋል።

እንደ ፕሬዚዳንቱ ገለጻ፤ የግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በሕግ ማዕቀፍ ውስጥ ያሉ ችግሮችን በአፈጻጸም የሚስተዋሉ እንከኖችንና የፖሊሲ የአፈጻጸም ክፍተቶችን በመለየት ለፖሊሲ አውጭዎች በጥናት አስደግፎ በማመልከት መሻሻሎች እንዲኖሩ ይሠራሉ። እንዲሁም እንደ ሃገር የሚታዩ ችግሮችን በመለየት ሃገርን ለማሳደግ የሚረዱ የጥናት ውጤቶችንም ያቀርባሉ።

20ኛው የአፍሪካ የግል ከፍተኛ ትምህርት ዓለም አቀፍ ጉባኤ የአፍሪካ ከፍተኛ ትምህርት ጥራትን ለማሻሻል በሚረዱ ጉዳዮች ላይ እንደሚያተኩር አመልክተው፤ በእነዚህ ዋና ዋናና ንዑስ ጭብጦች ላይ ተመሥርተው የሚቀርቡ ሳይንሳዊ የምርምር ወረቀቶችና የፓናል ውይይቶችም ለፖሊሲ አውጭዎች የሚያግዙ የመፍትሔ ሀሳቦችን እንደሚያመነጩ ገልጸዋል።

ቅድስተ ማርያም ዩኒቨርሲቲው አፍሪካውያን ተመራማሪዎችን በአንድ መድረክ በማገናኘት እርስ በርስ እንዲማማሩና የወደፊቷን አፍሪካ የተሻለች ለማድረግ እንዲቻል እየተደረገ ያለውን ሁለንተናዊ ጥረት ለማገዝ የመሪነቱን ሚና እየተጫወተ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ ሃገራችን በተለይ በትምህርት ዘርፍ እያደረገች ያለውን ከፍተኛ ሚና በማስተዋወቅ መልካም ገጽታዋ እንዲጐላ ትልቅ ድርሻ በማበርከት ላይ መሆኑን ጠቁመዋል።

የአፍሪካ ዩኒቨርሲቲዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር ሰኢድ በክሪ በበኩላቸው፤ በአፍሪካ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከፍተኛ ችግር አለባቸው። በተለያዩ የአፍሪካ ሃገራት የሚታዩ ግጭቶች፣ አለመረጋጋቶች፣ ድህነትና መሰል ችግሮች የሚበዙት ተቋማቱ ጠንካራ ባለመሆናቸው ነው ብለዋል።

ምርምር ለማድረግ የገንዘብ ዕጥረት የሚያጋጥማቸው መሆኑ፣ የመሠረተ ልማት አለመኖር፣ ዩኒቨርሲቲዎች ለመማር ማስተማር ምቹ አለመሆን የትምህርት ዘርፉ ችግር መሆኑን አንስተዋል። በነባር ችግሮች ላይ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ዘርፉን እንደ አዲስ የፈተነው ችግር መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ ፕሬዚዳንቱ ገለጻ፤ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በትምህርት ዘርፉ ላይ ያሳደረውን ተጽእኖ ለመቋቋም የተጀመረው የኦንላይን ትምህርት ተማሪዎች በኦንላይ ትምህርት ለመከታተል አስፈላጊ ቁሶች አለመኖርና የትምህርት ተቋማቱም ለዘመናዊ የመማር ማስተማር ሂደት ምቹ አለመሆን ውጤታማ መሆን እንዳልቻለ አንስተዋል።

በአፍሪካ የሚስተዋሉ ችሮችን ለመቅረፍ በተለይ ድህነት፣ ድርቅ፣ ግጭቶችን ለመቅረፍ ዩኒቨርሲቲዎች ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ እንደሚገባ አስገንዝበዋል። ጥናትና ምርምር በማድረግ ለሚስተዋሉ ችግሮች መፍትሔ እንዲያመጡ መንግሥት ለግል የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ድጋፍ ማድረግ እንዳለበት ጠቁመዋል።

ቅድስተ ማርያም ዩኒቨርሲቲ ጉባኤውን በየዓመቱ ሲያካሂድ የቆየ ሲሆን በዘንድሮው ዓመት ጉባኤው ከአፍሪካ ዩኒቨርስቲዎች ሕብረት፣ ከትምህርት ሚኒስቴር፣ ከአፍሪካ ከፍተኛ ትምህርት አለም አቀፍ ኔትወርክ፣ ከግል ከፍተኛ ትምህርት ምርምር ፕሮግራም እና በደቡብ አፍሪካ ከሚገኘው ከኩዋዙሉ ናታል ዩኒቨርሲቲ ጋር በጋራ በመሆን ማዘጋጀቱ ታውቋል።



# «ፊቼ ጫምባላላን ከመላው ኢትዮጵያውያን ጋር ለማክበር ተዘጋጅተናል»

*- የሀዋሳ ከተማ ነዋሪዎች*

**ዳግም ከበደ**

ሀዋሳ፡- የሲዳማ ብሔር የዘመን መለወጫ የሆነውን ፍቼ ጫምባላላ ከመላው ኢትዮጵያውያን ጋር በፍቅርና በሕብረት ለማክበር መዘጋጀታቸውን የሀዋሳ ከተማ ነዋሪዎች ገለፁ።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ትናንት በከተማዋ ተገኝቶ ያነጋገራቸው ነዋሪዎች እንደገለፁት፤ በዓሉ የመተሳሰብ የፍቅርና የይቅርታ መንፈስ ይዞ በድምቀት ለማክበር እየተጠባበቁት ነው።

አባቶች ለአገር ሰላም፣ ለፍቅር፣ ይቅርታና ለሰው ልጆች ሰላምና ደስታ እንዲሆን የሚፀልዩበት የዘመን መለወጫ ነው ያለችው የሀዋሳ ከተማ ነዋሪ እጅጋየሁ በለጠ፤ የሲዳማ ሕዝብና ሁሉም ኢትዮጵያዊ በጋራ ሆኖ እንዲያከብረው ዝግጅት አድርገናል። እንግዶችን በመልካም መስተንግዶ በመቀበልና በዋዜማው "የፊቼ" በዓል ላይ ሁሉም ቤቱ ያዘጋጀውን መሰናዶ ከወዳጅ ዘመዶቹ ጋር በመደሰት የሚያከብረው መሆኑን ገልፃለች።

እንደ እጅጋየሁ ገለፃ፤ በኮሮና ወረርሽኝ ምክንያት ከዚህ ቀደም ያለፈው የዘመን መለወጫ በዓል በድምቀት ሳይከበር ቀርቶ ነበር። ዘንድሮ ግን ሁሉም የሲዳማ ነዋሪና በክልሉ የሚገኙ መላው ኢትዮጵያውያን በጋራ ሆነው በመተሳሰብ የአባቶቹን ፀሎትና ምርቃት እየተከታተለ በደስታ ያሳልፈዋል።

ሌላኛው የከተማው ነዋሪና የአዋሳ ዩኒቨርስቲ የሰባቱም ካምፓሶች የተማሪዎች ሕብረት ፕሬዚዳንት የሆነው ዘለቀ ገመቹ በበኩሉ እንደተናገረው፤ ፊቼ ጫምባላላ አቃፊ በዓል ነው። በእለቱ የተጣላ የሚታረቅበት፣ የተቸገረውን በመተባበር የሚረዳበት ከመሆኑ ባለፈ ከሕፃን እስከ አዋቂ በጋራ ተደስቶ የሚያከብረው ነው። በዩኒቨርስቲውም ከሁሉም የአገሪቷ አካባቢዎች የመጡ ተማሪዎችም በጋራ ያለምንም ልዩነት በፍቅርና መተሳሰብ እንዲያከብሩት የከተማዋ ነዋሪዎች ዝግጅታቸውን አጠናቀዋል። ተማሪዎች የሲዳማን ማኅበረሰብ መገለጫዎች በመጠቀም በአልባሳቱ በመድመቅ እንዲሁም ከአባቶች ምርቃት በማግኘት ያለ ልዩነት በፍቅር አክብረውት ይውላሉ ብሏል።

ሌላው የአዋሳ ከተማ ነዋሪ ቲቶ ቱኑ እንደገለፀው፤ የፊቼ ጫምባላላ ከክልሉ አልፎ በአገር አቀፍና ዓለም አቀፍ እውቅና ያለው የሁሉም በዓል ነው። ይህን የዘመን መለወጫ ከመላው ኢትዮጵያውያን ጋር ለማክበር ተዘጋጅተዋል። ከሁሉም የኢትዮጵያ ክፍል የሚመጡትን እንግዶች ለመቀበል መሰናዷቸውን ጨርሰዋል።

"ወጣቶች ቀንና ሌሊት የከተማዋን ሰላም ነቅቶ ለመጠበቅ አስፈላጊውን ዝግጅት አድርገናል" ያለው የከተማዋ ነዋሪ ቲቶ ቱሉ፤ ፍቼ ጫምባላላ የፍቅር፣ የአንድነት በዓል ከመሆኑ አንፃር ሁሉም ስጋት ሳይገባው የሚደሰትበትና ዘመኑ የሰላም እንዲሆን ከአባቶች ጋር በጋራ የሚፀልይበት መሆኑን አንስቷል።

የክልሉ መንግሥት ከከተማዋ ነዋሪዎች ጋር በጋራ በመሆን በዓሉ በሰላምና በፍቅር ተከብሮ እንዲያልፍ ሙሉ ዝግጅት ማድረጉን በተደጋጋሚ ሲገልፅ ቆይቷል። ነዋሪዎቹም ይሄን በማረጋገጥ የፍቼ ጫምባላላ በዓል ድንበር የሌለው፣ በመላው ዓለም ማኅበረሰብ እንክብካቤ የሚደረግለት እንዲሁም በዩኒስኮ በማይዳሰስ ሰው ወካይ ቅርፅ ሆኖ የተመዘገበ ከመሆኑ አንፃር ለኢትዮጵያውያኖችም የእንኳን አደረሳችሁ መልክት አስተላልፈዋል።

# በኢትዮጵያ የብዝሀ ሕይወት ሀብቶች አስጊ ደረጃ ላይ ናቸው

**በዳግማዊት ግርማ**

አዳማ፡- ፈጣን የሕዝብ ቁጥር መጨመርና አብዛኛው ሕዝብ የገቢ ምንጩ የተፈጠረው የተፈጥሮ ሀብት ላይ የተመሠረተ መሆኑ የብዝሐ ሕይወትና የሥርዓተ ምህዳር ስጋት ውስጥ መውደቃቸውን የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት ገለጸ።

የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር መለሰ ማሪዮ ብሔራዊ የብዝሀ ሕይወት መድረክ ምሥረታና የብሔራዊ ስነ-ምህዳር ዳሰሳ ማጠቃለያ አውደ ጥናት በአዳማ ከተማ ከትናንት በስቲያ ሲካሄድ እንደገለፁት፤ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር መጨመር የብዝሀ ሕይወትና የሥርዓተ ምህዳርን ስጋት ውስጥ ከትቷል።

አብዛኛው የሕዝብ መተዳደሪያው ከተፈጥሮ ሃብት በሚመነጭ በመሆኑ የብዝሀ ሕይወት ሀብቶች አስጊ ደረጃ ላይ መሆናቸውን አመልክተው፤የመሬት መራቆት፣ የአፈር መሸርሸር፣ ግድቦች እና የውሀ ማጠራቀሚያዎች በደለል መሞላት፣ የአፈር ንጥረ ነገሮች በጎርፍ መሸርሸራቸውና ዝቅተኛ የመሬት ምርታማነት የኢትዮጵያን የብዝሀ ሕይወት እና ስርዓተ ምህዳርን አስጊ ደረጃ ላይ እንዲገኙ ማድረጋቸውን ዋና ዳይሬክተሩ አስታውቀዋል።

እንደ ዶክተር መለሰ ገለፃ፤ የሥርዓተ ምህዳር መመናመንና የብዝሀ ሕይወት ጥፋት ለመቀነስና ለመከላከል በአገር ደረጃ ሥራዎችን መሥራት ይገባል።

የቁርጠኝነት ክፍተትን መድፈን፣ ተገቢ የሆነ በጀትና መዋቅር ማደራጀት፣ የብዝሀ ሕይወት ጉዳዮችን በሁሉም ሴክተሮችና መንግሥታዊ ባልሆኑ መሥሪያ ቤቶች ማካተት፣ ልዩ የሆነ የብዝሀ ሕይወት ፈንድ ማቋቋም እንዲሁም የብዝሀ ሕይወትና የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት በቅንጅት እንዲሠሩ ማድረግ በዘርፉ ለሚታዩት ችግሮች መፍትሔ ሊሆኑ እንደሚችሉ ዳይሬክተሩ ጠቁመዋል።

የግብርና ሚኒስቴር ተወካይ አቶ ተፈራ ታደሰ በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ የብዝሀ ሕይወት ሀብቶች በተለያዩ ሰው ሠራሽ እና ተፈጥሯዊ በሆኑ ችግሮች ምክንያት የመመናመንና የመጥፋት የስጋት ደረጃዎች ውስጥ ይገኛሉ ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ አቶ ተፈራ ገለፃ፤ ብዝሀ ሕይወት ላይ የተጋረጡትን ችግሮች በመቅረፍ ያሉትን ሀብቶች ጠብቆ ማቆየት ያስፈልጋል።ከዚህ አኳያ የማኅበረሰብ እውቀቶች በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል።

በመድረኩ ከላይ የተጠቀሱትን ተግዳሮቶች ለመቅረፍ በአውሮፓውያኑ የጊዜ ቀመር መሰረት ከ2017 ጀምሮ በኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት አማካኝነት ብሔራዊ የሥርዓተ ምህዳር ዳሰሳ ፕሮጀክት እየተካሄደ መሆኑንም ታውቋል።

# «አብሮነታችን እኛን የሚያሻግረንና ለነገ የተሻልን የሚያደርገን ነው»

\- ኡስታዝ አቡበከር አህመድ

**ሙሳ ሙሐመድ**


ኡዝታዝ አቡበከር አህመድ


አምባሳደር ብርቱካን አያና

አዲስ አበባ፡- እኛ ኢትዮጵያውያን አብሮነታችን ሁልጊዜም ቢሆን እኛን የሚያሻግረንና እኛን ለነገ የተሻልን የሚያደርገን ነው ሲሉ ኡስታዝ አቡበከር አህመድ ገለጹ፡

ኡስታዝ አቡበከር ትናንት የኢድ ኤክስፖ በተከፈተበት ወቅት ባደረጉት ንግግር በኢትዮጵያውያን ላይ ባለፉት ዓመታቶች የደረሱብን ጉዳቶች የጋራ ጉዳቶቻችን ናቸው። ኢትዮጵያዊ አብሮነታችን ሁልጊዜም ቢሆን እኛን ወደፊት የሚያሻግሩንና ለነገ የተሻልን የሚያደርጉን ናቸው። በመሆኑም በውስጥና በውጭ ያለነው ሁላችንም አብሮነታችንን ልናጠናክር ይገባል ብለዋል።

ከጫፍ እስከ ጫፍ በኢትዮጵያ ላይ የደረሰው ፈተና የሁላችን ፈተና ነው። ያንን ፈተና ወደ ደስታ መቀየር፣ ወደ መልካም ነገር ማምጣት ደግሞ ኃላፊነቱም የዜጎች ነው። እነኝህን ማድረግ የምንችለው ደግሞ አብሮነታችን አጠናከረን በጋራ ስንቆም ነው። መንግሥት እንደ መንግሥት የራሱን ድርሻ ይወጣል፣ ማሕበረሰቡም የራሱን ድርሻ ሊወጣ ይገባል ብለዋል።

በውጭ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውንም የጀመሩትን ትንኮሳዎችን የመቀልበስ ሂደት ጅምር አጠናክረው ሊያስቀጥሉ እንደሚገባ ኡስታዝ አቡበከር ተናግረዋል።

አሁን የጋራ ሥራዎችን በመሥራት የተበላሹ ነገሮችን የማስተካከል ሥራ ከሁላችንም ይጠበቃል ያሉት ኡስታዝ አቡበከር፣ የጋራ ሥራዎቻችን በመሥራት የተጎዳውን ማከም፣ የተበላሸውን ቅርጽ ማስተካከልና የተሰበሩ ልቦችንና ያቀረቀሩ አንገቶችን ቀና የማድረግ የማኅበረሰብ ግዴታና ድርሻ ስላለብን የዲያስፖራዎች መምጣት የድርሻቸውን ለመወጣት ትልቅ ፋይዳ አለው ብለዋል።

ከኢድ እስከ ኢድ መርሐ-ግብርም ኢትዮጵያ በእስልምና ታሪክ ውስጥ ያላት ትልቅ ድርሻ ዛሬም ነገም መወጣት አለባቸው። ይህን ማድረግ ኃላፊነታችን እና ግዴታችን ትልቅ ነው። በጋራ በመሥራትና አብሮነታችንን በማጠናከር በጋራ ለዓለም ማሳየትና ማስገንዘብ ይገባል ብለዋል።

የኢድ ልዩ መገለጫው በደስታ የሚታለፍ በመሆኑ ነው ያሉት ኡስታዝ አቡበክር፣ ኢድ ኢድነቱ የሚታወቀው ሌሎችንም ወደ ደስታ በማስገባት ነውና የሌሎች ደስታም ለማምጣት በጋራ መሥራት ይገባናል ብለዋል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ እና የብሔራዊ ጣምራ ኮሚቴው ሰብሳቢ አምባሳደር ብርቱካን አያና በበኩላቸው ፣ ከኢድ እስከ ኢድ መርሐ-ግብር ኢትዮጵያ ያላትን ሃይማኖታዊ ታሪካዊና ማኅበራዊ ሀብቶች በሚገባ ለዓለም የምታስተዋውቅበት መልካም አጋጣሚ ነው ብለዋል።

ከኢድ እስከ ኢድ መርሐ ግብር "የታላቁ ጉዞ ወደ ሃገር ቤት" ቀጣይ ምዕራፍ መሆኑን ያስታወሱት አምባሳደር ብርቱካን፤ ዲያስፖራዎች ሃገራቸውን በብዙ መልኩ እንዲያግዙ ብሎም አብሮነታችን ለማጠናከር ዓላማ ያለው ሃገራዊ ጥሪ መሆኑን አንስተዋል።

# መከላከያ ሚኒስቴር ግዳጅ ፈፅመው ከውጭ ስተመለሱ ትግርኛ ተናጋሪ የሠራዊቱ አባላት ምስጋና አቀረበ

አዲስ አበባ፡- የመከላከያ ሚኒስቴር ሁሉንም ጫና ተቋቁመው አገርና ተቋማቸው የሰጣቸውን ግዳጅ ፈፅመው ለተመለሱ የትግርኛ ተናጋሪ የሠራዊቱ አባላት ምስጋና አቅርቧል።

ሚኒስቴሩ ትላንት በማኅበራዊ የትስስር ገጹ ባወጣው መግለጫ፤ ከዚህ ቀደምም በዳርፉር፣ ተልእኮ ላይ ተሠማርተው የነበሩት ወደ አገር ቤት እንዲመለሱ ሲደረግ በውዥንብር ጥቂት ወታደሮች መቅረታቸውን አስታውቋል። ሱዳን ከሚገኘው ሳምሪ ተቀላቅለው ሲዋጉ የሞቱም እንደነበሩ ጠቁሟል። ይሁን እንጂ ሁሉንም ጫና ተቋቁመው አገርና ተቋማቸው የሰጣቸውን ግዳጅ ፈፅመው ለተመለሱ የትግርኛ ተናጋሪ የሠራዊታችን አባላት ተቋማችን ከፍተኛ ምስጋና ያቀርብላቸዋል ሲል በመግለጫው ጠቅሷል።

አሸባሪው የሕወሓት ቡድን የአገር ሉዓላዊነት ምሽግ የሆነውን መከላከያ ሠራዊት በመምታት ለውጡን ቀልብሶ ወደ ስልጣን በመመለስ ኢትዮጵያን መግዛት፤ መግዛት ካልቻለ የራስን ዕድል በራስ መወሰን በሚል ክልሎችን በመገነጣጠል ኢትዮጵያን የማፍረስ ዓላማ ይዞ ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም በሰሜን ዕዝ ሠራዊት ላይ ጥቃት መክፈቱን ሚኒስቴሩ በመግለጫው አንስቷል።

አሸባሪው ቡድን በሠሜን ዕዝ ሠራዊታችን ላይ ጥቃት ከመፈፀሙ አስቀድሞ በመከላከያ ሠራዊት ውስጥ የሚገኙ ትግርኛ ተናጋሪዎችን "ኢንፍልትሬት" በማድረግ ለእኩይ ዓላማቸው በማዘጋጀት የሠሜን ዕዝ መከላከያ ሠራዊታችን ላይ ጥቃት በመክፈት ሠራዊታችንን ከውስጥና ከውጭ ማጥቃቱንም መግለጫው ጠቅሷል።

በዚህም የሕግ ማስከበርና የሕልውና ዘመቻው ሲጀመር ከመከላከያ ሠራዊታችን ጋር አብረው ሢሰሩ የነበሩ ከወታደር እስከ ከፍተኛ አመራር ያሉ ትግርኛ ተናጋሪዎች ለዘመቻው ስኬትና እርስ በእርስ እንዳንግማታ ሲባል ደመወዝና ቀለባቸው ሳይቋረጥ በቤታቸው እንዲቆዩ መደረጉ ተገልጿል።

በመግለጫው እንደተጠቀሰው፤ ከሰሜን ዕዝ ጥቃት በፊት ወደ ውጭ ሃገር ሰላም ለማስከበር የተላኩ ትግርኛ ተናጋሪዎች ግን በሠራዊታችንና በተልዕኮው ላይ ችግር አይፈጥሩም በሚል በሥራቸው እንዲቀጥሉ ተደርጓል። ሆኖም ግን ሕወሓት የትግርኛ ተናጋሪዎች ወደ ሃገራቸው እንዳይመለሱ በውጭ በሚገኙ የወያኔ ቅጥረኞች የሐሰት ፕሮፖጋንዳ በመነዛቱ በአባላቱ ላይ ውዥንብር ፈጥሯል።

ሃገር ቤት ከተመለሳችሁ ትታሰራላችሁ የሚል የማስፈራሪያ ውሸት በመንዛትና በዘረኝነት በመቀስቀስ ሃገራቸውንና ተቋማቸውን ሲያገለግሉ የነበሩ የትግራይ ተወላጅ የሠራዊት አባላትን የማስኮብለል ሥራ መሠራቱን፤ የሠራዊት አባላቱ ተቋማቸውንና ሃገራቸውን ጠልተው ሳይሆን ወያኔ በሠራው አፍራሽ ሥራ ስጋት ገብቷቸው የተወሰኑ ወታደሮች ሰላም ማስከበር በሄዱበት አገር መቅረታቸውንና ወያኔ ጥቂት አፍራሾችን በውስጣቸው በመፍጠር የእኩይ ዓላማው አስፈጻሚ አድርጓቸው እንደነበር በመግለጫው ተዳሷል።

"ከዚህ ቀደምም በዳርፉር፣ ተልእኮ ላይ ተሰማርተው የነበሩት ወደ አገር ቤት እንዲመለሱ ሲደረግ በተመሳሳይ ውዥንብር ጥቂት ወታደሮች ቀርተዋል። ሱዳን ከሚገኘው ሳምሪ ተቀላቅለው ሲዋጉ የሞቱም ነበሩ። ይሁን እንጂ ሁሉንም ጫና ተቋቁመው ሃገርና ተቋማቸው የሰጣቸውን ግዳጅ ፈፅመው ለተመለሱ የትግርኛ ተናጋሪ የሠራዊታችን አባላት ተቋማችን ከፍተኛ ምስጋና ያቀርብላቸዋል" ይላል መግለጫው።

ከዚህም ባሻገር፤ በሕግ ማስከበርና የህልውና ዘመቻው ወቅት በቤታቸው እንዲቆዩ የተደረጉ እና ከሠላም ማስከበር የተመለሡ በሺዎች የሚቆጠሩ የትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪ የሠራዊት አባላት እና ሲቪል ሠራተኞች ዛሬም የተቋሙ አባላት ስለሆኑ መብታቸውና ጥቅማጥቅማቸው እንደሚከበር ተጠቅሷል። አሁን ያለው ግጭት በማናቸውም አግባብ ከተፈታ ወደ ሥራቸው ተመልሰው ሃገራቸውን ያገለግላሉ በሚል አቋም እየተሰራ እንዳለም ተመላክቷል።

ሚኒስቴሩ በመግለጫው፤ "አሁንም በሰላም ማስከበር ተልዕኮ ላላችሁ፤ ከሠራዊት ጋር ግዳጅ እየተወጣችሁ ላላችሁና ለጊዜው ከሥራ ውጭ ሁናችሁ ነገር ግን ደመወዝና ጥቅማጥቅማችሁ ተጠብቆ ያላችሁ ወታደሮች በወያኔ አፍራሽ ፕሮፖጋንዳ ሳትንበረከኩ ሃገራችሁን እንድታገለግሉ፤ ቤተሰባችሁን እንዳትበትኑ፤ ጥቅማችሁ እንዳይቋረጥ፤ በክህደት ታሪክ እንዳትመዘገቡ እናሳስባለን" ሲል ገልጿል፡



# ሃገራዊ ችግሮች በምክክር እንዲፈቱ እንደሚሠራ መኢአድ ገለጸ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- በቀጣይ በሚካሄደው ሃገራዊ ምክክር ኢትዮጵያን ማዕከል ያደረገ ሀሳብ በማቅረብ ዘርፈ ብዙ የሆኑ ሃገራዊ ችግሮች በምክክር እንዲፈቱ እንደሚሠራ የመላው አንድነት ድርጅት/መኢአድ/ አስታወቀ።

መኢአድ ከ9ኛው የድርጅቱ ጉባኤ በኋላ በቀጣይ በሚያከናውናቸው የሥራ እንቅስቃሴዎች ላይ ትናንት የድርጅቱ ፕሬዚዳንት አቶ ማሙሸት አማረ በሰጡት መግለጫ፤ ኢትዮጵያ ከገባችበት ችግር ልትወጣ የምትችለው በአፈሙዝ ሳይሆን በውይይት መሆኑን ገልጸዋል።

መኢአድ ሃገራዊ የምክክር መድረክ እንዲፈጠርና ኢትዮጵያ ብሔራዊ መግባባት እንደሚያስፈልጋት በ30 ዓመት የትግል ጉዞው ሳያቋርጥ ሲሠራ ቆይቷል። እንደ ሃገር እየተከተልን ያለው የፌደራሊዝም ሥርዓት ኢትዮጵያን ሊያሻግር አይችልም። አንድ ሰው የጤና እክል ሲገጠመው ወደ ባህላዊ ወይም ዘመናዊ ሕክምና ሂዶ እንደሚታከም ሁሉ ሃገር ስትታመምና የፖለቲካ ችግር ሲገጥማት የሚያስፈልገው በውይይትና ምክክር መታከም ነው። ለዚህም ሃገራዊ ምክክሩ ከገባንበት አዙሪት ለመውጣት እንደሚያስችል የድርጅቱ እምነት መሆኑን ጠቅሰዋል።

በሃገራዊ ምክክሩ ሂደት ግልጽነት የጎደለው አካሄድ መታረም እንዳለበት የጠቆሙት አቶ ማሙሸት፤ በጠብመንጃ፣ በማፈናቀል፣ በማሰር፣ ሃገርና ሕዝብን መታደግ ስለማይቻል ግልጽ የሆነ ሃገራዊ ምክክር እንዲካሄድ መኢአድ አስፈላጊውን መስዋዕትነት ይከፍላል ብለዋል።

ፓርቲው ለምክክሩ ስኬት ግፊት የሚያደርግና ለውይይቱ የሚሆኑ ግብዓቶችን እንደሚያበረክትም ጠቁመዋል።

እንደ ፕሬዚዳንቱ ገለጻ፤ ፓርቲያችን ሳይሆን ኢትዮጵያን ማዕከል በማድረግ «ሀሳብ የምናቀርብበት፣ ለኢትዮጵያ የሚጠቅምና ለመጪው ትውልድ መደላድል ፈጥረን የምናልፍበት፣ ሥርዓት የምናመቻችበት አሁን ያለው ችግር፣ በፊትም አሉ የሚባሉ ትርክቶች የሚታረሙበት» ምክክር እንዲካሄድ መኢአድ ጽኑ ፍላጎት አለው።

የፓርቲው ተቀዳሚ ምክትል ሊቀመንበር አቶ አብራሃም ጌጡ በበኩላቸው፤ ሃገራዊ ምክክሩ ወሳኝ የሆነ አጀንዳና በታሪክ አጋጣሚ ኢትዮጵያውያን ችግራችን የምንፈታበት ነው። ሃገራችን የገጠማት ፈርጀ ብዙ የሆኑ የፖለቲካ ችግሮች ሊፈቱ የሚችሉት በምክክርና በውይይት እንደሆነ የመኢአድ ቁልፍ አቋም ነው ብለዋል።

በሕግ የበላይነት ዙሪያ፣ በሰንደቅ ዓላማ፣ በብሔራዊ ጀግኖቻችን እና መሰል ጉዳዮች ላይ ስምምነት የሌለው ፖለቲካ ፓርቲ ያለ በመሆኑ ችግራችን ለመፍታት የተደራጀውም፣ ያልተደራጀም፣ ፖለቲከኛው፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ወጣቱ፣ ምሑሩ መላ ኢትዮጵያውያን መወያየት ይገባል ብሎ መኢአድ እንደሚያምን ገልጸዋል።

መኢአድ በመግለጫው፤ ወጣቶች ኢትዮጵያ የምትገኝበትን ሁኔታ በመገንዘብ ጊዜ ወለድ የሆነውን ጽንፈኛ አስተሳሰብ በመጸየፍ ለመጭው ትውልድ የምትሆን ሃገር ለመገንባት በሚደረገው ጥረት የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ጥሪ አቅርቧል።

በኢትዮጵያ ያለውን ሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ ችግር ለመቅረፍ ለወጣቶች፣ ለሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች፣ ለፍትሕ አካላት፣ ለጸጥታ አካላት፣ ለሃይማኖት አባቶች፣ ለአገር ሽማግሌዎች፣ በንግድ ሥራ ለተሠማሩ ዜጎች አብረን እንሥራ ሲልም ጠይቋል።

መኢአድ ባለፈው ሳምንት ባካሄደው 9ኛ ጉባኤው 21 የሥራ አስፈጻሚ አባላት የመረጠ ሲሆን 12 የሚሆኑት አዲስ የሥራ አስፈጻሚ አባላት ሲሆኑ አምስቱ ደግሞ ሴቶች ናቸው።

# «የካቢኔ አባላት...

ከገፅ 1 የዞረ

ለዚህም መስተዳደሩ በቀጣይ እያንዳንዱን ካቢኔ የተወሰኑ ክፍለ ከተማዎችን በኃላፊነት እንዲይዝ በማድረግ በተሰጣቸው ክፍለ ከተማ ላይ ውጤት እንዲያመጡ የሚያደርግ አሠራር መዘርጋት እንዳለበት ጠቁመዋል።

በተለይ በዳቦ ምርት ላይ እያንዳንዱ ካቢኔ በክፍለ ከተሞች ውጤት ማምጣት አለበት ያሉት ዶክተር ዐቢይ፤ ካቢኔዎች 50ና 60 ሺህ ሰዎችን በቀን መመገብ የሚችሉ ፋብሪካዎችን እንዲገነቡ ባለሃብቶችን ማስተባበር አለባቸው። ከዚህ ባለፈ በጓሮ አትክልት በአነስተኛ ስፍራ ላይ እንዴት ማምረት ይቻላል የሚለውን የባህል አብዮት ማምጣት ይጠበቅባችኋል ብለዋል።

ከንቲባዋን ጨምሮ የከተማ አመራሮች በሚመደቡባቸው ክፍለ ከተሞች ላይ ወርደው በሚሠሩበት ወቅት በክፍለ ከተሞቹ ምንድነው መፈታት ያለበት? የትኛው ሌባ ነው? የትኛው በቀናነት ይሠራል? የሚለውን መለየትና ማስተካከል እንደሚጠበቅባቸው ገልጸዋል።

እኔ ቦሌና የተለያዩ አካባቢዎች ላይ ሳይጠናቀቁ የቀሩ ህንጻዎችን ሳይ እያንዳንዱ ባለሃብት ጋር እየደወልኩ ምንድነው ችግራችሁ እያልኩ ነው በፍጥነት እንዲያጠናቅቁ አደርጋለሁ፤ እናንተም በየክፍለ ከተማው ያለሥራ ታጥሮ የተቀመጠው መሬት የቱ ነው? ሳይጠናቀቅ የቀረው ሕንፃስ የቱ ነው? እያላችሁ በመከታተል ውጤታማ ሥራ ማከናወን ይኖርባቸዋል ሲሉ አቅጣጫ አስቀምጠዋል።

በሌላ በኩል የደሃውን ኑሮ ለማቃለል የሚደረጉ ጥረቶች ያስፈልጋሉ፤ ለአብነት በቤት አቅርቦት ረገድ ሁሉም ሰው ቤት ይኑረው የሚል አሠራር ባይኖርም፤ ከአልሚዎች ጋር በሚደረግ ውል ቤት ለመገንቢያ የሚሆን መሬት ሲቀርብላቸው በምላሹ ከተገነቡት ቤቶች 30 በመቶ ለከተማ አስተዳደሩ የሚሰጡ መሆን አለባቸው ብለዋል።

በተጨማሪ በየሕንጻዎች ላይ ለተቸገሩ የሚውል ቤቶችን ማከራየት የሚቻልበትን መንገድ መፈለግ እንደሚገባና አሠራሩ ዜጎች በተመጣጣኝ ዋጋ የቤት ኪራይ እንዲያገኙ በማድረግ የኪራይ ዋጋን እንደሚያረጋጋ ጠቁመው፤ ይህ አይነቱ አካሄድ የማኅበራዊ ኃላፊነትን መወጣት መሆኑንም ገልጸዋል።

ከዚህ ባለፈ ግን እንደፈለጉ የኪራይ ዋጋ መጨመር እንዳይቻል የሚያዝ ሕግ አውጥቶ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቃል ሲሉ ተናግረዋል።

ከእነዚህ ሁሉ ሥራዎች ባለፈ ደግሞ ሁሉም የከተማዋ አመራሮች የየእራሳቸው አሻራ ያረፈበት ትልቅ ፕሮጀክቶችን መሥራት ይጠበቅባቸዋል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በተጨማሪ በከተማዋ የሚሠሩ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ለአብነት አድዋ ዜሮ ኪሎ ሜትር ፕሮጀክቶችና የሆስፒታሎች ግንባታ እንዲሁም ሌሎች ለሕዝብ የሚጠቅሙ ሰፋፊ ልማቶችን በየጊዜው መከታተል እንደሚያስፈልግ አሳስበዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በበኩላቸው፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሰጡት አቅጣጫ መሠረት ካቢኔውን በቡድን በመክፈል ክፍለከተሞችን በኃላፊነት እንዲከታተሉ ይደረጋል ብለዋል።

ወደ የክፍለ ከተሞቹ በሚያስፈልጉ ቀናት በመሄድ አገልግሎቱን ማሻሻል ፤ የሕዝብ ጥያቄዎችን በምንችለው መጠን መመለስና ፤ የመሬት ፣ የልማትና የምግብ እንዲሁም የቤት ችግሮችን ለመፍታት የሚደረገው ሥራ በይበልጥ ማሳደግ ይጠበቅብናል ሲሉ ተናግረዋል።

ለሕዝባችን ለውጥ ማምጣት ካለብን ከእራሳችን ከአመራሩ ነው መጀመር ያለብን ያሉት ከንቲባዋ፤ በዚህ አግባብ ሞዴል የሚሆኑ ክፍለ ከተሞችን ለማውጣት ጠንክረን መሥራትና የኅብረተሰቡን ጥያቄ መመለስ እንዳለብን አቅጣጫ ወስደናል ብለዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የ2014 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት አፈጻጸም ሪፖርት ቀርቦ ውይይት ከተደረገበት በኋላ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ግቢ በአነስተኛ ቦታዎች የተሰሩ የጓሮ አትክልት ልማቶች ተጎብኝተዋል። በተለይም በተንጠልጣይ የፕላስቲክ ዕቃዎች፤ በግድግዳዎች እንዲሁም በአነስተኛ መሬት ላይ ማዘጋጀት የአትክልት ማልማት የሚቻልባቸው ዘዴዎች በተመለከተ ጉብኝት ተደርጓል።

በቀረበው የ9 ወራት ሪፖርት ላይ በከተማዋ 40 የመጠጥ ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮዎች መከናወናቸው ተገልጿል።

በተጨማሪ በመንገድ ግንባታና ፣ በጤናና ሌሎች ፕሮጀክቶች ግንባታ ሰፊ ሥራ መከናወኑ ተናግረው በቀጣይ ወራትም ግንባታዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ ከንቲባዋ አረጋግጠዋል።በተለያዩ ጊዜያት ሲጓተቱ የነበሩ 336 ፕሮጀክቶችን ግንባታ መከናወኑን ከንቲባዋ ጠቁመው፤ ከዚህ ውስጥ 145ቱ ፕሮጀክቶች ተጠናቀው ለአገልግሎት መብቃታቸውን አስታውቀዋል።

# በጦርነቱ ለተፈናቀሉ ወገኖች ድጋፍ በማበርከት ላይ የሚገኙ አካላት በሰላም ግንባታ ላይም እንዲያተኩሩ ተጠየቀ

አዲስ አበባ፡- በጦርነቱ ለተፈናቀሉ ወገኖች ድጋፍ በማበርከት ላይ የሚገኙ አካላት በሰላም ግንባታ ላይም እንዲያተኩሩ የአማራ ክልል ርዕሰ መሥተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ ጠይቀዋል።



ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ የዓለም የምግብ ፕሮግራም ልዑካንን ትናንት በጽሕፈት ቤታቸው ተቀብለው አነጋግረዋል። በዓለም የምግብ ፕሮግራም የኢትዮጵያ ዳይሬክተር ክላውድ ጂቢዳር የተመራው የልዑካን ቡድን እስካሁን በክልሉ እያከናወናቸው ባሉና በቀጣይ የክልሉን መንግሥት የትኩረት አቅጣጫ አውቆ ለመደገፍ በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ ገለጻ አድርጓል።

ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ እንደገለጹት የዓለም የምግብ ፕሮግራም በክልሉ እስካሁን ላበረከተውና እያበረከተ ላለውም አስተዋጽኦ ምሥጋና አቅርበዋል።

በክልሉ ከቀን ቀን የሚስተዋለው ድጋፍ የሚሹ ወገኖች ቁጥር እያሻቀበ ከመሄዱ አኳያ ፕሮግራሙ መልካም ተግባራቶቹን አስፍቶ እንዲቀጥል ጠይቀዋል።

ለችግር የተጋለጡ ወገኖች በዘላቂነት ኑሯቸውን መምራት እንዲችሉ ለጋሽ አካላት በስብዕና እና ሰላም ግንባታ ላይ አተኩረው እንዲሠሩ ዶክተር ይልቃል ጠይቀዋል።

በፕሮግራሙ አማካኝነት በጦርነቱና በከፊል የተፈጥሮ አደጋ ለተፈናቀሉ ከአንድ ሚሊዮን 872 ሺህ በላይ ወገኖች ካለፈው መስከረም ወር ጀምሮ በልዩ ልዩ ስልቶች የዕለት ደራሽ የምግብ እህል እየደገፈ እንደሚገኝ ነው የተነገረው።

ዳይሬክተሩ በክልሉ ከ11 ነጥብ 6 ሚሊዮን በላይ ወገኖች ድጋፍ የሚሹ መኾናቸውን ስለተገነዘብን የክልሉን መንግሥት ፍላጎት ባገናዘበ ሁኔታ የድርሻችንን ከመወጣት ባሻገር የችግሩን ስፋት ለሌሎች ለጋሾችም ለማሳወቅ የሚያስችል መረጃ ለማግኘት ውይይት አካሂደናል" ብለዋል።

የዓለም የምግብ ፕሮግራም በክልሉ በ23 ወረዳዎች ድጋፍ ከሚሰጣቸው ወገኖች መካከል በ129 ትምህርት ቤቶች የምግብ አገልግሎት የሚሰጣቸው 45 ሺህ ተማሪዎች ይገኙበታል።

በ221 ሚሊዮን ብር ለ200 ሺህ አርሶ አደሮች የምርጥ ዘር አቅርቦት እና ለእርባታ የሚኾኑ የቤት እንስሳትን በማቅረብ የሚደገፉ እንዳሉም ተጠቅሷል።

ለ85 ሺህ 600 ነፍሰ ጡርና አጥቢ እናቶች እንዲሁም ከአምስት ዓመት በታች ዕድሜ ላላቸው ሕጻናት የአልሚ ምግብ ድጋፍ እየቀረበ መኾኑም ታውቋል።

ከርዕሰ መስተዳድር ጽሕፈት ቤት የተገኘ መረጃ እንደሚያመላክተው የዓለም ምግብ ፕሮግራም የሚሰጠው አገልግሎት የተሳለጠ እንዲኾንና ቅንጅታዊ አሠራሩንም ለማጠናከር ከአምስት ወር በፊት ጀምሮ ክልላዊ የማስተባበሪያ ቢሮ በባሕርዳር ከተማ እንደከፈተም አሚኮ ዘግቧል።

# በወልቃይት፣ ጠገዴና...

ከገፅ 1 የዞረ

በጎንደር ዩኒቨርስቲ የወልቃይት፣ ጠገዴና ጠለምት ሕዝብ ላይ የተካሄደውን ጅምላ ጭፍጨፋዎችና የዘር ማጥፋት ወንጀሎች አስመልክቶ ጥናት ያደረገው የጎንደር ዩኒቨርስቲ የጥናት ቡድን መሪ ረዳት ፕሮፌሰር ጌታ አስራደ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ሕወሓት አካባቢውን መቆጣጠር ከጀመረበት ከ1972 ዓ.ም ጀምሮ በአካባቢው ማኅበረሰብ ላይ ከፍተኛ ኢ-ሰብዓዊና ስነልቦናዊ ግፎች ተፈጽመዋል።

ረዳት ፕሮፌሰሩ እንደገለፁት፤ ሕወሓት በአካባቢው ማኅበረሰብ ላይ በፈፀመው ግፍ የተነሳ ከእያንዳንዱ ቤተሰብ 26 ነጥብ 5 ከመቶ ለስደት ተዳርጓል፤ 19ነጥብ5 ከመቶ ታፍኖ የት እንደገባ አይታወቅም፣ እንዲሁም 29 ከመቶ ለሞት ተዳርጓል።

ሕወሓት በ1972 ዓ.ም ነሐሴ መጨረሻ አካባቢ ተከዜን ተሻግሮ የጎንደር ክፍለሃገር አካል የሆነውን ወልቃይትን መውረር ጀመረ ያሉት ረዳት ፕሮፌሰር ጌታ፤ ከዚያ አድማሱን እያሰፋ የደርግ መንግሥት በተለያዩ ውስጣዊና ውጫዊ ችግሮች ምክንያት አጣብቂኝ ውስጥ በነበረበት ወቅት በሰሜን በኩል ያለውን ወልቃይትን፣ ጠገዴን እና ጠለምትን ወደ መውረር መሄዱን ጠቅሰዋል።

በዚህ ምክንያት የወልቃይት፣ጠገዴና ጠለምት አማራዎች ወረራ ሲካሄደባቸውና ደም አፋሳሽ ድርጊት ሲፈጸምባቸው ከፋኝ የሚል የትጥቅ ትግል እስከማደራጀት የሄዱበት ሁኔታ እንደነበር ረዳት ፕሮፌሰር ጌታ ጠቁመው፤ በዚህም ከሕወሓት ጋር ለአስርተ ዓመታት ተፋልመዋል ብለዋል።

በኛ ጥናት ያረጋገጥነው ወረራው የቅኝ ግዛት ወረራ ነው የሚመስለው የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰር ጌታ፤ ቅኝ ግዛት ሲመጣ በጉልበት ተጭኖ ሃብትና ንብረትን ሊዘርፍ፣ ሊያሳድድና ሊገድልም ጭምር ነው የሚመጣው፤ ሕወሓትም ይህን ነው የፈጸመው ብለዋል።

የወልቃይት፣ ጠገዴና ጠለምት ሕዝብ ማንነቴ ይመለስልኝ፣ በጉልበት ያለማንነቴ ወደትግራይ ተካልያለሁ በማለት ጉዳዩን የማንነት አስመላሽ ኮሚቴ በማቋቋም ሕጋዊ በሆነ መንገድ እስከ ፌዴሬሽን ምክር ቤት ድረስ አድርሶት ላለፉት ስምንት ዓመታት አካባቢ የተጀመረው የማንነት አስመላሽ ኮሚቴ ጉዳይ እስካሁን እልባት አለማግኘቱንም ረዳት ፕሮፌሰር ጌታ ጠቁመዋል።

ረዳት ፕሮፌሰር ጌታ በጥናታቸውም በወልቃይት፣ ጠገዴና ጠለምት ሕዝብ ላይ የታሪክ፣ የባህልና የቋንቋ ለውጥ መኖሩን አረጋግጠናል ብለዋል።

ታሪክ አዋቂ የሆኑና ማኅበረሰቡን ያነቃሉ፤ መንግሥትን ይሞግታሉ፤ የሚባሉ ሰዎች ልቅም ተደርገው በጭለማና በብርሃንም ጭምር ታፍነው ተወስደው ከፊሎቹ ተገድለዋል፤ ከፊሎቹ ደግሞ የት እንደገቡ አይታወቅም ሲሉም ጠቁመዋል።

እስካሁን ባለው ሂደት ማይካድራን ጨምሮ በገሃነም አካባቢ በርካታ ሰዎች የተፈጁበት 12 የጅምላ ጭፍጨፋ ቀጠናዎች መገኘታቸውንና ሌሎች 12 የሚሆኑ ተጠርጣሪ ቦታዎችም እንዳሉ ረዳት ፕሮፌሰሩ ጠቁመዋል።

ረዳት ፕሮፌሰሩ እንደገለፁት፤ በግድያው ወቅት ብዙ አይነት ስልት ነበር የሚከተሉት። አንዳንዴ አደባባይ ላይ ረሽነው አስከሬንን አደባባይ ላይ ያሰጡ ነበር። ገበያ ላይ ጥለው እንዳይለቀስ ያደርጉም ነበር። ይህ የሰዎችን ስነልቦና ለመጉዳት ነው። ሌላው ደግሞ ገድሎ ገደል ውስጥ መክተትም ሌላው ስልታቸው ነበር። ይህ ሕዝቡን ለማሸማቀቅና ስነልቦናውን ለመስለብ ነው።

ሕወሓት በዚህ አካባቢ በዚህ ልክ የሞት ቀጠና እንዲሆን ካደረገባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ከመልክዓ ምድር አንጻር ቁልፍ ቦታ በመሆኑ ነው የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰር ጌታ፤ አካባቢው ሰሊጥ፣ማሽላ፣ ጥጥ፣ የሚመረትበት፣ የቀንድ ከብት በብዛት የሚረባበት ወደሱዳንና ኤርትራም ጭምር ኮሪደር የሚሆን በመሆኑ ከዚህ ለመጠቀም ነው ብለዋል።

በዚህም መሠረት የሕወሓት ካድሬዎች በጣም ሰፋፊ የእርሻ መሬቶችን በዚያ አካባቢ ይዘዋል። ተወላጁ መሬቱን ተነጥቆ አካባቢው የሕወሓት ካድሬዎች ንብረት እንዲሆን ተደርጓል። በዚህም ለረጅም ጊዜ ሰሊጥ፣ ማሽላና ጥጥ ሲያመርቱበት እንደነበር አይተናል ብለዋል።

ይህ ስልታዊ፣ የተደራጀ፣ መንግሥት መር የሆነ በማንነት ላይ በማኒፌስቶ የተደገፈ፣ ወንጀል ነው የተፈፀመው ያሉት ረዳት ፕሮፌሰር ጌታ፤ ይህን ወንጀል መንግሥትም ሆነ ሌላው አካል በአደባባይ አውጥቶ ወንጀሉን የሠራውን አካል መጠየቅ፣ ወደፊት ደግሞ ትምህርት እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል።

# «ኢትዮጵያ የተለያዩ...

ከገፅ 1 የዞረ

እሴቶችን ማስታወስ ያስፈልጋል ነው ያሉት።

በጎንደር ከተማ የተፈጠረው ክስተት አሳዛኝ፣ ሃይማኖቶቹንም ሆነ ታሪካችንን የሚመጥን አይደለም ያሉት አቶ ደመቀ፤ከችግሩ ለመውጣት ማስተዋልና መከባበር ያስፈልጋል፤ በመከባበርና በማስተዋል መጓዝ እንደሚገባም ገልጸዋል። ጉዳት ለደረሰባቸውና ለተጎጂ ቤተሰቦች መጽናናትን ተመኝተዋል።

የጉዞ ጥሪው የኢትዮጵያን ገፅታ ለመገንባትና ቱሪዝሙን ለማነቃቃት ሚናው የጎላና ለዲፕሎማሲ ሥራው አቅም የሚፈጥር መሆኑን ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ተቀዳሚ ሙፍቲ ሐጅ ዑመር እድሪስ፤ በአንዳንድ ቦታ ችግር እየተፈጠረ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ በጎንደር የተፈጠረው የሰሞኑ ድርጊትም ሊወገዝ እንደሚገባ ተናግረዋል።

"ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች የምናውቀው መተባበርና መከባበር ነው፣ የሚያምርብን በሃዘና በደስታ ስንተባበር ነው፣ ወደሚያምርብን መመለስ አለብን" ያሉት ተቀዳሚ ሙፍቲ ሐጅ ዑመር፤ በአገር ጉዳይ ላይ እየተመካከሩ መሥራት እንደሚገባና የመመካከርና የመተባበር ትርፉ ሰላምን ማረጋገጥ መሆኑን ገልጸዋል።

ዲያስፖራዎች ስለሰላም፣ ስለአንድነትና ስለእድገት መስበክ አለባቸው። ልማትን ማፋጠን ይኖርባቸዋል። ሕዝብ ከድህነት እንዲወጣ በሚደረገው ርብርብ ድርሻቸውን እንዲወጡም አደራ ብለዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በበኩላቸው፣ "ዲያስፖራው በአሁኑ ሰዓት የጠላትን አንገት የሚያስደፋ ወዳጅን ደግሞ የሚያኮራ ተግባር እየፈጸማችሁ ትገኛላችሁ" ብለዋል።

መርሐ ግብሩ ዲያስፖራው እያከናወነ ያለው ወገንን ያኮራ ተግባር አጠናክሮ ለማስቀጠል ድርሻ እንደሚኖረው ተናግረዋል።

በመርሃ ግብሩ ላይ የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ጥሪን ተቀብለው ወደ አገራቸው የገቡ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን፣ የመንግሥት ኃላፊዎችና የእምነቱ ተከታዮች ታድመዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## መጽሐፍትን ለአብርሆት!

በአዲስ አበባ ከተማ አራት ኪሎ አካባቢ ተገንብቶ ወደ ሥራ ለገባው አብርሆት ቤተመጻሕፍት ሕዝቡ ፣ ተቋማትና ሌሎችም መጻሕፍት እንዲለገሱ በመንግሥት በኩል የቀረበውን ጥሪ ተከትሎ መጽሐፍት ልገሳው ተጀምሯል። አንጋፋው የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም በቀደምት የድርጅቱ አንጋፋ ደራሲያንና ጋዜጠኞች ስም ከየሠራተኞቹና ዓላማውን ከሚደግፉ ወገኖች ያሰባሰባቸውን ከአምስት ሺ በላይ መጽሐፍትን ከትናንት በስቲያ ለቤተመጽሐፍቱ አስረክቧል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እነዚህን መጽሐፍት ያሰባሰበው ‹‹አምስት ሺ መጽሐፍት በአምስት ቀናት›› የሚል መርሐ ግብር አካሂዶ ነው፤ በእዚህም ከዕቅዱ በላይ ከአምስት ሺ የሚበልጡ መጽሐፍትን ማሰባሰብ በመቻሉም በእጅጉ የተሳካ ተግባር ማከናወን ችሏል።

በቀጣይም አንደ ሃገር አንድ ሚሊዮን መጽሐፍት ለማሰባሰብ የተያዘውን ዕቅድ ለማሳካትም ሰፋፊ ሥራዎችን እንደሚሠራ አስታውቋል።“በዕድሜ ልክ” በሚል መሪ ቃል ሁለተኛውን ዙር መጻሕፍት የማሰባሰብ ዘመቻ ጀምሯል፤ ይህም ዘመቻ የድርጅቱን 81ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ ለአንድ ዓመት 100 ምርጥ መጽሐፍት፤ ለ81 ዓመታት ስምንት ሺህ 100 ምርጥ መጽሐፍትን የማሰባሰብ ዓላማ ያለው ነው። ይህንንም በተሳካ ሁኔታ እንደሚያጠናቅቅ ተገልጿል።

መጽሐፍቱን የተረከቡት የመንግሥት ኃላፊዎችም ተቋሙ መጽሐፍቱን በማሰባሰብ በኩል አርአያነት ያለው ተግባር ማከናወኑን ጠቅሰው አድናቆት ችረውታል። ሌሎች ተቋማትና ዜጎችም በአጠቃላይ ለእዚህ የዕውቀት ማዕከል ለሆነ ቤተመጽሐፍት መጽሐፍትን እንዲለግሱም ጥሪ ቀርቧል።

በመንግስት በኩል በሃገር አቀፍ ደረጃ በአንድ ወር ውስጥ አንድ ሚሊዮን መጽሐፍትን ለማሰባሰብ እቅድ ተይዟል። ይህም የቤተ መጽሐፍቱን አቅም በማሳደግ ረገድ ትልቅ ሚና እንደሚኖረው ታምኖበታል። ይህን አርአያነት ያለው በሚል የተገለጸን መጽሐፍትን የማሰባሰብ ተግባር ሌሎች ተቋማትና ዜጎች ሁሉ ተከትለው እንደ ሃገር የተያዘው ዕቅድ እንዲሳካ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

አንድ ተቋም በአምስት ቀናት ከአምስት ሺ በላይ መጽሐፍትን ማሰባሰብ ከቻለ የበርካታ ተቋማት ባለቤት የሆነችው ሃገራችንም በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ መጽሐፍትን ማሰባሰብ እንደምትችል ጥርጥር የለውም። ተቋማት መጽሐፍቱን በማሰባሰብ በእዚህ ታላቅ የሃገር ተቋም የተሰነቀው ራዕይ እንዲሳካ የበኩላቸውን አሻራ ማኖር ይጠበቅባቸዋል።

አብርሆት ቤተመጽሐፍት እጅግ ግዙፍ ቤተመጽሐፍት ነው። እጅግ ግዙፍ የሚያሰኙትን በርካታ መረጃዎችም አሉት። በድንቁርና ምክንያት በሃገራችን ላይ ሲደርስ የኖረው ችግር ሊፈታ የሚችለው በእውቀት ነው፤ እውቀትን ለመጨበጥ ደግሞ በተለይ ልጆች የሃገርን፣ የነጻነትን፣ የታሪክን ምንነት ወደ ብልጽግና የመጓዝ ጠቀሜታንና ፍሬን እንዲገነዘቡ ማድረግ ይገባል። የዚያ መሠረቱ ዕውቀት መሆኑና ይህን እውቀት ለመገብየት ደግሞ እንደ አብርሆት ቤተመጽሐፍት ያሉ ቤተመጽሐፍት በእጅጉ እንደሚያስፈልጉ ታምኖበታል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በቤተመጻሕፍቱ ምረቃ ወቅት፤ አብርሆት ብዙ የተቆለፉብንን ታሪኮች፣ የሀብት መፍጠሪያ እና የሰላም መንገዶች የሚከፈቱበት ቁልፍ ነው ብለዋል። ኢትዮጵያን እንዲመጥን ተደርጎ የተገነባም ብለውታል። ይህ ሁሉ የቤተመጽሐፍቱን እጅግ ታላቅ መሆን በሚገባ ያመለክታል።

የራሳቸው ፊደል ካላቸው 18 ሃገሮች አንዷ በሆነችው ኢትዮጵያ መገንባቱም በራሱ የቤተመጽሐፍቱን ታላቅነት ያስገነዝባል። በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ግዙፍ የሕዝብ ቤተመጽሐፍት፣ በአፍሪካም ካሉት ግዙፍ አስር ቤተመጻሐፍቶች አንዱ መሆኑም የቤተመጽሐፍቱን ታላቅነት አስረግጠው ይመሰክራሉ።

በ19 ሺ ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የተገነባው ይህ ቤተ መጽሐፍት በአንድ ጊዜ ከ2 ሺህ በላይ ተጠቃሚዎችን ማስተናገድ ይችላል፤ በውስጡ ከማንበቢያ ስፍራ በተጨማሪ 8 የመጽሐፍ መሸጫ መደብሮች፣ የስብሰባ አዳራሽ፣ ካፍቴሪያ፣ የሕፃናት የማንበቢያ ክፍሎች፣ በቡድን ውይይት ማድረግ የሚያስችሉ ክፍሎችም ተዘጋጅተውለታል። በአራት ወለሎቹ አንድ ነጥብ 4 ሚሊዮን መጽሐፍትን መያዝ የሚችል አንድ ነጥብ አምስት ኪ.ሜ የሚረዝም መደርደሪያ። በአንድ ጊዜ 115 ተሽከርካሪዎችን ለማቆም የሚያስችል የተሟላ የመኪና ማቆሚያ እንዲኖረው ተደርጎ የተገነባም ነው።

ከዚህ ሁሉ ቤተ መጽሐፍቱ ምን ያህል አንባቢያንን እንደሚጠብቁት መገንዘብ አያዳግትም፤ የሁሉም ተቋም ነው። የሕዝብ ቤተመጽሐፍት እንደመሆኑም ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ከታዳጊዎች አንስቶ እስከ አዛውንትና ተመራማሪዎች ድረስ በእዚህ ቤተመጽሐፍት እንደሚገለገሉ ይጠበቃል።

ይህ ግዙፍ ተቋም በተመረቀ ማግስት ወደ ሥራ ገብቷል፤ ገና መጽሐፍ እየተሰባሰበለት ባለበት በዚህ ወቅት ከመጽሐፍት ውጪ 300 ሺ የሃገር ውስጥ እንዲሁም 120 ሺ ዓለም አቀፍ የጥናት ወረቀቶች በቤተመጽሐፍቱ እንደሚገኙም መረጃዎች ያመለክታሉ። ገና ከአሁኑ በየቀኑ ከሶስት እስከ አምስት ሺህ ሰዎች ለንባብ እየጎበኙት ናቸው።

ይህም በሃገራችን ያለው የቤተ መጽሐፍትና የመጽሐፍት እጥረት ከፍተኛ መሆኑን እንዲሁም ሕዝቡ ምን ያህል የማንበብ ፍላጎት እንዳለውም ይጠቁማል። አራት ሚሊዮን መጽሐፍት የመያዝ አቅም አለው፤ ለቤተመጽሐፍቱ ቢያንስ ሁለት ኮፒ ያላቸው ሁለት ሚሊዮን መጽሐፍት ያስፈልጋሉ።

ይህን አይነት ቁመና ያለውን ቤተመጽሐፍት በሚያስፈልጉት መጽሐፍት ለማሟላት ብዙ ሥራዎች ያስፈልጋሉ። የመጽሐፍት ቤቱ ግዝፈት የኢትዮጵያውያንን እና ተቋማትን መጽሐፍት የማሰባሰብ ኃላፊነት ከፍተኛ ያደርገዋል። መጽሐፍቱን ለማሰባሰብ ብዙ ጊዜ መውሰድም የለበትም፤ በጥሪው መሠረት ዜጎች፣ ሃገራዊና ዓለም አቀፍ ተቋማት፣ ወዘተ፣ ለእዚህ ወሳኝ ጥሪ ፈጣን ምላሽ በመስጠት መጽሐፍቱን ለማሟላት ሊረባረቡ ይገባል። እነዚህ ተቋማትና ዜጎች በልገሳው በንቃት እንዲሳተፉ ለማድረግ የተለያዩ የቅስቀሳ ሥራዎች መደረግ ይኖርባቸዋል።

ቤተመጽሐፍቱ የዚህ ዘመን ቤተመጽሐፍት እንደመሆኑ ዘመኑን የዋጀ አገልግሎት እንደሚሰጥ ቢጠበቅም፤ በገበያ ላይ ሊገኙ የማይችሉ የኢትዮጵያን ታሪክ፣ ጥበብ ፣ ወዘተ የሚያመለክቱ መጽሐፍት በእጅጉ ያስፈልጉታል። እነዚህ መጽሐፍት ሊገኙ የሚችሉት ደግሞ በአብዛኛው በግለሰቦች እና በአንዳንድ ተቋማት እጅ ነው። ዜጎች እነዚህ መጽሐፍት በትክክለኛው ስፍራ እንዲገኙ ለማድረግ በመጽሐፍ ልገሳው በዜግነት ኃላፊነትና በንቃት መሳተፍ ይኖርባቸዋል። ቤተመጻሐፍቱን በሚጠበቀው ልክ ታላቅ ቤተመጽሐፍት ማድረግ የሚቻለው የሚወዱትን መጽሐፍ ከመደርደሪያው አንስቶ በመለገስ እንደመሆኑ ዜጎች ለዚህ ታላቅ ጥሪ ፈጣን ምላሽ መስጠት ይጠበቅባቸዋል።

ግለሰቦች በቤተመጽሐፍቱ በአካል ተገኝተው ልገሳውን ሊያደርጉ ይችላሉ። ተቋማት ግን የተለያዩ የማሰባሰቢያ መርሐ ግብሮችን በማዘጋጀት ሠራተኞች፣ ነጋዴዎች፣ አባቶች እናቶች፣ ምሁራን ፣ ወዘተ መጽሐፍት በመለገሱ ተግባር እንዲሳተፉ ግንዛቤ የመፍጠር ፣ የማሰባሰብ ሥራዎችን ጊዜ ሳይወስዱ ማከናወን ይኖርባቸዋል። መጽሐፍትን ለአብርሆት ቤተመጽሐፍት!

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## «እውነት!» ምንድነው?

**ከአስባቸው ደሳለኝ አበሻ (ለንደን)**

እንደምን አላችሁልኝ ውድ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ አንባቢዎች። በቅድሚያ እንኳን ለፋሲካ በአል በሰላም አደረሳችሁ። ለዛሬው ከአንድ ወዳጄ ጋር በስልክ ባደረግነው ውይይትና ጨዋታ ላይ የቀረበልኝ ድንገቴ ጥያቄን በማንሳት ላይ አተኩራለሁ። ነገሩ እንዲህ ነው፤ ከዚህ ወዳጄ ጋር በስልክ እየተጨዋወትን ሳለ በመሃል ጨዋታዬን አቋረጠኝና “እውነት ምንድነው?” ሲል ድንገተኛ ጥያቄ አነሳልኝ። በቀጥታ ጥያቄውን ለመመለስ ብሞክርም እውነትን እንዲህ ነው ብሎ በአንድ አረፍተ ነገር ብቻ ቋጥሮ ለማስረዳት ባለመቻሌ፤ ጥያቄውን ወደ እናንተ ይዤው መጥቻለሁ። በእርግጥ “እውነት” ምንድ ነው?

እውነት ምን እንደሆነ በትክክል ለመረዳት፣ የሰው ልጅ ከአንድ ሚሊዮን አመት በላይ እንደፈጀበት የታሪክ ተመራማሪዎች ቢስማሙም፤ እውነት የተገለፀው በአንድ የፍርድ ወንበር ላይ ነበር። ለምሳሌ፣ አይሁዳውያን እየሱስ ክርስቶስን በመክሰስ በፍርድ አደባባይ ጲላጦስ ዘንድ ሲያቀርቡት እየሱስ መልስ አልሰጠም ነበረ። “ጲላጦስ ‘አንተ እንዲህ ሲከስሱህ ለምን ዝም ትላለህ? አንተ ንጉሥ ነህን? ንገረኝ’ አለው። ጌታ ኢየሱስም መልሶ፡- ‘እኔ ንጉሥ እንደ ሆንኩ አንተ ትላለህ። እኔ ለእውነት ልመሰክር ስለዚህ ተወልጃለሁ፤ ስለዚህም ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤ ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምፄን ይሰማል፤ አለው”። ጲላጦስም፣ እውነት ምንድነው? አለው።

የሰው ልጅ መልስ አጥቶ አንድ ሚሊዮን አመት የፈጀበትን ጥያቄ፣ እኔንም ጓደኛዬ እንደጠየቀኝ ሁሉ ጲላጦስም መልሶ እየሱስ ክርስቶስን “እውነት ምንድነው?” ብሎ ጠየቀው። እውነት በመስቀል ላይ፣ በመከራ ውስጥ መገኘቷን ብትሰቀልም ወደ ላይ ከፍ ከፍ የምትል፣ ብትቀበርም ሲኦልን የምትበረብር፣ ወደ ላይም የምታርግ፣ ፅንታም የምትኖር መሆኗን ከአንድ ሚሊዮን አመት በኋላ የሰው ልጅ እጅግ ዘግይቶ ቢያውቅም፤ አሁንም ድረስ “እውነት ምንድነው?” እያለ እንደ ጲላጦስ መጠየቁን ቀጥሏል። ምክንያቱም እውነት በደጋፊዎች ቁጥር ብዛት አትገለጽም። ለዚህም ማሳያው በኢየሱስ ላይ ከእውነታው የተቃረነ ፍርድ እንዲሰጥ ያጨበጨቡና የጮኹ ብዙዎች መሆናቸው ነው። ለዚህ ይመስለኛል የሰው ልጅ እውነት ምንድነው? የሚለው ጥያቄ ለመመለስ የሚቸገረው። እምነታችን አፋዊ እንጅ ልባዊ ባለመሆኑ ዛሬም ነገም እውነት ምንድ ነው እያልን መጠየቃችን ገና ይቀጥላል።

የእናንተን ባላውቅም በእኔ እምነት ግን የሰው ልጅ፣ በአዕምሮ ብቃቱና በስነ ልቦና አመለካከቱ፣ በፍላጎቱም ሆነ በልቦና መሻት አካባቢውን በራሱ ስሜትና ፍላጎት ተነሳስቶ ዓለምን ለመለወጥ ከፈጠረበት ምኞት ጀምሮ እስከ መቀየር፣ ከመፍጠር እስከ ማጥፋት፣ ደመ ነፍሳዊ እንቅስቃሴዎች፣ እንደሚያደርግ ግልፅ ቢሆንም፤ ከክፋት ደግነትን፣ ከመለያየት አንድነትን፣ ከጦርነት ሰላምን መምረጥ የአንድ ማሕበረሰብ የስልጣኔ መለያው እውነት ነው ብዬ አምናለሁ።በዚህ ምክንያት በጋራም ሆነ በተናጠል የምናደርጋቸው ዘር ተኮር ጥላቻዎችና ፅንፈኝነት በሰው ልጆች ላይ ልናደርስ የምንችለውን የሞራል ልዕልናና ስነልቦናዊ ጉዳትንም አብረን ማሰብና መገመት ይኖርብናል።

ውድ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ አንባቢዎቼ እናንተስ ምን ትላላችሁ?። በእርግጥ፣ የሰው ልጅ መቃብር እስኪዘጋበት፣ አፈር እስኪሸከም ድረስ ፍላጎቱን ለማርካት ሲል በማያቋርጥ ጉዞ የሚጓዝ መንገደኛ ቢሆንም፤ ሰው ራሱ በሰራውና በፈጠረው ውጤት የማይረካ፣ ያለኝ ይበቃኛል የማይል ለግል ዝና ሲል ስግብግብ በስጋዊም ሆነ በነፍሳዊ ፍላጎቱ እርካታን የማያገኝ እንደ ወንዝ ውሀ በጉዞ ላይ ያለ ፍጡር በመሆኑ እውነት ምንድ ነው? ብሎ ቢጠይቅ ብዙም ሊያስገርመን አይችልም።ታላላቅ የሚባሉ፣ በታሪክ መዛግብት ላይ ዛሬም ድረስ፣ ገና ወደፊትም ድረስ የሚዘከሩ ሰዎች ሳይቀሩ በአንድ ወቅት በሰሩት ሐገራዊ ስህተት እስከ መቃብር ድረስ ጥፋታቸው ተከትሎ በውኃ በተሞላው ስምጥ ሸለቆ ውስጥ ታሪካቸው እንዳይገኝ ቀብሮ አስቀምጦታል።

እዚህ ላይ፣ ሰዎች አውቀውም ሆነ ሳያውቁ ከሚያደርሱብን ህመም ለመፈወስ ብቸኛ ምርጫ ጥላቻና በቀል ሳይሆን ፍቅር አሸናፊ መሆንን አስመክረው የሰውን ልጅ ያስደመሙት የሩዋንዳ ሙሽሮችን ታሪክን ለአብነት ብጠቅሰው ደስ ይለኛል።እውነቱ እንደዚህ ነው ከ28 ዓመታት በፊት በሩዋንዳ በነበረው የዘር ፍጅት ባለቤቷን የገደለውን ሰው ይቅር በማለት አባቱ ሲገደል የ14 አመት ልጅ የነበረውን አልፍሬድና የዘር ማጥፋት በተፈፀመበት ወቅት የዘጠኝ ዓመት ታዳጊ የነበረችው የግራቲየን ሴት ልጅ የሷን ወንድ ልጅ እንድታገባ በመፍቀዱ በማህበረሰቡ ላይ የተዘራውን ጥላቻን ከስሩ ነቅለው ጥለውታል።

እአአ 1994 በ100 ቀናት ውስጥ 800 ሺህ የሚያህል ሩዋንዳውያን በተገደሉበት የዘር ጭፍጨፋ የተፈጠረውን የማህበረሰብ ቁስል እንዲሽር የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ዕርቅና ሰላም ለማምጣት የራሷ ድርሻ ቢኖራትም፤ እነዚህን ሙሽሮች የሚያክል አለምን ያስደመመ ዜና ሊሆን ግን አልቻለም። ከዚህ የምንረዳው፣ “እውነት ማለት ከልብ ይቅር የመባባል ፍቅር” መሆኑን ነው።ፍቅር ማለት መከባበር፣ መለማመድ፣ መተሳሰብ፣ ይቅር መባባል መሆኑን ሩዋንዳውያን የሙሽሮቹ ወላጆች በልጆቻቸው ሰርግ ከእምነት ተቋማት እኩል ድርሻ በማበርከት ሐገራቸውን ከእርስ በእርስ እልቂት አትርፈዋታል።ለእኔ እውነት ማለት የሚሰጠኝ ትርጉም እንደዚህ ነው።

በእርግጥ እያንዳንዳችን ስጋ ለባሽ “ሰው” በመሆናችን ብዙ ስህተቶች ልንፈፅም ብንችልም፤ በመቻቻልና በመተሳሰብ ላይ የተመሰረተ ባህል ካዳበርን በወዳጅነት ሰበብ ጥፋቶች ሁሉ በይቅርታ ይሰረዛሉ። ከታላላቅ በጎነቶች ውስጥ አንዱ የሆነው ፍቅርም የሁላችንም ህግ አስከባሪ ዳኛ አሸናፊ ይሆናል። ፍቅር እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ የሚባሉ ውድድሮችን የማይደግፍ በመሆኑ እውነተኛ ስሜታችንን በቅንነት ስለምንገልፅበት ለጋራ ችግሮቻችን ሁሉ በጣም አስፈላጊ ከሆኑት እውነቶች አንዱ ይሆናል። ብዙ ጊዜ በተሳሳተ አመለካከት ህዝብ በፍቅር እንዳይኖር እራሱ የሰው ልጅ ዋና ጠላት ቢሆንም፤ አንዳችን ለአንዳችን አስፈላጊ መሆናችንን አምነን በመቀበል ጠንካራ መተማመን ፈጥረን መልካም ግንኙነት እንድንመሰርት ይረዳናል።

ሰላምን ከወደድን ጦርነትን እንጠላለን። ሥርዓት አልበኝነትን ከጠላን ሥርዓትን እንወዳለን። በሌላ አነጋገር የፍቅር ተቃራኒ የሆነውን ጥላቻን እንጠላለን። ተቃርኖውን ሊፈታ የሚችለውን ውጥረት ማስወገድ ከቻል ደግሞ እውነት የሚለውን የሰው ልጅ የሞራል ልዕልና የበላይነትን ለማረጋገጥ ጥጉ ላይ ደርሰናል ማለት ነው። ሰሞኑን የትንሳኤን በዓል ምክንያት በማድረግ ለጎዳና ተዳዳሪና ቤተሰብ ለሌላቸው ህፃናትና ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው አቅመ ደካሞ አረጋውያን በቤተ መንግሥትም ሆነ በከተማ አስተዳደሩ እንዲሁም ቅን ኢትዮጵያውያን ተሰባስበው ያደረጉት ማዕድን የማጋራት መርሀ ግብር የዚሁ የአገራዊ መግባባቱ፣ የመተሳሰብና የመቻቻል ባሕል ምልክት በመሆኑ የሚበረታታ የሰባዕዊነት ተግባር ነውና መቀጠል ይኖርበታል።

እንደ ሩዋንዳዎቹ ዘር ተኮር ትንኮሳንና ጥላቻን ተፀይፈን የአካባቢያችንን መጥፎ ባህሪን ለመቀየር፣ ቂም በቀልን ቀብረን በመተሳሰብ ብሔራዊ ውይይት በማድረግ ችግሮቻችንን መፍታት እንደምንችል ካረጋገጥን አለም በእርግጥ ያከብረናል። አገራዊ አጀንዳችንን እውነት ለማድረግ ከገባንበት የጦርነት ቀጠና እንዴት ወደ ሰላም ድርድር ለመሸጋገርና ለመመካከር ቅን የሐይማኖት አባቶች፣ የበሳል ፖለቲካ አመራሮች፣ ታዋቂ ሰዎችና ምሁራኖች እንዲሁም የሞያ ስነ ምግባር የገዛቸው ጋዜጠኞች ያስፈልጉናል።ያስፈልጉናል ብቻ ሳይሆን የዝግጅቱ አስተባባሪ የመፍትሔው አካል ሆነው ለሃገራዊ መግባባት መሰለፍ ይኖርባቸዋል። ለእኔ እውነት ማለት ይህው ነው። እናንተስ ምን ትላላችሁ? ለዛሬው አበቃሁ፤ ቸር ይግጠመን።

# ነፃ ሃሳብ

# በበጎ ሰብዕና የነገዋን ታላቅ አገር እንገንባ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ለአንድ አገር የእድገትና የስልጣኔ ምንጭ ከሆኑ የማኅበረሰብ እሴቶች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ለበጎነት የሚያበቃው መልካም ሰብዕና ነው። መልካም ሰብዕና የሌለው አገርና ሕዝብ ነውር የሚያውቅ አዲስ ትውልድ መፍጠር አይቻለውም። ካለ መልካም ሰብዕና መልካም አገርና ትውልድ አይፈጠርም። ታላቅ አገርና ሕዝብ ለመፍጠር ከመነሳታችን በፊት መጀመሪያ እኛ የታላቅ አስተሳሰብና ሰብዕና ባለቤቶች መሆን ይጠበቅብናል። እንደ ወላጅ አሁን ላይ ለልጆቻችን የምናስተምራቸው ምንድነው? ለታናናሾቻችን ምን ዓይነት ቤተሰብ ነን? ነገ ላይ በእኛ በኩል አገር የሚዋጁ ትውልዶች ይፈጠራሉ። አሁን የምንሆነው ነገር የነገዋን ኢትዮጵያ፣ የነገውን ትውልድ የመወሰን ጉልበት አለው። አገር እኮ የዜጎቿ የአስተሳሰብ ውጤት ናት። በየትኛውም እውቀት መዝኑት አገር ዜጎቿን ነው የምትመስለው ስለዚህም እኛ የኢትዮጵያ መልኮች ነን፤ ኢትዮጵያን የሳልናት እኛ ነን። አሁን ላይ እንደ ችግርም ሆነ እንደ መልካም ዕድል ከበውን ያሉ ነገሮች ሁሉ በእኛ ሰብዕና የተሳሉ ናቸው።

ሰብዕና ወንዝ ነው፤ ከግለሰብ ተነስቶ ወደ ማኅበረሰብ የሚፈስ። ከዜጎች ተነስቶ ወደ አገርና ትውልድ የሚጎርፍ። ኢትዮጵያም የትናንቶቹ አባቶቻችን ሥጦታችን ናት። እኛም በበጎና በተገባ የአባቶቻችን ሰብዕና የነገዋን ኢትዮጵያ የመፍጠር ግዴታ አለብን። በዘርና በጎሳ፣ በቋንቋና በቦታ እየተባላን የምናፈራው የጋራ ልዕልና የለም። በዓለም አቀፍ ደረጃ በአገራት መካከል የሚታየው የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የስልጣኔ ልዩነት በዚያች አገር ላይ የሚኖሩ ሕዝቦች የፈጠሩት የአስተሳሰብ ልዩነት ነው። ሰብዕና ማረፊያው አስተሳሰብ ነው። በአስተሳሰቡ የላቀ ማኅበረሰብ በኢኮኖሚው፣ በፖለቲካው የላቀ አገርና ሕዝብ ይፈጥራል። በሰብዕናው ምስጉን የሆነ የፖለቲካ ፓርቲ ነገ ላይ ታሪክ የማይረሳውን የአንድነት ግንብ ይገነባል እንጂ በሀሳብ ልዩነት ጦርነት አይከፍትም። በየትኛውም እውቀት መዝኑት አገራዊ ችግሮቻችን ከዜጎቻችንና ከፖለቲካ ፓርቲዎቻችን የሰብዕና ግድፈት የመነጩ ሆነው እናገኛቸዋለን። ዜጋ ጨዋነት ሲርቀው... አገር ሊመራ የተሰናዳ የፖለቲካ ፓርቲ ራስ ወዳድነትን ሲያስቀድም ትውልድ መረን ይሆናል። እነዚህ ሁሉ ችግሮች በአንድ ይሆኑና በጦርነትና በመለያየት የምታምንን አገር ይፈጥራሉ። ስለዚህ የሚያስፈልገን አገር ገንቢ ሰብዕና ነው። የሚያስፈልገን ከዛሬ አርቆ የሚያይ ዓይንና አእምሮ ነው።

የሰው ልጅ የመጀመሪያው ጥበብ፣ እግዚአብሔርን መፍራት ነው። እግዚአብሔርን መፍራት ደግሞ ከበጎ ስነ ምግባር የሚጀምር የአእምሮ ርምጃ ነው። ሰው ከሥርዓት ሲርቅ አውሬ ነው። ሰው በራስ ወዳድነት ሲረታ ምንም ነው። ለዚያም ነው አገር መታደግ አቅቶን አውሬም ምንምም የሆንነው። ሰብዕና ከግለሰብ የሚጀምር ሰፈርና መንደርን አካሎ አገር ላይ የሚያርፍ የዘመናዊ አስተሳሰብ ውጤት ነው። ዘመናዊነት መነሻውም መድረሻውም ማኅበረሰብ ነው። ማሰብ ስንጀምር..በእውቀትና በማስተዋል ስንበረታ ከማንም በፊት ቀድመን የምናየው ማኅበረሰባችንን ነው። ከምንም በፊት የምንረዳው የአንድነትን ኃይል ነው። በሥነ ምግባር ለታነጸና አርቆ ለሚያይ ባለአእምሮ ሕዝብ የምንም ነገር ቀዳሚ ጉዳዩ ነው። ብዙዎቻችን ግን ይሄን እውነት አናውቀውም፤ ለብዙዎቻችን ስልጣኔ ከራስ እውነትና እሴት መራቅ ነው የሚመስለን። ከራስ እውነት መሸሽ፣ ከራስ ማህበራዊ ልማድ ማፈንገጥ ነው የሚመስለን። ዘርና ብሔርን መሠረት ባደረገ የእኔነት ስሜት አገር የሚገነባ የሚመስለንም ሞልተናል። እንደ ዜጋም፣ እንደ ፖለቲካ ፓርቲም ከዚህ አፍራሽ አመለካከት መውጣት አዲሲቷን ኢትዮጵያ ለመፍጠር ቀዳሚው መስፈርት ነው።

ስልጣኔ በምንም መልኩ ራስን አያስክድም። በምንም መልኩ ባህልና ሥርዓትን አይደፍርም። በምንም መልኩ መረንና ራስ ወዳድ አያደርግም። በምንም መልኩ ተነጋግሮ የመስማማትን ጥበብ አይሰውርም። የዘመነ ጭንቅላት ከሥርዓትና ከነውር ወጥቶ አያውቅም። ራሳችንን መፈተሽ ይኖርብናል። ትልቅ አገርና ሕዝብ ይዘን በአንድነት መቆም ያልቻልነው ለምንድነው ብለን ራሳችንን መጠየቅ አለብን። ሰፊ ታሪክ፣ ጥልቅ ባህል ከቦን የማንረባ ሆነን የቆምነው ለምንድነው ስንል እንጠይቅ። ለብዙዎቻችን አራዳነት ሥርዓትን መተው፣ ነውር አለማወቅ ወይም ደግሞ ከባህልና ወግ ያፈነገጡ ድርጊቶችን መከወን ነው። ይሄ ግን የዘመናዊነት ባህሪ አይደለም። ይሄ በማኅበረሰባችን ተረት «ከርሞ ጥጃነት» ነው። ስልጣኔ ከትናንት ሌላ መሆን፣ ከአምናው አንድ ርምጃ ፈቀቅ ማለት ነው። አሁን ላይ ብዙዎቻችን ስልጣኔ ሳይገባን በከንቱ የምንኖር ነን። መልካም ስብዕናን ሳንላበስ ብሩህ ነገን የምንናፍቅ ነን። ተነጋግረን ሳንግባባ ትልቅ ተስፋ የምንጠብቅ ነን። መልካም ነገሮች ያሉት በመልካም አመለካከት ውስጥ እንደሆነ ገና አልገባንም።

በአንድ አገር ላይ ለውጥ ለማምጣት ትምህርትና የመሳሰሉ ዋጋ ያላቸው ነገሮች ብቻቸውን በቂዎች አይደሉም። እውቀት ያለ መልካም ሰብዕና ዋጋ የለውም። አሁን ላይ ለአገራችን ችግር እየሆኑ ያሉት የተማሩ ግለሰቦች ናቸው። ከትናንት እስከዛሬ የስጋታችን ምንጮች ፊደል የቆጠሩ እናውቃለን ባዮች ናቸው። ብዙ ያልገቡን ነገሮች እንዳሉ ይሄ አንዱ ማሳያ ነው። ትምህርት ለአንድ አገር የስልጣኔ ዋልታና ማገር ሆኖ ሳለ እኛ ግን ለችግርና ለመከራ እንጠቀምበታለን። መማር ከትናንት እስከዛሬ አበሳ የሆነባት አገር ላይ ነን። መማር እኮ ክፉ ነገር ሆኖ አይደለም፤ መማር መቼም የትም ክፉ ሆኖ አያውቅም፤ እንዲያውም ዓለም የአሁኑን ስልጣኔ ያገኘችው ፊደል በቆጠሩ ባለ አእምሮዎች ነው። ችግሩ ያለው ከእኛ ነው። ምክንያቱም ስንማር በኩረጃ ነው፣ ስናልፍ በሙስና ነው። ወደ ስልጣን ስንመጣ በብሔር ነው። አገርና ትውልድን መሠረት አድርገን የተራመድንበት አንድም የፍትህ ጎዳና የለንም። በጣም የሚገርመው ደግሞ ዛሬም ያን ትናንትና ብዙ ዋጋ የከፈልንበትንና የተወለካከፍንበትን ጎርባጣ ጎዳና መድገማችን ነው። ልባችንን ለክፋት እያስገዛን የምናስበው ሀሳብ፣ የምንቀመጠው ስብሰባ፣ የምንመራው ሰልፍ፣ የምንማረው ትምህርት ያጠፉናል እንጂ አይጠቅሙንም። ከምንም በፊት ጥሩነትን መማር አለብን፤ ከምንም በፊት ሰውነትን እንልመድ። ከምንም በፊት አገርና ትውልድን እናስብ። ከምንም በፊት ፈጣሪን እንፍራ። ይሄ ሁሉ በሌለበት ሁኔታ ተምረንም ሆነ ባንማር የምናመጣው ለውጥ የለም።

ውስጣችሁ ርህራሄ ይኑር፤ በመልካምነት ካልታገዘ መማር ብቻውን ጥቅም የለውም። ከሚሠሩ እጆች እኩል፣ ከሚያስቡ ጭንቅላቶች እኩል መልካም ሰብዕና ያስፈልገናል። ሁላችንንም የሚያስማማ አንድ እውነት ቢኖር ኢትዮጵያ ተምረናል በሚሉ ክፉ ልቦች እየደማች መሆኗ ነው። ከእንግዲህ ለምትፈጠረው አዲሲቷ ምድር ግን መባረክን እናስቀድም። የተባረከ ልብ ባይማርም የተማረ ነው። የተባረከ ልብ በወዳጁ ላይ ክፉ አያደርግም። የተባረከ ልብ ለሥርዓት የተገዛ ነው። ድሮነትን ሳስብ እደነቃለሁ፤ ፈጣሪ አምላክ በአባቶቻችን ልብ ውስጥ በዝቶና ተትረፍርፎ ነበር እላለሁ። እንደዛማ ባይሆን ባልሰለጠነ ዓለም ላይ ቆመው ለዘመናዊው ዓለም ትዕንግርት የሆኑ አክሱምና ላሊበላን አያንጹልንም ነበር። እንደዛ እማ ባይሆን በጦርና ጎራዴ ታንክና መድፍ አይማርኩም ነበር። እንደዛማ ባይሆን ከእኔና ከእናንተ ተሽለው ዛሬም ድረስ በመልካምነት አይጠሩም ነበር። እነርሱ የጥሩ ሰብዕና ባለቤቶች ነበሩ። ነውር የሚያውቁ በባህላቸው የተገሩ የመልካም ነፍስ ባለቤቶች ነበሩ። ለትውልድ የሚቀር መልካም ሥራ እንሠራ ዘንድ የዋሆቹን አባቶቻችንን መምሰል አለብን።

ብዙዎቻችን አሁን ላይ የምንማረው አገር ከመጥቀም ይልቅ አገር ለመጉዳት እየሆነ ነው። ስለሚያበላ ሥራ፣ ስለሚያተርፍ ንግድ እንጂ፤ እንዴት አድርገን አገራችንን እንደምንጠቅም አናስብም። መጀመሪያ ለአገራችን እንኑር፤ መጀመሪያ ቅደም ተከተላችንን እንወቅ።

> **ወዴትም ይሁን ለምናደርገው ጉዞ ጥሩ ሰው መሆን ከፍ ያለ ዋጋ አለው፡፡ የምንራመደው በእግራችን ቢሆንም፣ የምናስበው በጭንቅላታችን ቢሆንም የምንመራው ግን ውስጣችን በተከልነው ማህበረሰባዊ እሴት ነው፤ እርሱም ሥርዓት ይባላል፡፡ መልካም ሰብዕና በዙሪያው በርካታ ንቦችን እንደሚሰበስብ ሸጋ ጠረን እንዳለው አበባ ነው፡፡ የመጨረሻው የውበት ጥግ፣ የመጨረሻው የስልጣኔ መገለጫም ነው፡፡ እርሱ መልካም የሚሸት የነፍስ ሽቶ ነው፡፡**

ለአገራችን መኖር ከጀመርን አገራችን የምትከፍለን ብዙ ነገር አላት። ችግሩ ከፈረሱ ጋሪው ሆኖ ማስቀደም ያለብንን አለማወቃችን ነው። ሕይወት በሁኔታዎችና በሀሳብ የተቃኘ ቅደም ተከተል አላት። በእዚያ ቅደም ተከተል ውስጥ መጓዝ ስንችል ብቻ ነው ለራሳችንም ለሌሎችም ልክ የምንሆነው። አሁን ላይ እንደ አገር ቅደም ተከተላችን ተዛብቷል። ወደ ኋላ ተመልሰን የተውነውን፣ የረሳነውን ነገር ማስተካከል አለብን። መጀመር ካለብን መጀመር ይኖርብናል። እንደ አገር መቅደም ያለበትን ማስቀደም ካልቻልን ውስብስብ ችግሮችን እየፈጠርን ነው የምንሄደው። በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ ምድር መቅደም ያለበት ሰላም ነው። እርቅ ነው። አንድነትና ወንድማማችነት ነው። እኚህ የህልውና በኩሮች እውቅና ባላገኙበት ሁኔታ ላይ የምናመጣው ለውጥ አለ ብዬ አላስብም።

እስኪ ይሄን ጊዜ ለኢትዮጵያ እንስጥ። ችግሮቻችንን የምናስተካክልበት፣ ተነጋግረን የምንግባባበት ይሁን። እስኪ ከእንግዲህ ባለው ጊዜአችን፣ ከእንግዲህ ባለው ወጣትነታችን፣ ከእንግዲህ ባለው የስልጣን ዘመናችን ከእኔነት ሸሽተን አገራችንን እናስቀድም። ያኔ የምንፈልገው ነገር ሁሉ በራሱ ጊዜ መስተካከል የሚጀምር ይመስለኛል። ምክንያቱም ማስቀደም ያለብንን አስቀድመናልና። መልካም አስተሳሰብን ሳንይዝ የምንሻገረው ወንዝ፣ የምናሳካው ህልምና ራዕይ የለም። ራሳችንን በሰብዕና ሳንገነባ የምንጀምረው ማንኛውም ነገር ጊዜአዊ ነው። ሰብዕና የማንነት መስተዋት ነው። ራሳችንን የምናይበትና የምናሳይበት ነጸብራቃችን ነው። ማን እንደሆንን፣ ከየት ተነስተን ወዴት እንደምንሄድ የምንመራበት አቅጣጫ ጠቋሚ መሣሪያችን ነው። የዚህ የሰብእና ማረፊያ ደግሞ አገርና ሕዝብ ከፍ ሲል ደግሞ ትውልድ ነው።

በሕይወት መንገድ ላይ የሚወድቁ ሰዎች ራሳቸውን በሰብና ያልገነቡ ናቸው። ራሳቸውን በሰብዕና የገነቡ ሰዎች አይወድቁም፤ ቢወድቁ እንኳን ዳግም ለመነሳት የሚያስችል ሙሉ ኃይል አላቸው። አሁን ላይ አገራችን እየተቸገረች ያለችው በወጣቱ የሰብዕና ግድፈት ነው። ከአገሪቱ የሕዝብ ቁጥር ከፍተኛው ወጣት በሆነባት አገር የሰብዕና ግንባታ የአንበሳውን ድርሻ መያዝ አለበት። በአእምሮና በስነልቦና ያልተገነባ ወጣት ጥፋት እንጂ ልማት አያውቅም። አላማችን ታላቅ አገርና ሕዝብ መፍጠር ከሆነ ወጣቱ በስነ ምግባር መታነጽ አለበት። የፖለቲካ ፓርቲዎች ከክሽፈት ወጥተው መታደስን ይማሩ። ያ ካልሆነ ህልማችን ፍሬ አያፈራም። በሕይወታችን፣ በኑሯችን መላቅ ከፈለግን መጀመሪያ ልናደርገው የሚገባን በስነ ምግባራችን ተመስጋኞች መሆን ነው። ህልማችን ከሕይወት መላቅ ከሆነ ከሁሉ በፊት ራሳችንን ለማኅበረሰቡ የተገባ ነፍስና ስጋን እናልብሰው። አገር የማኅበረሰብ መፈጠሪያ ናትና።

ማኅበረሰብ የማያውቀው፣ አገርና ሕዝብ ያልተቀበለው ሰውነት ምን ቢያምር ዋጋ አያወጣም። ዋጋችን ያለው ማኅበረሰባችን ጋ ነው። ሕዝብ እንዲወደን ሕዝብ እንዲመርቀን ሆነን እንኑር። ሕዝብ ከጠላን የምንሄድበት የሕይወት ጎዳና አይቀናንም። ለዚህ ደግሞ የመልካም ሰብዕና ባለቤት ሆኖ መኖር ከፍ ያለ ዋጋ አለው። ከትናንት እስከዛሬ ዓለም ላይ ያሉ ስኬታማ ሰዎች ከስኬት ለመድረስ ከትጋታቸው እኩል አንጻባራቂ ሰብዕናን የተላበሱ እንደሆኑ ይነገራል። እንደዚሁም በሳይንሱ ዘርፍ የሚገኙ በርካታ ፈላስፎች መልካም ሰብዕና ወደፈለግንበት ስፍራ የምንጓዝበት እንቅፋት አልባ ጎዳና ነው ይላሉ። እዚህ ጋ ሰብዕና ስንል እያንዳንዱን ድርጊታችንን ያጠቃልላል። አለባበስ፣ አመጋገብ፣ አነጋገር፣ ከሰዎች ጋር ያለን መስተጋብር ለባህልና እሴት የምንሰጠው ዋጋ፣ ለታላላቆቻችን ያለን ክብር፣ ለቤተሰቦቻችን በአጠቃላይ ለማኅበረሰቡ ያለንን አተያይ የሚያጠቃልል ነው። አገር ወደ ፊት እንድትቀጥል በጥሩ ስነምግባር የታነጹ ህልም ያላቸው ዜጎች ያስፈልጓታል። ይሄ ባልሆነባት አገር ላይ ሕዝብም ሆነ መንግሥት ያለትውልድ የሚሆን አመርቂ ሞራል አይኖረውም።

የብዙዎቻችን ነገ የሰመረ ይሆን ዘንድ በራዕይ መኖር ግድ ይለናል። ለዚህ ደግሞ የተባረከ ልብ ያስፈልገናል። መባረክ መማር አይደለም፣ መባረክ ብልጠት አይደለም፤ መባረክ በእኛ መኖር ሌሎች እንዲኖሩ መፍቀድ ነው። መባረክ በደግነትና በቅንነት ወደ ፊት መራመድ ነው። መባረክ ለአገርና ለሕዝብ ሲሉ ሁሉን መተው ነው። ወዴትም ይሁን ለምናደርገው ጉዞ ጥሩ ሰው መሆን ከፍ ያለ ዋጋ አለው። የምንራመደው በእግራችን ቢሆንም፣ የምናስበው በጭንቅላታችን ቢሆንም የምንመራው ግን ውስጣችን በተከልነው ማህበረሰባዊ እሴት ነው፤ እርሱም ሥርዓት ይባላል። መልካም ሰብዕና በዙሪያው በርካታ ንቦችን እንደሚሰበስብ ሸጋ ጠረን እንዳለው አበባ ነው። የመጨረሻው የውበት ጥግ፣ የመጨረሻው የስልጣኔ መገለጫም ነው። እርሱ መልካም የሚሸት የነፍስ ሽቶ ነው። ውብ..ውብ የምንሸትበት፣ ቆንጆ... ቆንጆ የምንጠርንበት እጹብ የሕይወት መዐዛ እለዋለሁ። ኢትዮጵያን የምንወድ ወጣቶች በዚህ እውነት እንኑር። ነጋችንን በዚህ ዘለዓለማዊ እውነት እንገንባ።

ያለ እኛ ኢትዮጵያ ምንም ናት፤ መኖራችን ለአገር ይጠቅማልና ስንኖር በምክንያትና በስሌት ይሁን። በተገራ ማኅበረሰባዊ ሥርዓት መራመድ ድሀዋን አገራችንን ወደ ፊት ያራምዳታልና የሚጠቅመንን ለይተን እንወቅ። ሰብዕናችሁ ላይ እክል ካለ አሁኑኑ ቆም ብላችሁ ራሳችሁን ለማስተካከል ሞክሩ እንጂ ከነ ግድፈታችሁ ወደ ፊት ለመሄድ አትሞክሩ። ልሂድ ብትሉ እንኳን አይቻላችሁም። ልሂድ ብትሉ እንኳን መንገድ ላይ ነው የምትቀሩት። ፍሬኑ የተበላሸ መኪና ታውቃላችሁ? ሰብዕናው የተበላሸ ሰው ፍሬኑ እንደተበላሸ መኪና ነው። ሁለቱም ሩቅ መሄድ አይችሉም፤ ቢሄዱ እንኳን ፍጻሜአቸው ገደል መግባት ነው። የአገራችን አሁናዊ ችግሮችም እንዲህ ናቸው። ዛሬ ላይ አገራችንን ገደል እየከተቱ ያሉ አስተሳሰቦች፣ ድርጊቶች የዚህ ፍሬ ውጤቶች ናቸው። ሰብዕናው የተበላሸ ወጣት፣ ሰብእናው የተበላሸ የመንግሥት ባለስልጣን፣ ሰብእናው የተበላሸ ተማሪ ይዘን ወዴትም መሄድ አንችልም። መጀመሪያ ፈርሰን እንሥራ። እየሄድን የምንቆመው፣ እየገነባን የምናፈርሰው፣ እየሳቅን የምናለቅሰው መሠረታችን ስለተበላሸ ነውና ገደል ከመግባታችን በፊት የሕይወታችንን መሪ ሰብዕናችንን እናስተካክል እያልኩ ላብቃ። ሰላም!

# ወቅታዊ

# «በወልቃይት፣ ጠገዴና ጠለምት ሕዝብ ላይ የተፈፀመው ነገር ከቅኝ ግዛት ወረራ ጋር ተመሳሳይ ነው»

**-ጌታ አስራደ (ረዳት ፕሮፌሰር)**

**በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የተካሄደው የወልቃይት፣ ጠገዴና ጠለምት ጉዳይ ጥናት ቡድን መሪ**



ፎቶ- ፀሐይ ንጉሴ

**ወርቁ ማሩ**

የጎንደር ዩኒቨርሲቲ በወልቃይት፣ ጠገዴና ጠለምት ሕዝብ ላይ ካለፉት አርባ ሁለት ዓመታት ጀምሮ የደረሱትን ዘርፈብዙ በደሎች አስመልክቶ 21 አባላት ያሉት የጥናት ቡድን በማዋቀር እና በርካታ የመረጃ ምንጮችን በማሰባሰብ ለ15 ወራት የዘለቀ ጥናት ካካሄደ በኋላ የጥናት ውጤቱን በቅርቡ ይፋ ማድረጉ ይታወቃል። ጥናቱ ሳይንሳዊ የጥናት መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ በርካታ ናሙናዎችን በመውሰድ የተከናወነ እንደሆነም የጥናት ቡድኑ ገልፆ ነበር። በጥናቱም በወልቃይት፣ ጠገዴና ጠለምት ሕዝብ ላይ ማንነትን መሠረት ያደረጉ ጅምላ ጭፍጨፋዎች መፈጸማቸው ይፋ ተደርጓል። እኛም ይህንን መነሻ በማድረግ በጥናቱ አካሄድና አጠቃላይ የጥናት ሂደት እንዲሁም የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶችን በተመለከተ ከጥናት ቡድኑ መሪ ረዳት ፕሮፌሰር ጌታ አስራደ ጋር ቃለምልልስ አድርገን ያጠናቀርነውን እንደሚከተለው ይዘን ቀርበናል፤ መልካም ንባብ።

**አዲስ ዘመን፡- በቅድሚያ እስኪ የጥናቱ መነሻ ምን እንደነበር እና ጥናቱን ለማካሄድ የሄዳችሁበትን መንገድ ይግለፁልን።**

**አቶ ጌታ፡-** ዩኒቨርሲቲዎች የተቋቋሙለት ዓላማ አላቸው። ይህም በዋናነት በሦስት አገልግሎቶች ላይ የተመሠረተ ነው። እነዚህም መማር ማስተማር፤ የማኅበረሰብ አገልግሎት እና ጥናትና ምርምር ማድረግ ናቸው። የመምህራንም ድርሻ በነዚህ ላይ ያተኩራል ማለት ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በመማር ማስተማር፤ በማኅበረሰብ አገልግሎት እና በጥናትና ምርምር ሰፊ ሥራ ሲሠራ ቆይቷል፤ አሁንም እያደረገ ይገኛል።

ጥናትና ምርምር ሲካሄድ ደግሞ ችግር ፈቺ የሆነ፣ የማኅበረሰቡን ችግር ነቅሶ በማውጣት እና መፍትሄውንም ጭምር በማመላከት የመንግሥት እቅድ እና የፖሊሲ ግብአት እንዲሆን ማድረግ ነው።

እንደሚታወቀው በማኅበረሰባችን ውስጥ በተለይ ግብርና መር ኢኮኖሚ ነው እስካሁን ድረስ የሚተገበረው። ከዚህ ጋር ተያይዞ ጎንደር ዩኒቨርሲቲም አካባቢው በብዛት ያለው አርሶ አደር እንደመሆኑ በግብርና፣ በጤና፣ በምጣኔ ሀብት ዙሪያ በማኅበራዊ ዘርፎች ሁሉ በየጊዜው ጥናትና ምርምር ያደርጋል።

አንድ ጥናት ሲጠና እንዲሁ አይጠናም። መነሻ ምክንያቶች ይኖሩታል። ለጥናቱ ገፊ ምክንያቶች ምንድናቸው የሚለው የመጀመሪያ ወደተግባር ለመግባት የሚያስችል መነሻ ነው።

ዩኒቨርሲቲው በማንኛውም ጉዳይ ላይ ጥናት ለማካሄድ ችግር አለ ወይ፤ ለነዚያ ችግሮችስ መፍትሄ ያስፈልጋቸዋል ወይ፤ የሚለው ነው። ስለዚህ ጥናት ለማካሄድ ድንበር የለውም። ቦታ አይገድበውም። የችግሩ ዓይነት ሊገድበው አይችልም።

ሁላችንም እንደምናውቀው ወልቃይት፣ ጠገዴና ጠለምት አካባቢ የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ጥናት ለማድረግ የተነሳበት ምክንያቶች አሉ። የመጀመሪያው ነገር አካባቢዎቹ እንደሚታወቀው እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ የጎንደር ክፋይ የሆኑ አካባቢዎች ናቸው። ይህም ማለት ለዘመናት የጎንደር እና የትግራይ ክፍላተሃገራት ድንበር የተከዜ ወንዝ ፤ ሁለቱ ሕዝቦች ደግሞ ለረጅም ጊዜ በጥሩ ጉርብትና ምናልባትም ተቀራራቢ ማኅበራዊ ሥነልቦናና ታሪክም ጭምር ያላቸው ናቸው ።

ሁለቱ ሕዝቦች በግልጽ ጦርነት ውስጥ የገቡበት ጊዜም የለም። የድንበር ይገባኛል ያነሱበትም ጊዜ የለም። ነገር ግን በ1968 ዓ.ም ወደበረሃ ወርዶ የትጥቅ ትግል የጀመረው ሕወሓት አንድ ማኒፌስቶ ይዞ መጣ። ይህ ማኒፌስቶ ወይም ፍኖተ መርህ አንድ አስደንጋጭ ነጥብ በውስጡ ይዟል። ከዚያ በፊት የሌለ ታሪክ እንደተደረገ ተደርጎ ወጣቱን ሊሰብክ የሚችል በተለይ ደግሞ አብሮ ለዘመናት የኖረውን የአማራና የትግራይ ሕዝብ ጠላት እንደሆኑ ተደርጎ እዚያ ማኒፌስቶ ውስጥ በግልጽ ሰፍሯል። ትግሌ ከአማራ ጋር ነው፤ ዘላለማዊ ጠላቴ አማራ ነው፤ ለትግራይ ሕዝብ መውደቅ ምክንያት አማራ ነው የሚል አስደንጋጭ ሃሳብ ነው ይዞ የመጣው።

ይህ ብቻ ሳይሆን የትግራይ ወሰን ተከዜ ብቻ ሳይሆን እነወልቃይትን፣ እነጠገዴን፣ እነጠለምትን እነራያን፣ በአፋር በኩልም እንዲሁ በርካታ የአፋር አካባቢዎችን፣ እና የጎንደርና የወሎን ግዛት የሚያካትት እንደሆነ አድርጎ ነው ካርታ አዘጋጅቶ የመጣው።

ሕወሓት በደደቢት ላይ በሽፍትነት ከጀመረ በኋላ ማኒፌስቶ አዘጋጅቶ በ1972 ዓ.ም ነሐሴ መጨረሻ አካባቢ ተከዜን ተሻግሮ የጎንደር ክፍለሃገር አካል የሆነውን ወልቃይትን መውረር ጀመረ። ከዚያ አድማሱን እያሰፋ የደርግ መንግሥት በተለያዩ ውስጣዊና ውጫዊ ችግሮች ምክንያት አጣብቂኝ ውስጥ በነበረበት ወቅት በሽፍትነት የነበረው ሕወሓት የጎንደርን ክፍለሃገር በተለይ በሰሜን በኩል ያለውን ወልቃይትን፣ ጠገዴን እና ጠለምትን ወደ መውረር ሄደ።

በዚህ ምክንያት የወልቃይት፣ጠገዴና ጠለምት አማራዎች ወረራ ተካሄደባቸው። በጣም ደም አፋሳሽ እና በሂደትም የዚያን አካባቢ ማኅበረሰብ ከፋኝ የሚል የራሱን የትጥቅ ትግል እስከማደራጀት የሄደበት ሁኔታ ነበር። በዚህም ከሕወሓት ጋር ለአስርት አመታት በጦርነት ቆይቷል። ይህ እንግዲህ ከደርግ ጋር ከሚዋጋው ባሻገር ነው ማለት ነው። በሂደት በማኒፌስቶውም እንደተቀመጠው ይህንን አካባቢ ሕወሓት የመንግሥትነት ስልጣን ሲይዝ ወደትግራይ የመጠቅለል ሥራ ሠራ።

ይህን ሲሠራ እንግዲህ ምንም ዓይነት ሕገመንግሥታዊ መሠረት የለውም። ሁለተኛ የአካባቢውን ኅብረተሰብ አላወያዩትም። ያንን የሽግግር ወቅት እና ውዥንብሩን እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም እና ስልጣኑን ተገን በማድረግ ወደትግራይ ክልል እንዲካለል ሲያደርግ እዚያ አካባቢ ያለው ኅብረተሰብ ወደነፃነት እንቅስቃሴ እና ትግል በመግባት ብዙ መስዋእትነት ከፍሏል።

በዚህ ምክንያት በመቶ ሺዎች የሚቆጠር የአካባቢው ማኅበረሰብ አካባቢውን ጥሎ እንዲሰደድ ተደርጓል። በእኛ ጥናት ያረጋገጥነው ወረራው የቅኝ ግዛት ወረራ ነው የሚመስለው። ምክንያቱም ቅኝ ግዛት ሲመጣ በጉልበት ተጭኖህ ሊገዛህ ነው የሚመጣው። ሀብትህን ሊዘርፍ ነው የሚመጣው። ሊያሳድድህና ሊገድልህም ጭምር ነው የሚመጣው። ሕወሓትም ይህን ነው የፈጸመው።

ከዚያ በኋላ የወልቃይት ጠገዴና ጠለምት ማኅበረሰብ በየትኛውም ዓለም እንዲበተን ሆነ። አሁን እኛ ባገኘነው ጥናት መሠረት ከእያንዳንዱ ቤተሰብ 26 ነጥብ 5 ከመቶ ለስደት ተዳርጓል፤ 19 ነጥብ5 ከመቶ ታፍኖ የት እንደገባ አይታወቅም፣ እንዲሁም 29 ከመቶ ለሞት ተዳርጓል።

ሌላኛው የጥናታችን መነሻ የነበረው በዚህ አማካኝነት ይህንን አቤቱታ በመስጠት እንደነ ልሳነ ግፉአን፣ እንደነ እንደነ ኢሰመጉ፣ እነ ሞረሽ ወገኔ፣ በቅርቡም የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ጥናት አካሂደው እዚያ አካባቢ ብዙ ግፍ እንደደረሰ የጥናት መነሻ የሚሆኑ ነገሮች ተቀምጠዋል።

ከዚያ በኋላም የወልቃይት፣ ጠገዴና ጠለምት ሕዝብ ማንነቴ ይመለስልኝ፣ በጉልበት ያለማንነቴ ወደትግራይ ተካልያለሁ በማለት ጉዳዩን የማንነት አስመላሽ ኮሚቴ በማቋቋም ሕጋዊ በሆነ መንገድ እስከ ፌዴሬሽን ምክር ቤት ድረስ አድርሶት ላለፉት ስምንት አመታት አካባቢ የተጀመረው የማንነት አስመላሽ ኮሚቴ ጉዳይ እስካሁን እልባት አላገኘም። ይህ ጉዳይ በመንግሥት በኩል እልባት አለማግኘቱ፣ በቂ የሆነ ምርመራም አለመካሄዱ ለእኛ ለጥናታችን መነሻ ሆኖናል።

ሌላኛው በግልጽ እንደሚታወቀው ከማዕከላዊ መንግሥት ጋር እሰጥ አገባ ውስጥ የገባው ሕወሓት ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም በሰሜን እዝ ላይ በሚያሳዝን ሁኔታ በድንገት ጥቃት ሲፈፅም በስድስተኛው ቀን ማይካድራ ላይ 1644 የአማራ ተወላጆችን ጨፍጭፏል። ይህ በአንድ ቀን ብቻ የተደረገ፣ በተጠና፣ በተደራጀ፣ ስልታዊ በሆነ፣ መዋቅር በተዘረጋለት መልኩ የተሠራ የዘር ማጥፋት ሂደት ነው።

እነዚህ ነገሮች ሁሉ አካባቢው ላይ ሰፊ ጥናት እንድታጠና ያስገድዳሉ። ምክንያቱም ይህ የሰብአዊነት ጉዳይ ነው፤ የሰላም ጉዳይ ነው፤ የፍትህ ጉዳይ ነው፤ ስለዚህ ዩኒቨርሲቲው በነዚህ ጉዳዮች ላይ ጥናት በማጥናት የድርሻውን እንዲወጣ ያስገድደዋል ማለት ነው።

እንዲያውም ወደጥናቱ ገብተን ካየን በኋላ በጣም የዘገየ ጥናት እንደሆነ ነው የተረዳሁት። ይህ ጥናት መጠናት የነበረበት አሁን አልነበረም። ዩኒቨርሲቲዎችም፣ ሌሎች የጥናት ተቋማትም በዚህ ኃላፊነት ነበረባቸው። ምክንያቱም እዚያ አካባቢ ያለ ኅብረተሰብ ተሰዶ፣ ተገድሎ እና ታፍኖ እስከሚያልቅ፣ ማንነቱን እስከሚነጠቅ፣ ቋንቋ እስሚከለከል፣ ባህሉን፣ ወጉንና ልምዱን እንኳን መተግበር እንዳይችል እስከሚደረግ ድረስ መቆየት አልነበረበትም። የመንግሥትም ፍትህ ጭምር የዘገየ ይመስላል። እነዚህ ሁሉ የጥናታችን መነሻዎች ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- ከዚያ በኋላ ጥናቱ በምን መልክ ነው የተካሄደው?**

**አቶ ጌታ፡-** አንድ ጥናት ሲካሄድ ቅድመ ሁኔታዎች አሉት። የመጀመሪያው ለጥናት ቅድመ ሁኔታዎች የሆኑ መነሻዎች አሉ ወይ የሚል ነው። ለዚህ መልሱ አዎ የሚል ነው። ሁለተኛው ለዚያ ጥናት የሚሆን ንድፈሃሳብ ይዘጋጃል። ጎንደር ዩኒቨርሲቲም 21 የሚሆኑ የጥናት ቡድን አባላትን አዋቅሮ ዝርዝር ንድፈሃሳብ እንዲዘጋጅ አድርጓል። ምን ዓይነት ስልት መከተል እንዳለበት፤ የጥናቱ ወሰን፣ መቼ ተጀምሮ መቼ ማለቅ እንዳለበት፣ በጀት፣ ተሳታፊዎች እነማናቸው የሚሉ ሃሳቦችን የያዘ ሰነድ ከተዘጋጀ በኋላ መነሻ ሃሳብ ተገመገመ። የጥናት ስነምግባር ደንብ ቦርድም መነሻ ሃሳቡን ገምግሞ አፅድቆታል፤ገለልተኛ የሆኑ በቦርድ የተቋቋሙ ባለሙያዎች ይህንን ከገመገሙ በኋላ ሳይንሳዊ መሆኑን፣ የፖለቲካ ወገንተኝት የሌለው ስለመሆኑ ተገቢ የሆነ ጥናት ነው ተብሎ ከፀደቀ በኋላ ነው በጀት የተለቀቀለት።

ንድፈሃሳቡ ከፀደቀ በኋላ አካባቢውን የመቃኘት ሥራ ነው ቡድኑ የሠራው። ምክንያቱም የጥናቱ አላማ የተደበቀውን ጉዳይ ነው ማውጣት ያለበት። ስለዚህ ዝም ተብሎ ዘው ተብሎ የሚገባበት እና የሚወጣበት አይደለም። ትልልቅ ሰዎችን ቃለመጠይቅ አደረግን፣ የመንግሥት ተቋማትን አየን፣ ሰነዶችን አገላበጥን፣በዚህ ሂደት ውስጥም የጥናት ስልታችንን በዝርዝር አስቀመጥን።

ጥናታችን ሁሉንም ዓይነት ስልቶች ያካተተ ነው። ምክንያቱም ጥናት ስታጠና እውነታውን ማግኘት አለብህ። ይህ እዚህ አካባቢ የተፈፀመው ወንጀልም ሆነ ጥፋት ውስብስብ ያለ ሂደትን የተከተለ ነው። አንደኛ ጥፋቱ መንግሥት መር ነው። ሁለተኛ ስልታዊ ነው። ሦስተኛ የተቀናጀ ነው። በርካታ አካላት እጃቸው አለበት። አራተኛ በተቻለ መጠን መረጃዎች እንዳይገኙ ለማድረግ ከፍተኛ ሥራ ተሠርቷል። ስለዚህ ይህ ከሆነ ምንድነው ማድረግ ያለብን በሚል የጥናት ስልታችን ሁሉን ዓይነት ዘዴዎችን እንድንከተል አስገድዶናል። ለምሳሌ አንደኛው የገጠርንም የከተማውንም ኅብረተሰብ ያካተተ አባወራዎችን ቃለመጠይቅ ማድረግ ነው። ታሪኩ፣ ባህሉ፣ ሕወሓት ከገባ በኋላ የነበረው የሕወሓት አስተዳደራዊ ሥርዓት ምን ይመስላል፤ የተፈፀሙ ወንጀሎችና በደሎች ነበሩ ወይ፣ አሁን ማኅበረሰቡ ምን ይፈልጋል፤ ምን ዓይነት ስነልቦና ነው ያለው፤ የሚለውን የሚዳስስ 912 አባወራዎችን የሚያካትት ቃለምልልስ ተደርጓል።

ሌላኛው መንገድ የመስክ ምልከታ ማድረግ ነው። የመስክ ምልከታችን ተቋማትን፣ ቤቶችን፣ በዓላትን፣ የሚያካትት ነው። ለምሳሌ በዓላት ላይ ምን ዓይነት ቋንቋዎችን ይናገራሉ? ምን ዓይነት ባህል ነው ያላቸው? ግንኙነታቸው ምንድነው የሚመስለው? ስነልቦናቸው ምንድነው? የሚመስለው የሚለውን ባካተተ መልኩ የወንጀል አሻራዎችን ተከትለን በማነፍነፍ ምልከታ አካሂደናል።

በሌላ በኩል የቡድን ውይይት ተካሂዷል። የአገር ሽማግሌዎች፣ ታሪክ አዋቂዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች፣ አቤቱታ ሲያቀርቡ የነበሩ ወዘተ፣ ከሙያ ዘርፍም ከሁሉም ሙያ ከሕክምና፣ ከትምህርት፣ ከምጣኔ ሀብት ወዘተ የተካተቱበት ነው።

ሌላኛው ጥልቅ ቃለመጠይቅ ነው። በዚህም አንድ ሰው ያለምንም ገደብ ሃሳቡን በዝርዝር የሚገልጽበት ነው። ከዚህ በተጨማሪ እያንዳንዱ ፎቶ፣ ቃለመጠይቅ እና ውይይት ሲደረግ ሙሉ ፈቃደኝነታቸው ተጠይቆና

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

ፈቃደኛ ሲሆኑ ብቻ ነው የጥናቱ አካል የሆኑት። የጥናቱ ተሳታፊዎች በራሳቸው ሙሉ ፈቃድ፣ በራሳቸው ነፃነት ተሰምቷቸው ነው። ፈቃደኛ ካልሆኑ አካላት መረጃ አልሰበሰብንም። ጥልቅ ቃለመጠይቅ ታሪክ አዋቂዎችን፣ ሽማግሌዎችን በወቅቱ በስፍራው የነበሩ ሰዎችን ጭምር ያካተተ ነው።

ሌላኛው የሰነድ ማስረጃ ነው። ምንም እንኳ ጥናቱ ስልታዊ ሆኖ ብዙ ሰነዶች ቢጠፉም ወንጀል ሠርቶ ማምለጥ አይቻልምና በርካታ ሰነዶችን ማሰባሰብ ችለናል። እነዚህ አሁንም በመጽሐፍ መልክ የሚወጡ ጭምር ናቸው። ቦታውን ሲወሩ ከመንግሥት ተቋማት ሲፃፉ የነበሩ ደብዳቤዎች፣ የወልቃይት፣ ጠገዴና ጠለምት ሕዝብ እንዴት እንደተቀበላቸው፤ ሰዎችን አፍነው ለመውሰድና አማርኛ ቋንቋ እንዳይናገሩ፣ ባህላቸውን እንዳይለማመዱ ለማድረግ ሲሠሩ የነበሩ ተግባራትን በተመለከተ በርካታ ሰነዶችን አግኝተናል። ከተቋማት፤ ከግለሰቦች፣ ከታሪክም ጭምር ማለት ነው።

ሌላኛው ደግሞ ፍንጭን ተከትሎ የመሄድ ስልት / Snow ball technique/ ነው። ይህ ዘዴ አንድ ሰው የሆነ ፍንጭ ሲናገር እሱን በመያዝ ወደሚቀጥለው መሄድና እሱን ተከለትሎ በመሄድ እስከመጨረሻው ምንጩጋ እስከሚደረስ ድረስ የመጓዝ ዘዴ ነው። በዚህ ስልት በተለይ አብዛኞቹን የዘር ፍጅት የተካሄደባቸውን ቦታዎች ለማግኘት በጣም ምስጢራዊ፣ ድብቅ፣ መሬት ውስጥ የተቀበሩ እና ሰው የማይደርስባቸው አካባቢዎች ስለነበሩ፣ ይህንን ስልት ነው የተከተልነው።

በዚህ ሂደት እዚያ አካባቢ ለረጅም ጊዜ ጥያቄ ሲያነሱ የነበሩ ሰዎችን ተጠቅመናል። እያንዳንዷ መረጃ አባወራው ድረስ በመሄድ ዋሻ ውስጥ በመሄድ፤ የተቀበሩትን የጅምላ መቃብሮች፣ አፈላልጎ ማግኘት፣ ሰዎች ወንዝ ውስጥ ሲከተቱ የነበሩ ሰዎችን፣ ለዚህ ምስክር የሚሆኑ ሰዎችን ጭምር በማምጣት እነዚህን ሰዎች በመጠቀም ነው የጅምላ መቃብሮችን ማግኘት የቻልነው።

**አዲስ ዘመን፡- በመጨረሻ ግኝታችሁ ምን ነበር?**


**አቶ ጌታ፡-** የእኛ ጥናት ታሪክን ያጠናል፤ የወልቃይት ጠገዴና ጠለምት ሕዝብ ታሪኩ፤ ባህሉ፤ ልማዱ ወዘተ የሚለውን ያጠናል። ከዚህ ጋር ተያይዞ የደረሰ የታሪክ፣ የባህልና የቋንቋ ቅየራ መኖሩን አረጋግጠናል። ለውጡንም ጭምር እያነፃፀርን ለማሳየት ሞክረናል። ይህ በዝርዝር በመጽሐፍ መልክ ይወጣል።

ሌላኛው የደረሰ የዘር ማጥፋት ወንጀል አለ። ከላይ እንደተገለፀው 29 ከመቶ የሚሆነው እዚያ አካባቢ ያለው ማኅበረሰብ ሕይወቱ እንዳለፈ አረጋግጠናል። ይህ ሕወሓት ባመጣው ጦስ የደረሰ ነው። ሁለተኛው 26.5 ከመቶ የሚሆኑ ሰዎች አድራሻቸውን እንዲለቁና እንዲበተኑ ተደርጓል። በዚህ የተነሳ የወልቃይት ሕዝብ በሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች እና በበርካታ የውጭ አገራት ተበትኖ ይገኛል። ሱዳን፣ ኤርትራ፣ እስራኤል፣ አውሮፓ ወዘተ ተበታትነው ነው ያሉት። እኛ ጥናቱን ካካሄድን በኋላ እነዚህ ሰዎች የት እንደተበተኑ ጭምር ሙሉ መረጃ አሰባስበናል። የት አገር እንደሄዱ፣ መቼ እንደሄዱ ወዘተ ማለት ነው።

ሦስተኛው ታፍነው የሚጠፉ ሰዎች ናቸው። በተለይ ታሪክ አዋቂ፣ ማኅበረሰቡን ያነቃሉ፤ መንግሥትን ይሞግታሉ፤ የሚባሉ ሰዎች ልቅም ተደርገው በጭለማና በብርሃንም ጭምር ታፍነው ተወስደዋል። የሚያሳዝነው እነዚህን ሰዎች ቤተሰቦቻቸው የት ሄደው ነው ብለው ሲጠይቋቸው እንኳ እንዲናገሩ አይፈቀድላቸውም። ስልጠና ወስደናቸዋል ጭምር የሚል ምላሽ ይሰጧቸዋል። እንግዲህ ሃያና ሰላሳ ዓመት የሆናቸው አሉ፤ እነዚህ ሰዎች የት እንደደረሱ እንኳን ማወቅ አይቻልም። ማኅበረሰቡ አንድ ሰው ለምሳሌ ሚስት ባሏ ታፍኖ ሲሄድ የት ሊሄድ ነው ብላ መጠየቅ አትችልም። ይህንን ያህል የስነልቦና ጫና እንዲደረግበት ተደርጓል ማኅበረሰቡ። በዚህ አማካኝነት ሰዎችን ማፈናቀል፤ መግደል አፍኖ መውሰድ ናቸው በዋናነት ከሰብአዊነት አኳያ የተፈፀሙት። ከሕክምና፣ ከግብርና፣ ከኢኮኖሚና ከትምህርት አንጻር የሚያሳዝን ግፍ ነው የተፈፀመው። በነዚህ ውስጥም አንኳር የሆነው ጅምላ ጭፍጨፋ ነው።

በዚህ ሂደት ውስጥ 12 የጅምላ መቃብር ቀጣናዎች ተገኝተዋል። ማይካድራን ጨምሮ በጣም በርካታ ሰዎች የተፈጁበት ቀጣናዎች ተገኝተዋል ማለት ነው። ከነዚህ ውስጥ ስምንቱ የተረጋገጡ ናቸው። ሌሎች 12 የሚሆኑ ተጠርጣሪ ቦታዎችም አሉ።

ማይካድራ ላይ ሲኬድ ስምንት ዋና ዋና የጅምላ



መቃብሮች አሉ፤ የሟች ቁጥር 1563 ነው። 81ዱ ደግሞ በሕክምና ጥረት ሕይወታቸው የተረፈ ነው። ለምስክርነት የበቁትም እነሱ ናቸው። ስለዚህ ይህንን ያህል ሰፊ ጅምላ ጭፍጨፋ መካሄዱን ለማረጋገጥ ተችሏል።

እነዚህን ማነው ያደረገው፣ መቼ የሚለውን በተመለከተ ያላለቀ ሥራ አለ። የካርቦን እና የፎረንሲክ ምርመራዎች ይቀራሉ። ዘመናዊ የላቦራቶሪ ምርመራዎችን ለማካሄድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሥራት ላይ እንገኛለን። ነገር ግን መረጃዎቹ ካለው ሰነድ ተነስተን ግልጽ ነው። ጅምላ ጭፍጨፋውን ሕወሓት ስለማካሄዱ ግልጽ ነው። ጭፍጨፋውም በጎንደር አካባቢ ባሉ የወልቃይት ጠገዴና ጠለምት አማራዎች ላይ ስለመፈፀሙ፣ ከበቂ በላይ ማስረጃዎች አሉ።

እንደሚታወቀው ሕወሓት ሲመጣ አማራ ጠላቴ ነው ብሎ በወረራ ነው የጀመረው። ስለዚህ ከ1972 ዓ.ም ጀምሮ የመንግሥት ስልጣን እስከያዘበት ጊዜ ድረስ ይህን አካባቢ ሲቆጣጠር የነበረው ሕወሓት ነው። ሁለተኛ እዚህ አካባቢ ያለው ማኅበረሰብ ሲሰደድ፣ ሲገደል፣ ሲታፈን እንደኖረ በጣም በርካታ ዜጎች ሰሚ አጥተው በታፈነ ሁኔታ ውስጥ እንደነበሩ በርካታ ማኅበሰረብ አባላት ሲጮሁ ነው የቆዩት። ሦስተኛ ከዚህ በፊት የነበሩት የነኢሰመጉም፣ የነሞረሽ ወገኔም፣ የነልሳነ ግፉአን፣ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን፣ በቅርቡ ደግሞ የማይካድራን ጨምሮ ሕወሓት በግልጽ እዚያ አካባቢ ያሉ አማራዎችን ሲጨፈጭፍ መኖሩን ያሳያል።

ሌላው ደግሞ ማይካድራ ላይ የፈፀመው የአደባባይ ወንጀል ይህንን አይፈፅምም ብለህ እንድትነሳ አያደርግህም። መታወቂያቸውን፣ ሲም ካርዳቸውን፣ ስልክ ቁጥራቸው ለይቶ አማራ የሆኑ ግለሰቦች ላይ ነው ግፉን የፈፀመው።

ሌላው የሕወሓት ከፍተኛ ባለስልጣናት ብዙ ጊዜ ይህንን በአደባባይ ይናገሩት ነበር። ለምሳሌ እነጄኔራል ሳሞራ የኑስ፤ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ፣ ሌሎችም ከፍተኛ አመራሮች በግልጽ ተናግረውታል። በአንድ ወቅት ሁመራ ላይ የወልቃይት ጠገዴና ጠለምት ማኅበሰረብ በጣም አቤቱታ ሲያበዛ የአካባቢውን ትላልቅ ሰዎች ሰብስበው ችግራችሁ ምንድነው ብለው አወያዩአቸው። እኛ መሬታችንን በሕወሓት ካድሬዎች ተነጥቀናል፤ እየሞትን ነው፤ እየተሰደድን ነው፤ ፍትህ እንፈልጋለን፤ ወረራ ተካሂዶብናል፤ ስለዚህ ወደአማራ ክልል እንካለል የሚል ጥያቄ ሲያነሱ አቶ መለስ ዜናዊ በአደባባይ እኛ ወደወልቃይት፣ ጠገዴና ጠለምት ጨፌ ተጎዝጉዞልን አልመጣንም፤ የመጣነው ደም አፍሰን፣ አጥንት ከስክሰን ነው፤ ከ20 ሺህ በላይ የትግራይ ሰራዊትን መስዋዕት ከፍለን ነው። መሬት ለተወለደበት አትሆንም። ለጉልበተኞች ነው የምትሆነው። ስለዚህ አካባቢውን በጉልበት ይዘነዋል፤ እናንተም ጉልበት ካላችሁ በጉልበት ሞክሩት፤ በሌላ መልኩ ብትሞክሩት ግን አይሳካላችሁም የሚል ምላሽ እንደሰጧቸው የአካባቢው ሽማግሌዎች ምስክርነታቸውን ሰጥተውናል። እነ ጄኔራል ሳሞራ የኑስም አማራን አከርካሪውን ሰብረነዋል ብለው በአደባባይ ተናግረዋል። እነዚህ ከራሳቸው የመጣ ምስክርነት ነው።

ሌላው ይህ አካባቢ የተገኘው ጅምላ መቃብር ዛፍ የበቀለበት፤ ፍርስራሽ የወደቀበት፤ እንደሆነ በመስክ ምልከታ ወቅት የታየ ነው። ደጀና፣ ገሃነምና ምንምኔ አካባቢ ያሉት የ20 እና የ30 አመት ፍርስራሾች ስለመሆናቸው በግልጽ ይታወቃል። ይህ አካባቢ የሕወሓት ካምፕ እንደነበርም በግልጽ ይታወቃል። ስለዚህ ወንጀሉን ማን እንደፈፀመው ግልጽ ነው ማለት ነው።

ከዚህም ባሻገር የሟች ቤተሰቦች ከሕወሓት ካድሬዎች ማን እንደገደላቸው ጭምር በግልጽ የተናገሩበት ሁኔታ ነው ያለው። አባቴን የገደለው እከሌ ነው፤ በዚህ ቀን፣ በዚህ ሰዓት፣ በዚህ ቦታ ብለው በግልጽ ይናገራሉ። ያም ሆኖ ግን ጅምላ ጭፍጨፋ ዓለም አቀፍ ወንጀል ስለሆነና ጉዳዩን በዚያ ልክ ከፍ አድርጎ መደምደሚያ ለመስጠት የላቦራቶሪ ምርመራዎቹን ማካሄድ አስፈላጊ ሆኗል።

በግድያው ወቅት ብዙ ዓይነት ስልት ነበር የሚከተሉት። አንዳንዴ አደባባይ ላይ ረሽነው አስከሬንን አደባባይ ላይ ያሰጡ ነበር። ገበያ ላይ ጥለው እንዳይለቀስ ያደርጉም ነበር። ይህ የሰዎችን ስነልቦና ለመጉዳት ነው። ሌላው ደግሞ ገድሎ ገደል ውስጥ መክተት ነው።

አብዛኛው የፈፀሙት ግን እንደነ ገሃነም ዓይነት በመሬት ውስጥ ከተዘጋጁ እስር ቤቶች በምሽት እያወጡ በየቀኑ የሚረሽኑበት ሁኔታ ነበር። ይህን እዚያ እስር ቤት የነበሩና በተዓምር የተረፉ ናቸው የገለፁልን። የአካባቢው ማኅበረሰብም ይህ የዕለት ተዕለት ተግባር እንደነበር ይናገራል። ሌሊት አውጥተው ጉድጓድ ራሳቸውን አስቆፍረው በአውቶማቲክ መሣሪያ በጅምላ የረሸኗቸው ሰዎችም አሉ።

አብዛኞቹን ደግሞ ወንዝ ዳር ነበር የሚቀብሩት። ለምሳሌ ተከዜ ተፋሰስ አካባቢ፣ አድኖ የሚባል ጅምላ መቃብር፣ ገሃነም አካባቢም በቃሌና ወንዝ ተፋሰስ ከወንዙ አምስትና አስር ሜትር ርቀት ላይ ይቀብሯቸው ነበር። ምክንያቱም በክረምት ወንዝ ሲሞላ አስከሬኑን ይዞ እንዲሄድ ለማድረግ ነው።

ወንዝ ዳር ካልሆነ ደግሞ ሰዎችን ገድለው ከቀበሩ በኋላ መሬቱን ልክ እንደ አውድማ ይደመድሙትና ደብዛው እንዳይገኝ ያደርጉ ነበር። ድንጋይ የለውም፣ ምልክት የለውም፣ አንዳንድ ቦታ ደግሞ እንዲታረስም ይደረጋል። በሌላም በኩል አየር ማረፊያዎችን፣ ሆስፒታሎችንና ጤና ጣቢያዎችን ጭምር የመግደያ ቦታ አድርገው ነበር። ይህ የጤና ባለሙያዎች ጭምር ምስክርነት የሰጡበት ነው። ስለዚህ ጥናታችን ይህንን ያካተተ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከነዚህ ጅምላ ጭፍጨፋዎችና ማሳደዶች በስተጀርባ ያለው ፍላጎት ምን ነበር?**

**አቶ ጌታ፡-** ሕወሓት በዚህ አካባቢ በዚህ ልክ የሞት ቀጣና እንዲሆን ካደረገባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ከመልክዓምድር አንጻር ቁልፍ ቦታ መሆኑ ነው። አካባቢው የእርሻ መሬት ነው። ሰሊጥ፣ ማሽላ፣ ጥጥ፣ የሚመረትበት አካባቢ ነው። የቀንድ ከብት በብዛት የሚረባበት ነው። ወደሱዳንና ኤርትራም ጭምር ኮሪደር የሚሆን ነው። ሕወሓት ካድሬውን ወደ ወልቃይት፣ ጠገዴና ጠለምት እንዲመጣ እዚያ አካባቢ ያሉ ገበሬዎችን ገድሎ እና እንዲሰደዱ አድርጎ መሬታቸውን በሙሉ ቀምቷል። በዚህ የተነሳ የሕወሓት ካድሬዎች በጣም ሰፋፊ የእርሻ መሬቶችን በዚያ አካባቢ ይዘዋል። ተወላጁ መሬቱን ተነጥቆ አካባቢው የሕወሓት ካድሬዎች ንብረት እንዲሆን ተደርጓል። በዚህም ለረጅም ጊዜ ሰሊጥ፣ ማሽላና ጥጥ ሲያመርቱበት እንደነበር አይተናል።

በዚያ አካባቢ የወልቃይት ተወላጅ የሆነ የሥራ ዕድል የሚያገኝበት ዕድል ጠባብ ነበር። የወልቃይት የሥራ ማስታወቂያ እንኳን የሚለጠፈው ሽሬና መቀሌ ላይ ነበር። ስለዚህ ዕድሉን የሚያገኙት ሽሬና መቀሌ አካባቢ ያሉ የሕወሓት ደጋፊዎችና ካድሬዎች ናቸው።

በሌላም በኩል በየትኛውም መንገድ በዚያ አካባቢ ያለ የንግድ እንቅስቃሴ እንዲዳከም ነው የተደረገው። ኢኮኖሚው ባዶ እንዲሆን ተደርጓል። ከብቶቻቸውን ጭምር ለመዝረፍ ሰበብ ነበር የሚፈለግባቸው። ለምሳሌ የወልቃይት ከብት ሄዶ እነሱ ከወልቃይት የነጠቁትን መሬት ከረገጠ ለአንድ የቁም ከብት እስከ 1600 ብር እንዲከፍል ያደርጉ ነበር። እዚያ አካባቢ በርካታ የሕወሓት ሰዎች ሰፋፊ እርሻ እያላቸውና ኢንቨስትመንት ውስጥ ገብተው ሳለ ግብር አይከፍሉም ነበር። እስካሁን ድረስ ሳይመለሱ የቀሩ በርካታ የባንክ ብድሮችንም ይወስዱ ነበር።

የአካባቢው ተወላጅ ግን ከአቅሙ በላይ ግብር እንዲከፍል በማድረግ ንግዱን እንዲተው ተደርጓል። ትንሽ ምግብ ቤት እንኳን መክፈት የማይችሉበት ሁኔታ ነበር። ስለዚህ ወደ ሥራ መግባት አይችሉም፤ ንግድ ላይ መሰማራት አይችሉም፤ እርሻውን ተነጥቀዋል፤ተምረው እንኳ ሥራ እንዳይዙ ተደርገዋል።

የወልቃይት ተወላጅ የሆነ ሰው ትምህርቱን እንኳን በአግባቡ እንዳይከታተል ይደረግ ነበር። ሴቶችንም አስገድደው ይደፍሩ ነበር። በዚህ የተነሳ ያለዕድሜ ማርገዝና ከትምህርት ማቋረጥና የመሳሰሉ ችግሮች በርካታ ነበሩ። በዚህ የተነሳ በርካታ የወልቃይት ልጆች በተለያዩ የጎረቤትና የአገር ውስጥ አካባቢዎች ተሰደው ነበር። ለምሳሌ በጎንደር ወልቃይት የሚባል ሰፈር አለ።

ከዚህም ባሻገር ከባህል አንጻር የሚሠራው ሴራ ከፍተኛ ነበር። ለምሳሌ መቀሌ አማርኛ እንደልብ ይነገራል። ወልቃይት ላይ ግን አማርኛ መናገር አይቻልም ነበር። ወልቃይት ላይ ምግብ ቤት ላይ በአማርኛ ስም መፃፍ አይቻልም። ብዙ ዋጋ ያስከፍላል።

ወልቃይት ላይ የስፖርት ክለብ ሳይቀር በአማርኛ የተፃፈበት ልብስ መልበስ አይቻልም ነበር። የነፋሲል ከነማን ቲሸርት በአማርኛ ተጽፎበታል ተብሎ እንዳይለብሱ ነው የተደረገው። አዲ ረመጥ ላይ አንድ ትልቅ ሰው ምግብ ቤት ከፍተው በአማርኛ ስም በመጻፋቸው ምግብ ቤቱ እንዲዘጋ ተደርጓል። ግፉ በዚህ ልክ ነው የነበረው።

ከባህልም አንጻር የአካባቢው ሕዝብ በኀዘኑም ሆነ በደስታው ጊዜ የጎንደር አማርኛን ነው የሚጠቀመው። ከሚዲያም አንጻር ላለፉት የሕወሓት ዘመን እኮ ስለወልቃይት ጠገዴና ጠለምት መናገር ወንጀል ነው የነበረው። ጋዜጠኞችንም በዚህ ዙሪያ ስናናግር የወልቃይት ጉዳይ ቀይ መስመር ነው ብለው በግልጽ ነግረውናል።

ማንኛውም ሚዲያ እንዳይዘግበው ነው የተደረገው። ስለዚህ ይህ ስልታዊ፣ የተደራጀ፣ መንግሥት መር የሆነና በማኒፌስቶ የተደገፈ፣ በማንነት ላይ የተፈፀመ ወንጀል ነው። ይህን ወንጀል መንግሥትም ሆነ ሌላው አካል በአደባባይ አውጥቶ ወንጀሉን የሠራውን አካል መጠየቅ፣ ወደፊት ደግሞ ትምህርት እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል።

ከዚህ በኋላ ጉዳዩን መንግሥትም፤ ሰብአዊ መብት ላይ የሚሠሩ አካላትም በባለቤትነት የሚይዙት፣ የፍትህ ተቋማት በሰፊው የሚሠሩበት፣ ፌዴራል ፖሊስና ሌሎች የምርመራ ተቋማትም በዘርፉ ልምድ ያላቸው ሌሎች ተቋማትና ዩኒቨርሲቲዎች እንዲሁም ምሁራን ሊሳተፉበት ይገባል። ጉዳዩን ከፖለቲካ ወገንተኝነት ውጪ ማንኛውም አካል በሰብአዊነት ሊሠራው ይገባል። የዓለም አቀፍ ተቋማትና የሌሎች አገራት ዩኒቨርሲቲዎች ፕሮፌሰሮችን ጭምር ለማሳተፍ እየሠራን ነው። ስለዚህ ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ ይገባል። እኛም ወደፊት የጥናቱን ግኝት በዓለም አቀፍ ጆርናሎች ላይ በተለያዩ ቋንቋዎች በማሳተም በዓለም አቀፍ ደረጃ ተደራሽ ለማድረግ እየሠራን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ማብራሪያ በዝግጅት ክፍሉ ስም አመሰግናለሁ።**

**አቶ ጌታ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## ከሥራ ፈጣሪነት ኢንቨስተር እስከ መሆን ህልም ያላቸውን ወጣቶች ያሰባሰበ ማእከል

**አሥመረት ብሥራት**

ወጣት ሜሮን ተስፋዬ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ህንፃ ኮሌጅ በአርክቴክት የትምህርት መስክ የመጀመሪያ ዲግሪያዋን ከያዘች በኋላ እንደማንኛውም ተመራቂ ተማሪ ስራ ፍለጋ መዞር አላሻትም ። የተማረችበት የትምህርት መስክ (አርክቴክቸር) ከዲዛይን ጋር በጣም የተገናኘ ነበር። በዩኒቨርሲቲ ቆይታዋ የሚማሩበትን ደብተር በራሳቸው እንዲሰሩ መምህራኖቻቸው ያበረታቷቸው ስለነበር መፍጠር የሆነ ነገር መስራት የሚል እሳቤ ልቧን ሞልቶት ምን መስራት እንደምትችል እያሰላሰለች ሳለ ነበር በማህበራዊ መገናኛ ብዙሃን ወጣቶች አንድ ላይ በመሆን ያላቸውን ሃሳብ የሚያሳድጉበት፤ ሃሳቡንም ወደ መሬት አውርደው እንዲጠቀሙ የሚያስችል‹‹ ክሬኤቲቭ ሀብ ››የተባለ ማእከል መኖሩን የሰማችው።

በተለያየ ዘርፍ የተወሰነ ቁጥር ያላቸውን ወጣቶች መወዳደር እንደሚችሉ ስትሰማ በቆዳ ዘርፍ ተወዳድራ ወደዚህ ተቋም ገባች፤ በዚህም የቆዳ ውጤቶችን ማምረት፤ ቆዳን ከእንጨት ጋር፤ ቆዳን ከጨርቅ ጋር በማዋሃድ ለአይን የሚማርኩ ቦርሳዎችን በማምረት በዛው በክሬኤቲቭ ሀብ ውስጥ ባለ የማሳያ ቦታ በማሳየት እና በመሸጥ ኑሮዋን እየገፋች ትገኛለች። ከቦርሳዎቹ ባሻገር በቆዳ የተለበጡ የተለያዩ ማስታወሻ ደብተሮችን ፣የሰአት ማሰሪያዎችን ትሰራለች። የፈጠራ ስራዎች ሃሳብ በውስጧ ሲመጡ ዲዛይን አድርጋ ከመስራቷም በላይ ሰዎች ትእዛዝ ሲሰጧት በትእዛዙ መሰረት ሰርታ እንደምታስረክብ ትናገራለች።

አሁን በመኖሪያ ቤቷና በክሬኤቲቭ ሀብ ውስጥ ስራዎቿን እየሰራች መሆኑን የምትናገረው ይች ወጣት ዛሬ ላይ ሀሳብ ብላ የያዘቻቸውን ነገሮች ወደ ፈጠራ ስራ አሳድጋለች። በቀጣይ ደግሞ ሀገሯን በቆዳው ዘርፍ እሴት ጨመራ በመስራት ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ማቀዷን ትናገራለች። በጣም ብዙ ወጣቶች ልባቸው ውስጥ ብዙ የፈጠራ ሃሳቦች አላቸው። ይሄንን አውጥተው ግባቸውን እስኪመቱ ድረስ የሚያግዝ ድጋፍ ቢደረግላቸው መልካም ነው ስትል ትመክራለች።

አሁን የምታመርታቸው አነስተኛ ቦርሳ እስከ አንድ ሺህ ብር ድረስ የሚሸጥ ሲሆን ከፍ ያለ ቦርሳ ደግሞ እስከ ሶስት ሺህ ድረስ ዋጋ ተቆርጦላቸው ለገበያ ታቀርባለች። እሷና እሷን መሰል ሃሳብ ያላቸው ወጣቶችን ከፍ ለማድረግ ሃሳብን ወደ ገንዘብ የሚቀየርበት ጊዜና ምቹ ቦታ ያስፈልጋል ትላለች።

ሌላዋ ወጣት ናታኒየም ወንድወሰን ትባላለች። ፋሽን ዲዛይነር ስትሆን ‹‹ናታኒየም ኩቱር›› በሚባል መጠሪያ ለተለያየ ሰው ሊሆኑ የሚችሉ ልብሶችን በማዘጋጀት ትታወቃለች። ይች ወጣት የመጀመሪያ ዲግሪዋን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሶፍትዌር ኢንጂነሪንግ ብትጨርስም ልቧ ግን ለፋሽን ያደላ ነበርና፤ ይህን ውስጣዊ ፍላጎቷን ለማሳካት ከተማረችው ትምህርት በተጨማሪ በቢዝነስ ማኔጅመንት ተጨማሪ ዲግሪ ይዛለች።

ወጣቷ በኮምፒውተርና በቢዝነስ ማኔጅመንት የመጀመሪያ ዲግሪዋን ካገኘች በኋላ ከመክሊቷ ጋር የሚያገናኛትን የፋሽንና ዲዛይን ክህሎት በአጭር ስልጠና አካብታ ወደ ስራ በምትገባበት ወቅት ነበር በዓለማችን ላይ የኮሮና ወረርሽኝ የተከሰተው።

ወቅቱ ማክስና ሌሎች ለበሽታው መከላከያነት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች እጥረት የነበረበት ስለነበር ፈጠን ብላ አስከፊውን ወረርሽኝ እንደ መልካም አጋጣሚ በመቀየር ማስኮችን አዘጋጅታ በኦንላይን ገበያ መሸጥ ጀመረች። ያ የኢኮኖሚ አቅሟን ለማሳደግ ያስቻላት ሲሆን ከዚህ በኋላ ለተለያዩ ዝግጅቶች የሚሆኑ ልብሶችን የማዘጋጀት ስራ ላይ ተሰማራች። ትእዛዞችን እየተቀበለች የፋሽን አልበሳትን ለወፍራሞችም ሆነ ለቀጭኖች ሁሉንም አይነት የሰውነት ቅርፅ ያላቸው ሰዎች እንዲለብሷቸው በማድረግ ማዘጋጀት ጀመረች።

ልብሶቿን የእናቷ ሱቅ ጀርባ ባለ ክፍት ቦታ ላይ ሆና በመስራት ክህሎቷን የምታሳድግበት መንገድ ስትፈልግ በምስራቅ አፍሪካ የመጀመሪያው የሆነ ፈጣሪ ወጣቶች አንድ ላይ በመሆን ያላቸውን ሃሳብ የሚያሳድጉበት፤ ሃሳቡንም ወደ መሬት አውርደው እንዲጠቀሙ የሚያስችል ክሬኤቲቭ ሀብ የተባለ ማእከል መኖሩን ሰማች።



ወጣት ሜሮን ተስፋዬ



ወጣት ናታኔም ወንደወሰን

ክሬኤቲቭ ሀቡ በቀድሞ በፌዴራል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ማስፋፊያ ባለስልጣንና በዩናይትድ ኔሺን ኢንዱስትሪ ዴቨሎፕመንት ኦርጋናይዜሽን ትብብር የተመሰረተ ሲሆን ለስራ ማስኬጃ የሚሆነውንም ገንዘብ የሚያገኘው ከጣሊያን ኤጀንሲ ፎር ዴቨሎፕመንት ኮርፖሬሽን ከተባለ ለጋሽ ድርጅት መሆኑን የማእከሉ ኃላፊ ነግረውናል።

በማአከሉ ለመገልገል የሚችሉ ወጣቶች ያላቸውን የስራ ሃሳብ እና ተጨባጭነቱን በደንብ ማሳየት ሲችሉ እንደነበር የምትናገረው ወጣት ናታኒየም፤ ከሷ የተሻሉ ሃሳቦች ሊኖሩ እንደሚችሉ ብታስበም የትኛውም የተከፈተ በር መዘጋት የለበትም የሚል እምነት ስለነበራት በእድሉ ተጠቃሚ ለመሆን ተወዳድራ ተሳክቶላታል። በማእከሉም የተለያዩ ክህሎቶችን ከማግኘቷም ባሻገር ናታኒየም ኩቱር የተባለውን የልብሶቿን ብራንድ ስም መስከረም 29 ቀን በማእከሉ በተደረገ ዝግጅት ለማስተዋወቅ ችላለች።

ወጣቷ የፋሽን ኢንዱስትሪው ውስጥ ተቀላቅላ ማህበረሰቡ በሀገር ውስጥ የተሰሩ ብራንድ የሆኑ ልብሶችን መልበስ እስኪችል ድረስ ጥረቷን የማታቆም መሆኑን ትናገራለች። በቀጣይም ሰፊ ፋብሪካ ከፍታ የበርካቶችን የስራ እድል ከመፍጠር በሻገር በታዋቂ ብራንድ አለምን የመድረስ ህልም ይዛ ትንቀሳቀሳለች።

እንደ ሜሮንና ናታኒየም ያሉ የክህሎት ባለቤት የሆኑ ወጣቶች በዚህ እድል ምን ያህል ተጠቀሙ ስንል የማእከሉን ስራ አስፈፃሚ አነጋግረናል። የክሬኤቲቭ ሀብ ማናጀር የሆኑት አቶ ተመስገን ፍሰሃ የአዲስ ነገር ፈጣሪዎች መገናኛ የሚል ትርጉም ይዞ የሚንቀሳቀሰው የስራ ፈጣሪዎች መሰብሰቢያ ከሰባ በላይ ለሆኑ ወጣቶች ክህሎት የማሳደግ ስራ እየሰራ መሆኑን አስረድተዋል። ማእከሉ የአዲስ ነገር ፈጣሪ የሆኑ በተለይም በዲዛይን ላይ የተሳተፉ ልጆች የሚሰሩበት ማለትም በፋሽን ዲዛይን፤ በሌዘር ማኑፋክቸሪንግ፤ በአይቲ፤ በምርት ማሳደግና በቴክስታይል የፈጠራ ዘርፎች ላይ የተሻሉ ሃሳቦች ያሏቸው ወጣቶች አንድ ላይ ተሰብስበው ሃሳባቸውን የሚያሳድጉበት ብሎም ወደ ተግባር የሚቀይሩበት፤ ያሏቸውን የክህሎት ክፍተቶች የሚሞሉበት ማእከል መሆኑን ይገልጻሉ።

በማእከሉ ወጣቶች በፈለጉት ልክ ተቀምጠው ፣አሰላስለው ሃሳባቸውን ወደ ውጤት የሚቀይሩበት ተቋም ነው። መግቢያው ላይ የሻይ ቡና አገልግሎት አለ። ይህም ወጣቶቹ ከተለያዩ ሰዎች ጋር በመገናኘት ውይይት የሚያደርጉበት ቦታ ሲሆን፤ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ወጣቶች ቁጭ ብለው የመጣላቸውን የፈጠራ ሃሳብ በያዙት ላፕቶፕ የሚያስቀምጡበት፤ በማእከሉ የሰው ሀይል አስተዳደር እና የህግ ባለሙያ ሰዎችን የሚያማክሩበት ክፍል ሲኖር፤ በቀጣይ የተለያዩ ስልጠናዎችና ፕሮግራሞች የሚካሄዱበት ቦታ አለ።

በጣም ዘመናዊ የሆኑ ዓለምአቀፍ ትምህርቶች፤ ስልጠናዎች፤ የተለያዩ ክህሎቶች ማለት የዲዛይን አስተሳሰቦችን መያዝ የሚችሉበት ስልጠና ይሰጣል የሚሉት አቶ ተመስገን ፤ ልጆቹ ከሃሳብ ባሻገር ውጤት ላይ ሰርቶ ማሳያ( ሳንፐል) ይሰራሉ፤ ከዛም ፈጠራቸውን ይዘው አብራቸው ከሚሰራ ኢንቨስተር ጋር እንዴት በጋራ መስራት እንደሚችሉ፤ የቢዝነስ ፕላን አፃፃፎችንና ሌሎች የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ያገኛሉ ብለዋል።

በኮምፒውተር ላይ ያሰቡትን ካስቀመጡ በኋላ በሶፍትዌር ተግብረው ሳምፕላቸው በስሪ ዲ ፕርንተር ይታተምላቸዋል፤ የዲዛይኖቻቸውንም ቅርፅ የሚያስይዙ የተለያዩ መቆራረጫዎች መኖሩን ተናግረው በተጨማሪም ዲጅታል ቤተሙከራ ውስጥ የተከፈለበት ንባብ ያነባሉ። የፈጠራ ናሙናቸውን ከሰሩ በኋላ በተለያዩ ኤግዚቢሽኖች እንዲተዋወቅላቸው ይደረጋል። መጨረሻው ማህበሩሰቡን የሚጠቅም ውጤታማ ስራ ለመስራት የሚቻል መሆኑን ነው የተናገሩት።

በዩናይትድኔሺን ኢንዱስትሪ ዴቨሎፕመንት ኦርጋናይዜሽን የእስቴከ ሆልደር አቶ መሳይ አማረ በበኩላቸው የፈጠራ ሀሳብ ያላቸው ወጣቶች ሲመረጡ የፈጠራ አቅም ያላቸው፣ የተለየ አበርክቶ ሊያደርጉ የሚችሉ በአምስቱም የፈጠራ ዘርፍ የመምረጫ መስፈርት ሲኖር ከሁሉም በላይ ሀሳባቸው መሬት ላይ መውረድ የሚችል ከሀሳብ የዘለለ ተጨባጭ ነገር ያለው ሊሆን የሚችል መሆኑ ታይቷል ። ይህ መስፈርት በማእከሉ ለስድስት ወር እንዲቆዩ የሚያደርጋቸው መሆኑን ተናግረው በቀጣይ ደግሞ ጠቀሜታው እየታየ ሊቀየር ይችላል ብለዋል።

በኦላይን በወጣ ማስታወቂያ 500 ወጣቶች የመዘገቡ ሲሆን የተሻለ የሆኑት 73 ወጣቶች ተመርጠው እየሰለጠኑ ይገኛሉ። አቅም ያላቸው በትንሽ ድጋፍ ተአመር ሊሰሩ የሚችሉ ወጣቶችን የሰበሰበው ይህ ማእከል ስራ ከጀመረ የወራት እድሜ ቢያስቆጥርም ስራ ፈጣሪዎቹ ግን በተገቢው መልኩ እየተገለገሉበት መሆኑን ለማየት ችለናል።

ዩናይትድ ኔሺን ኢንዱስትሪ ዴቨሎፕመንት ኦርጋናይዜሽን ናሽናል ክላስተር ዴቨሎፕመንት ኤክስፐርት አቶ ሰለሞን አሰፋ በበኩላቸው ፤ወጣቱ የክህሎት ሀሳቡን ወደ ውጤት የሚቀይርበት እና የፈጣሪነት ስነ ልቦና የሚያዳብርበት ተቋም መኖሩ እጅግ በጣም የሚያስደስት ነው። የተለያዩ ሀገር ኢንቬስተሮች ሀሳባቸውን ይዘው ወደ ሀገራችን በመምጣት በርካሽ የሰው ጉልበት፣ በራሳችን ጥሬ እቃ አምርተው ለእኛው መልሰው በውድ ዋጋ ይሸጡልናል። የፈጠራ ሀሳቡ፤ ጥሬ እቃው፣ ጉልበቱም ከኛ ከሆነ ለምን የውጪ ሰዎች ያስፈልጉናል። በራሳችን መስራትና ማደግ አለብን ። ለዚህ ደግሞ የማዕከሉ መኖር የፈጠራ ሰዎችን በማበረታታት፣ በመደገፍ የተሻለ የእድገት መንገድ የሚጠርግ ይሆናል።

በአጠቃላይ የፈጠራ ባለቤቶችን በአንድ ቦታ አድርጎ ውስጣቸው ያለውን ሀሳብ በአግባቡ እንዲያወጡ ብሎም ለሀገር ኢኮኖሚ ፋይዳ ያለው ነገር እንዲሰሩ ማድረግ የቻለ ማእከል መፈጠሩ፤ ከዚህም በሻገር ወጣትነትን ከፈጠራ ሀሳብ ጋር አቀናጅቶ ትኩሱን አቅማቸውን በማውጣት ከታች ተነስተው ትላልቅ ኢንቨስተሮች ለማፍራት የሚያስችል ተግባር እያከናወነ ይገኛል። ይህ ለትውልድ ራእይ ታላቅ ስንቅ የሰነቀ ተግባር ይደግ ይጎልብት እያልን በተቋሙ የነበረንን ቆይታ አጠናቀናል።

# የሕወሓቱ ጆሴፍ ጎብልስ

ታምራት ተስፋዬ

በዓለም የፖለቲካ ታሪክ የሚጠላትን አገር የመምራት እድል ያገኘ ብቸኛው ፓርቲ ሕወሓት ነው። በጎሰኝነት አስተሳሰብ፣በመጥበብ ፖለቲካ የተካኑት አሻባሪው ሕወሓት አባላትና ጋሻ ጃግሬዎቻቸው ኢትዮጵያን ለመጥቀም ከተጓዙባቸው ይልቅ ለማፍረስ የሄዱባቸው ጎዳናዎች ረጅምና አሰልቺ መሆናቸው የማይካድ ሃቅ ነው።

የቡድኑ አመራሮችና ደጋፊዎችም፣የማእከላዊ መንግስቱን ስልጣን በተቆጣጠሩበት ሃያ ሰባት አመታት ውስጥ አረመኔና ጨካኝ መሆናቸው በሚያስመሰክር መልኩ ለማየት የመስማትም ሆነ ለመንገር የሚዘገንኑ ኢ- ሰብአዊ ድርጊቶችን ፈፅመዋል።

በተለይ በዘመድ አዝማድ በመቧደን በዘር በመመዳደብ፣ በሚያስገርም፣ በሚያስደነግጥና በሚያስተዛዝብ መልኩ ኢትዮጵያን መዝብረዋል። እንደመዥገር ተለጥፈው የኢትዮጵያን ደም በመምጠጥ በሃብት ላይ ሃብት አግበስብሰዋል። ከሃያ ዓመታት በፊት ያልነበራቸው ሃብት አካብተዋል።

አባላቱ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሃብት ከዘረፉባቸው በርካታ መንገዶች አንዱ እርዳታ ቀዳሚ ነው። እ ርዳታ ለአሸባሪው ሕወሓት መክበሪያው ነው። ወያኔ ከበረሃ ወጥታ አዲስ አበባ እንድትገባና በእግሯ እንድትቆም ያደረጋት በድርቅ ለተጎዳ ሕዝብ የመጣ እርዳታ ነው።

ወያኔ ለህዝብ የመጣን እርዳታ እህል ሳይቀር የሚዘርፍ ሌባ፣ዘራፊና በቅጥፈት የተሞላ የማፊያ ድርጅት ስለመሆኑን ዋነኛ ማሳያ ደግሞ እ.ኤ.አ በ1984 የተከሰተውና በወቅቱ የቢቢሲው ጋዜጠኛ ሚካኤል ቡርክ‹‹በመሬት ላይ ለሲኦል የቀረበ ‹‹the closest thing to hell on Earth››ሲል የገለፀው ረሃብ ዋነኛ ማሳያ ነው።

በወቅቱ የወያኔ አባላት በዚህ ደረጃ አሰቃቂ ሆኖ የተገለፀውን ረሃብና የረኃብ ሰለባዎች ወደ ጎን በመተው ለነብስ ማዳኛ የመጣውን የሰብአዊ እርዳታ እህል ከታለመለት ዓላማ ውጭ ከዓለም አቀፍ ለጋሾችና አበዳሪ ድርጅቶች ጋር በመሞዳሞድ ለጦር መሳሪያ ግዥና ለግል ጥቅም አውለውታል።

ይህም የቀድሞ የማእከላዊ አባላቱ ሳይቀር በተደጋጋሚ በግልፅ በአደባባይ መስክረዋል። ጋዜጠኛ ማርቲን ፕላውትም የዘረፋ ቅሌቱን ለዓለም አጋልጦታል። ፕሮፌሰር ሀሰን ሰይድ‹‹መንግስታዊ ጥቃት በኢትዮጵያ፣ ሰብአዊ እርዳታ እና ሙስና›› በሚል ርዕስ ባሰነዱት መፅሃፍ በጥልቀት አትተውታል።

ቡድኑ ጫካ በነበረበት ጊዜ የጀመረው የዓለም አቀፍ የእርዳታ ስርቆት፣ ዘረፋና ሙስና የማይላቀቀው መናጢ አመል ሆኖበት በስልጣን በቆየባቸው ሃያ ሰባት አመታት ለምግብ፣ለመጠጥ ውሃ፣ ለመድሃኒትና ለትምህርት እየተባለ ወደ ኢትዮጵያ የሚፈሰውን እርዳት ቅርጥፍ አድርጎ በልቷል።

በኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ ትግል ስልጣኑን ከተነጠቀ በኋላም የስልጣን አባዜ የሚያመጣው እብደት ከእኛ በላይ ላሳር በሚል ትእቢት ተወጥሮ እኩይ ምግባሩን ሲያስቀጥል ቆይቷል። በተለይም ኢትዮጵያን መምራት የምችለው ብቸኛ ድርጅት ‹‹እኔ ነኝ›› በሚል መረጃ እያምታታና በሚዲያ የበላይነት ራሱን የተሻለ አድርጎ ሲያቀርብም ቆይቷል።

የሽብር ቡድኑ ከዚህ የባንዳ ተግባሩ ባሻገር ኢትዮጵያን የሚፈልጋት እርሱ እስከገዛትና የትግራይ ብሄርተኝነት የበላይነትን ይዞ እስከቀጠለ ብቻ በመሆኑ ለ20 አመታት ነፍሳቸውን ሰጥተው ሲጠብቁት የነበሩ የሰሜን እዝ አባላትን አስከፊ በሆነ መልኩ በመጨፍጨፍ እና በማዋረድ በኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ላይ ጥቃት በመሰንዘር ግልፅ ጦርነት ከፍቷል።

ጦርነቱን ወደ አፋርና ወደ አማራው ክልል በመግፋት ለበርካቶች እልቂት፣ ምክንያት ሆኗል። ወጣት፣ሴቶች፣ ህጻናትና አዛውንቶች ጨፍጭፏል። ደፍሯል። የእምነት ተቋማትን አቃጥሏል። ለመተካት የማይቻሉ ቅርሶች ሰርቋል። አውድሟል። በድሃ ህዝብ የተሰሩ ክሊኒኮች፣ ሆስፒታሎች ዘርፏል። አቃጥሏል። በርካቶችን ከቀያቸው አፈናቅሏል። ለረሃብ አጋልጧል።

**ጎብልስ የውሸት ተዋናይ ነው። የውሸት አቀናባሪ፣ ዲስኩር ደርዳሪ ነው። የውሸት ፈላስፋ ነው። የውሸትን ጥግ ያውቀዋል። በውሸት ፈጠራ እና ውሸት የመዋሸት ቴክኒክ የተካነ ነው። በውሸት መሰናዶ የተዋጣለት ነው። ውሸት ለእርሱ በጣም ቀላሉ ነው። ሙያው ነው። ስራው ነው። የዕለት ጉርሱ፣ እንጀራው ነው**

ይሑንና የቋመጠለትን ስልጣን መቆጣጠር ተስኖት፣በመጨረሻ‹‹በማንኛውም ግዳጅ ወይም ተግባር የላቀ ውጤት››በሚል እሴት የተገነባው፣በየትኛውም ሁኔታ በማንኛውም የአየር ፀባይ ማንኛውም ግዳጅ በውጤት የማጠናቀቅ አንፀባራቂ ድል የማስመዝገብ አቋምና አቅም ያለው የኢትዮጵያ ሰራዊትና የቁርጥ ቀን ልጆች ተቀጥቅጦ ወደ መጣበት ተመልሷል።

ይሑንና የቡድኑ አባላትና ጋሻጃግሬዎቻቸው የስልጣን አባዜ የሚያመጣው እብደት ከእኛ በላይ ላሳር በሚል ትእቢት ተወጥረው ፣ጤንነታቸውን በሚያጠያይቅ መልኩ ስልታዊ ማፈግፈግ ከሚለው ጀምሮ የበሬ ወለደ አይን ያወጣ የውሸት ፕሮፖጋንዳቸውን መንዛታቸውን አላቋረጡም። አዲስ አበባ ለመግባት የሰዓታት ጊዜ ነው የቀረኝ" በሚል ሲያደናግር የከረመው የጥፋት ኃይል ቆየት ብሎ ደግሞ ሌሎች የማደናገሪያ ፕሮፖጋንዳዎችን ሲያሰራጭ ተስተውሏል።

ፕሮፌሰር ጋሬዝ ጃውት እና ፕሮፌሰር ቪክቶሪያ ኦዶኔል‹‹Propaganda and Persuasion››በሚል ርእስ እኤአ በ2011 ለንባብ ባበቁት መጽሐፋቸው፣ፕሮፖጋንዳ መረጃዎችንና ሀሳቦችን ሆን ብሎ በስፋት በማሰራጨት አንድን ግለሰብ፣ቡድን፣ተቋም፣ድርጅትና አገር ለመደገፍ ወይም ለመቃወምና ለማጥላላት በድግግሞሽ የሚሰራጭ የመረጃ ቅስቀሳ ዘዴ እንደሆነ በስፋት ያትታሉ።

ሌሎች ስመጥር የኮሚኒኬሽን እና ፖለቲካ ፀሃፍት እና ምሁራንም፣ፕሮፖጋንዳን በአይነት እና በአላማው በመከፋፈል በሶስት ይመድቡታል። ከሶስቱ ፕሮፖጋንዳ አይነቶች አንዱና እጅግ አደገኛው ደግሞ‹‹ ጥቁር ፕሮፖጋንዳ ‹‹Black propaganda››የሚባለው ስለመሆኑ ይጠቁማሉ።

‹‹ትልቁ ውሸት››በሚል ሌላ ቅፅላው የሚታወቀው፣ ይሕ አይነቱ የፕሮፖጋንዳ ዘዴ መረጃ ምንጩ የማይታወቅና በሬ ወለደ የፈጠራ ውሸት፣ ወሬ፣ ሀሜትና አሉባልታዎች እውነት አስመስሎ የማናፈስና የማሰራጨት ዘዴ መሆኑን ያስገነዝባሉ።

የውሸት ፕሮፖጋንዳ በአንደኛው የአለም ጦርነት በጀርመን የተለመደ የፕሮፓጋንዳ ቴክኒክ መሆኑንም የተለያዩ መረጃዎች ይመሰክራሉ። የውሸት ፕሮፓጋንዳ ሲነሳም ዮሴፍ ጉብልስ ‹‹The Master of Lies››አብሮ ይነሳል። ሰውየው የጀርመኑ ናዚ ፓርቲ እና የመሪው አዶልፍ ሂትለር አፈ ቀላጤ ሆኖ ለአመታት አገልግሏል።

ጎብልስ የውሸት ተዋናይ ነው። የውሸት አቀናባሪ፣ ዲስኩር ደርዳሪ ነው። የውሸት ፈላስፋ ነው። የውሸትን ጥግ ያውቀዋል። በውሸት ፈጠራ እና ውሸት የመዋሸት ቴክኒክ የተካነ ነው። በውሸት መሰናዶ የተዋጣለት ነው። ውሸት ለእርሱ በጣም ቀላሉ ነው። ሙያው ነው። ስራው ነው። የዕለት ጉርሱ፣ እንጀራው ነው።

‹‹ውሸት በተደጋጋሚ ከተነገረ በመጨረሻ ሰዎች እውነት ነው ብለው ይታለላሉ የሚል እምነት ያለው ጎብልስ፣አይን ባወጣ ቅጥፈቱ የገዛ ህዝቡን ማሞኘት ይችልበታል። ህዝቡን ግራ አጋብቶ ማወናበድ፣ምንም ቢፈጠር ምንም እንዳልተፈጠረ ፣ተሸንፎ እንደአሸነፈ በመሆን ተከታዮቹን በደስታና በድል አድራጊነት የሚያስፈነጥዝ ሰው ነው። በዚህ ዋሾነቱም በስርዓተ መንግስቱ የፕሮፓጋንዳ ሚኒስትር እስከመሆን በቅቷል።

በእርግጥ ውሸት የእውነትን አቅጣጫ ሊያዛባ ይችላል። ይሑንና ይህ አይነቱ የበሬ ወለደ ውሸት ፕሮፓጋንዳ የተገነባ ድርጅትም ሆነ ማንነት የጊዜ ጉዳይ እንጂ ማነሱና ማፈሩ ብሎም መፈራረሱ አይቀሬ ነው። በአገሬ ሰው ‹‹እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል››እንደሚለው መሰል ፕሮፖጋንዳ ውሎ ሲያድር ፍፃሜው ሁሌም የተገላቢጦሽ ይሆናል።

ውሸት ለስልጣን ዕድሜ ማራዘሚያነት ይጠቅመኛል የሚለው ጎብልስም ሆነ መሪው ሂትለር የመጨረሻ የጠጡ በውሸታቸው የተጠመቀውን መራራ እና አሳፋሪ ፅዋ ማስታወስ ግን መቼም ቢሆን እውነትን ሸፍኖ ማስቀረት እንደማይቻል ማረጋገጫን የሚሰጥ ነው።

የአሸባሪው ወሃት አፈ ቀላጤዎችና ጋሻጃግሬቻቸው የጎብልስ ልጆችም ከትላንቱ የጎብልስ እና መሪው ውድቀት ሳይማሩ የውሸት ፕሮፖጋንዳን ዋነኛ ታክቲካቸው ማድረጋቸውን የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው። በእርግጥ በዚህ ተግባራቸው ለጊዜውም ቢሆን ተጠቅመዋል።

ስለ ሰው ልጆች የሰብዓዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ተቆርቋሪ ነን የሚሉት አንዳንድ ዓለም አቀፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የቡድኑን እኩይ ሥራ ከማውገዝ ይልቅ ከወልቃይት እስከ ማይካድራ ምድር ድረስ በድብቅና በገሃድ በፈጸማቸው የዘር ማጥፋት ወንጀሎች ሁሉ አይተው እንዳላዩ ሰምተው እንዳልሰሙ ብሎም ከጎናቸው እንዲቆሙ ማድረግ ችለዋል።

በተለይ በእርዳታን በሚመለከት፣ኢትዮጵያ በየቦታው የቁጥጥር ኬላ አስቀምጣ እንቅስቃሴውን አጓተተችብን እያሉ በየትዊተሩ እና ዓለምዓቀፍ መድረክ ላይ እርግማን የሚያዘንቡ ተቋማትና ባለስልጣናትን ማፍራትም ችለዋል።

ይሑንና የቡድኑ አባላት በኢትዮጵያውያን የጋራ ተጋድሎ በደረሰብት አስከፊ ሽንፈት ቅጭት ዛሬም እንደትላንቱ ከየአቅጣጫው ውሸቶችን ማስተጋባቱን ተያይዞታል። አመራሮችም እንደ ትላንቱ ሁሉ በንጹህ እንባና ደም እየነገዱ ናቸው።

ዛሬም ድረስ በለመደው ውሸትና ማስመሰል ህዝብ ያጭበረብራሉ። ውሸቱ አያልቅም አንዱ አልሰራ ሲል በሌላ ውሸት ይመጣሉ። ተርበን እንድናልቅ ዕርዳታ ዘጉብን በሚል ከምዕራባውያን አፍቃሪዎቹ ጋር በመሆን የተዛቡ መረጃዎችን ማሠራጨት በረሃብ እና ባለፈው ጦርነት በደረሠበትን ሠብዓዊ ቀውስ ለማትረፍ እየዳከሩ ይገኛል።

ጆሴፍ ጎብልስ መቃብር ፈንቅሎ ቢነሳ ሊቀናባቸው የሚችሉ ውሸቶችን እያስተጋቡም ናቸው። ይሕን ሃላፊነት ደግሞ የሕወሓቱ ጆስፍ ጎብልስ ወይንም የድርጅቱ ቃል አቀባይ ጌታቸው ረዳ በፊት አውራሪነት እየመራው ይገኛል።

ኢትዮጵያን ለማፍረስ ሲኦል ድረስ እንደሚወርድና በተለይም ከአማራ ህዝብ ጋር የምናወራርደው ሂሳብ አለ እያለ ሲናገር ቅንጣት ታክል እፍረት ያልታየበት ጌታቸው ጦርነቱን ወደ አማራና አፋር ክልል በማስፋት ለመናገር የሚዘገንን ጥፋት በህዝብ ላይ ከፈፀመ እንስሳትን ሳይቀር በጥይት ከጨፈጨፈ፣ዛፎችን ከረሸነ በኋላ ዛሬ ሳናውቅ ነው የገደልናችሁ፣ የዘርፍናችሁ የማለት ድፍረትን አግኝቷል።

ሰውየው‹‹ዝርፊያ መፈፀማችን ትክክል አልነበረም፤ ወደድንም ጠላንም አማራ ወገናችን ነው››ወዘተ›› ንግግር በመቀሌ ላይ አድርጓል። የዚህ ንግግር አላማ የአማራ ሕዝብ መቆርቆር አይደለም። ዶሮን ሲያታልሏት ዓይነት ነው።

የአፈ ቀላጤው ንግግር በተለመደ የቅጥፈት ፕሮፖጋንዳ ትላንት በመንበረ ስልጣን እያለ ግንባር ቀደም ጠላቴ የሚል ማኒፌስቶ ቀርፆ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የአማራም ህዝብ ሲያሰቃይ መክረሙ ሳያንስ ዳግም ወደ ስልጣን እንድንምጣ እርዳኝና እንደቀድሟችን እንሁን አይነት ነው።

በተደጋጋሚ ስለ ትግራይ ሕዝብ ረሃብ፣ ስለ ሰብዓዊ ዕርዳታ አስፈላጊነት የሚደሰኩሩት፣ጌታቸውና አጋሮቹ በጣም በሚያስገርምና በሚያስደነግጥ መልኩ ለክልል ህዝብ የመጣን የእርዳታ እህል ዛሬም እንደ ትላንቱ የግል ጥቅም እያዋሉት መሆኑ ነው።

ይሕንንም አፈና እና ጭቆናው አንገሸግሿቸው ወደ አማራ ክልል የተሰደዱ ዜጎች ሳይቀር የመሰከሩት ነው። የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ያነጋገራቸው የትግራይ ዴሞክራሲዊ ፓርቲ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ሙሉብርሃን ኃይሌም፣ የሰብዓዊ እርዳታ ወደ ትግራይ ክልል የሚላክ ቢሆንም ለሕዝቡ የሚደርስ እርዳታ የለም››ሲሉ ይሕኑ አረጋግጠዋል። ለትግራይ ሕዝብ የሚላከው እርዳታ ለሕዝቡ ሳይሆን ሕወሓት ራሱ ላደራጃቸው መደቦችና ታጣቂዎች እየተሰጠ መሆኑን ፓርቲያቸው ከተለያዩ ምንጮች እንዳረጋገጠ ገልጸዋል።

በሰብአዊ እርዳታ ሰበብ የሚደሰኩሩትን ጀምሮ በእያንዳንዱ ተግባር የጎብልስ ልጆች አላማ ሕዝብ እና ሰራዊቱን በስነ ልቦና ዘመቻ ለመፍታት መሆኑ እርግጥ ነው። ይሑንና ደግሞ ጠላትን ለማሸነፍ በአስተሳሰብ በልጦ መገኘት የግድ ነው።

ስለ ረሃብ፣ ስለ ሰብዓዊ ዕርዳታ ቀን ከሌት ሲወተውቱ የሚደመጡትም ለህዝብ ተጨንቀው አይደለም። ይልቅስ ለዳግም ውግያ ትጥቅና የስንቁን ጉዳይ በዚህ መንገድ ለማሳካት የሚመስል ነው። ቡድኑ አሁን ላይ የሆነ ሴራ እያሴረ መሆኑም እርግጥ ነው። የቡድኑ መሪ ዶክተር ደብረጽዮን ገብረሚካኤል ለተመድ ዋና ጸሐፊ የላኩት ደብዳቤም ይህን የሚያረጋግጥና ዛሬም ለስልጣን እንደሚቀምጡ ፍንጭ የሚሰጥ ነው። መልእክቱንም አፍቃሪ ሕወሓቶቹ ሊንዳ ቶማሥ እና ማርቲን ፕላውት በማህበራዊ ሚዲያው በኩል አጋርተውታል።

ይሕ ደግሞ ሕወሓት አሁንም ለሰላም እጁን የመዘርጋት ፍላጎት እንደሌለው የሚጠቁም ነው። በመሆኑም የኢትዮጵያ መንግሥት አጎራባቾቹ የአማራ ክልል እና የአፋር ክልል የጸጥታ ኃይሎች ትኩረታቸውን ከቡድኑ ባለመለየት፣ጠንካራ ዝግጅት ማድረግ የግድ ይላቸዋል።

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## መንግሥትና ከያኒያን አብረው መስራት ያለባቸው ወቅት

**ዋሰልኝ አዩለ**

በ2010 ዓ.ም ነው። ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ወደ ሥልጣን መምጣታቸውን ተከትሎ የተለያዩ ባለሙያዎችን እያወያዩ ነበር። ከእነዚህ ባለሙያዎች መካከልም የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች ይገኙበታል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አብይ አህመድ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎችን ማወያየታቸው የዚያ ሰሞን አጀንዳ ሆኖ ነበር። ያንኑ ውይይት ምክንያት በማድረግ ኤፍ ኤም አዲስ 97.1 የኪነ ጥበብ ባለሙያዎችን ስቲዲዮ ጋብዞ አንድ ውይይት ማካሄዱን አስታውሳለሁ። በውይይቱም አድማጮች የራሳቸውን አስተያየት ሲሰጡ ነበር። ከውይይቱ አንድ የኪነ ጥበብ ባለሙያ የተናገሩት ዛሬም ድረስ ውስጤ አለ። የገረመኝ ምክንያት ደግሞ የኪነ ጥበብ ሰው ሆነው ራሳቸው የኪነ ጥበብ ባለሙያውን መተቸታቸው ነበር።

ባለሙያው እንዳሉት፤ የኢህአዴግ አፋኝነት ለብዙ የጥበብ ሰዎች የስንፍና መደበቂያ ሆኖ ነበር። የሚገርም ድርሰት ጽፌ መንግሥት አገደብኝ ይባል ነበር። የኢትዮጵያን የፊልም ኢንዱስትሪ የሚያስመነድግ ፊልም ሰርተን መንግሥት እንዳይወጣ ከለከለን ይባል ነበር። እነዚያ ሰዎች ‹‹እስኪ ድርሰቱን አምጡት!›› ቢባሉ ላይኖራቸውም ይችላል ነበር ያሉት። ‹‹አሁን ነፃነቱ ተሰጥቷልና እስኪ ታግዶብኝ ነው ሲል የነበረ ሁሉ ያምጣው!›› ማለታቸውን አስታውሳለሁ። እኚህ ሰው ያንን አስተያየት የሰጡት በቅርበት የሚያውቁት ቢኖር ነው። ስንፍናን በመንግሥት ማሳበብና ይህንንም መደበቂያ ማድረግን ከተወቃሽነት ለመዳን ይጠቀሙበታል።

እዚህ ጋ ደግሞ ሌላ ወቀሳ አለ። ይህኛው እኔ ራሴ የታደምኩበት መድረክ ነው። የያኔው የሰላም ሚኒስትር ወይዘሮ ሙፈሪያት ካሚል የተገኙበት አንድ መድረክ ስድስት ኪሎ በሚገኘው ባህል ማዕከል (በተለምዶ ስብሰባ አዳራሽ) ‹‹ኪነ ጥበብ ለሰላም›› በሚል ከኪነ ጥበብ ባለሙያዎች ጋር የተደረገ አንድ ውይይት ነበር።

በውይይቱ ላይ ከተለያዩ የጥበብ ባለሙያዎች የተነሱ ቅሬታዎች ሲጨመቁ፤ መንግሥት የኪነ ጥበብ ባለሙያውን የሚፈልገው ሲጨንቀው ነው። ኪነ ጥበብ በሕዝብ ውስጥ ያለውን ሚና፣ ተቀባይነት፣ ፣ ሃይል ፣ወዘተ ስለሚያውቅ፤ ከሕዝብ ቁጣ ባጋጠመው ወቅት ወደ ኪነ ጥበብ ባለሙያው ያተኩራል። በአዘቦት አብረን እንሥራ ያላለውን በችግር ወቅት የአብረን እንሥራ የጥሪ ደብዳቤ ጋጋታ ያበዛል። የኪነ ጥበብ ዘርፉን ለማሳደግ ራሱን የቻለ ተቋማዊ አደረጃጀት ፈጥሮ ከባለሙያው ጋር አልሰራም የሚሉ ቅሬታዎች ተነስተዋል።

በነገራችን ላይ እስከአሁን በኪነ ጥበብ ዘርፉ ላይ እዚህ ግባ የሚባል የተመሰገነ ለውጥ ባይመጣም፣ በቅርቡ አዲሱ መንግስት ያወቀረውን ካቢኔ ተከትሎ በአደረጃጀት ደረጃ ራሱን የቻለ ዘርፍ ተቋቁሟል። የባህልና ቱሪዝም ሚኒስትር ወደ ባህልና ስፖርት ሚኒስትርነት ሲቀየር ኪነ ጥበብ ራሱን የቻለና በሚኒስትር ዴኤታ የሚመራ ዘርፍ ሆኗል። በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደረጃ ደግሞ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የነበረው፤ ባህል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ተብሏል። እነዚህ ነገሮች ኪነ ጥበብ ቢያንስ በስም ደረጃ እንኳን ትኩረት እየተሰጠው መሆኑን ይጠቁማሉ።

ይህንኑ ጉዳይ በተመለከተ በዚህ ዓመትም መድረኮች ተካሂደዋል። በቅርቡ የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚካሄደውን የምስራቅ አፍሪካና የታላላቅ ሀይቆች ሀገሮች የባህልና ኪነጥበብ ሳምንት አስመልክቶ ከመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች ጋር ውይይት አድርጎ ነበር።

በውይይቱ ላይ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የኪነጥበብ፣ ስነጥበብና ፈጠራ ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ነፊሳ አልማህዲ፣ ከኪነጥበብ ዘርፉ መጠቀም ያለብንን ያህል አልተጠቀምንም። የኪነ ጥበብ ባለሙያውም ህዝቡም መጠቀም ባለባቸው ልክ አልተጠቀሙም። ሌሎች አገሮች ግን በኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ፋይዳው በሚገባ እየተጠቀሙበት ሲሉ አስታውቀዋል።

ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ በኪነ ጥበብ ባለሙያው ይነሳ የነበረውን ቅሬታም አንስተዋል። ተጠቃሚ አልሆነም፤ ችግር ሲደርስበት እርዳታ ሲጠይቅ ነው የሚታየው ብለዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታዋ ገለጻ፤ ከኪነጥበቡ አንደኛ የጥበብ ሰዎች መጠቀም አለባቸው፤ ጥበቡን ከምናባቸው አውጥተው ነው የሚፈጥሩት፤ ማግኘት የሚገባቸውን ማግኘት አለባቸው፤ ማግኘት ያለባቸውን ማግኘት እንዳይችሉ ያረገው ምንድን ነው የሚለው መታወቅ አለበት።

‹‹ሰዎች ሙዚቃ እያዝናና ያስተምራል ብቻ ብለው ነው የሚያስቡት፤ እያዝናና ያስተምራል ብቻ ሳይሆን ሰዎችን ተጠቃሚ ያደርጋል ወደሚለው ወስደን በዚህ ላይ በደንብ መስራት አለብን። ወደ እዚህ መስሪያ ቤት ከመጣሁ በኋላ እንደምመለከተው የሚታየው ብዙም የሚያስደስት አይደለም፤ ያመኛል›› ሲሉ ያለውን ችግር ገልጸውታል። መሰራት ያለበት እንዳለም ተረድተዋል።

ሚኒስትር ዴኤታዋ እንደተናገሩት፤ መንግስትም ይህንን ተመልክቶ ነው የኪነጥበብና ስነጥበብ ክፍሉ ራሱን ችሎ በሚኒስትር ዴኤታ እንዲደራጅ ያደረገው። ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሰዎች የሚያነሷቸውን እና ሌሎች የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት ነው በሚኒስትር ዴኤታ ደረጃ በአዋጅ የተቀመጠው።

ከዚህ አንጻር ምቹ ሁኔታ አለ ብለን መጠቀም አለብን፤ አደረጃጀቱ በባህል ስር ነበር፤ አሁን ራሱን ችሏል። አደረጃጃቱ አለ፤ በሙያው የሰለጠኑ ሰዎች አሉ፤ ጥበቡን የሚፈልጉ ማህበረሰብ ክፍሎች አሉ። ስራው ከኛ ነው የሚጠበቀው፤ ሁሉም ነገሮች አሉ ሲሉም አስገንዝበዋል።

የኪነ ጥበብ ባለሙያውም ሆነ መንግሥት እርስበርስ መወቃቀስ ሳይሆን አብረው መስራት ነው ያለባቸው። ራሱን የቻለ ዘፍር መደራጀቱ በመንግሥት በኩል ትኩረት እንዲሰጠው ያግዛል። የኪነ ጥበብ ባለሙያውም በራሱ በኩል መወጣት ያለበትን በመወጣት አብረው ከሰሩ ተገቢውን ጥቅም ያገኛሉ።

የኪነ ጥበብ ባለሙያው ተገቢውን ጥቅም ላለማግኘቱ በተደጋጋሚ የሚነሳው አንዱ ምክንያት ደግሞ የባለቤትነት መብት ጉዳይ ነው። በተለይም በሙዚቃው ዘርፍ ይሄ ችግር ሲደጋገም ይሰማል።

የኢትዮጵያ ሙዚቀኞች ማህበር ፕሬዚዳንት ዳዊት ይፍሩን በዚሁ ጉዳይ ላይ አነናግረን ነበር። ፕሬዚዳንቱ በተለይም ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤ አርቲስቱ የፈጠራ ሥራው ተጠቃሚ ለመሆን እየጣረ ነው። ለዚህም የቅጅና ተዛማጅ መብት ማህበር ተቋቁሟል። ማህበሩ ከአዕምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት ጋር በጋራ እየሰራ ነው። ከሚዲያ ተቋማትም ጋር ይሰራል።

> *ኪነ ጥበብ አገርን ለማስተዋወቅ ከየትኛውም ነገር በላይ አቅም አለው። መንግሥትም ሆነ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች ይህን መረዳት አለባቸው። መንግሥት ኪነ ጥበብን የተመለከተ መዋቅር ሲዘረጋ ባለሙያው ደግሞ ዕድሉን መጠቀም አለበት*

የፈጠራ ባለቤቱን ተጠቃሚ ለማድረግ ከአዕምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤትና ከሚዲያ ተቋማት ጋር በጋራ የሚደረገው ሥራ ከመጪው ሐምሌ እስከ መስከረም ባለው ጊዜ እንደሚጀመርና በትኩረት እንደሚሰራበትም ነው ፕሬዚዳንቱ የተናገሩት።

እንደ አርቲስት ዳዊት ገለጻ፤ ባለሙያዎቹ በፈጠራ ሥራዎቻቸው እስከ አሁን ተጠቃሚ ባይሆኑም ከዚህ በኋላ በትኩረት ከተሰራበት ግን ተጠቃሚ ይሆናሉ። ሥርዓቱ ከተዘረጋ ብዙ ሰው ተጠቃሚ ይሆናል። ዜማና ግጥም የደረሰው ብቻ ሳይሆን ያንን መድረክ ላይ የተጫወቱትም ሰዎች ተጠቃሚ የሚሆኑበት መንገድ እንዲኖር እየተሰራበት ነው። ምክክሩ ረዘም ያለ ጊዜ ሊወስድ ቢችልም ከተጠናቀቀ ግን ተጠቃሚ ያደርጋል ብለዋል።

‹‹በመንግሥት በኩል ሕግ ወጥቷል›› ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ መንግሥት ያወጣውን ሕግ እና ለኪነ ጥበብ ዘርፉ የሚቀርብ አደረጃጀት መፍጠሩን እንደ ጥሩ ዕድል በመጠቀም በትኩረት መሥራት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል። የሙብት ባለቤቶች መብታቸውን ለማሳከበር ከሁሉም ባለድርሻ አካላትና እና ከባለሙያው ጋር መሥራት እንደሚገባቸው አሳስበዋል።

‹‹በግለሰብ ደረጃ መሯሯጥ መፍትሔ አያመጣም›› ያሉት ባለሙያው፤ ባለሙያውንም፣ ሕዝብንም ተጠቃሚ የሚያደርገው በጋራና በትብብር መሥራት ሲቻል እንደሆነም ተናግረዋል። የፈጠራ ባለሙያውም ከቸልተኝነት መውጣት እንዳለበት አስገንዝበዋል።

በሌላ በኩል ባለሙያዎቹ ራሳቸው የአንዱን ፈጠራ አንዱ መውሰድ እንደሌለባቸውም የማህበሩ ፕሬዚዳንት አሳስበዋል። በተለይም ጀማሪ ባለሙያዎች የራሳቸውን የፈጠራ ሥራ ማቅረብ አለባቸው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፣ ያለባለቤቱ ፈቃድ የቀደሞ ሥራዎችን ያቀርባሉ። መሥራት ካስፈለገ ባለቤቱን በማስፈቀድና ለባለቤቱም ተገቢውን ጥቅም በመስጠት ነው ሲሉ ያብራራሉ። እነዚያ የቀደሞ ሥራዎች ተወዳጅ የሆኑት የራሳቸው ወጥ ፈጠራ ስለሆኑ ነው፤ ስለዚህ የጥበብ ባለሙያውም እንዲህ አይነት ችግሮችን ለመቅረፍ በጋራ መሥራት አለበት ሲሉ ያስገነዝባሉ።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፊልም ትምህርት ቤት መምህር የሆኑት አቶ ዳንኤል ወርቁ በተለይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤ ኪነ ጥበብ አገርን ለማስተዋወቅ ከየትኛውም ነገር በላይ አቅም አለው። መንግሥትም ሆነ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች ይህን መረዳት አለባቸው። መንግሥት ኪነ ጥበብን የተመለከተ መዋቅር ሲዘረጋ ባለሙያው ደግሞ ዕድሉን መጠቀም አለበት።

እንደ አቶ ዳንኤል ገለጻ፤ የጥበብ ባለሙያዎች ከመንግሥት አስፈላጊውን ድጋፍ ለማግኘት ጥረት የሚያደርጉት በተናጠል ነው፤ ያ ደግሞ ውጤታማ አያደርግላቸውም፤ መንግሥትም ነገሩን እያድበሰበሰ ሊያልፈው ይችላል፤ ባለሙያዎች በሕብረት ሆነው ከጠየቁ ግን አስፈላጊውን እገዛ የማግኘት ዕድላቸው ይሰፋል።

መንግሥት ለጥበብ ሥራዎች ድጋፍ ማድረግ እንዳለበት የገለጹት መምህር ዳንኤል፤ ሀገሮች የፊልም ኢንዱስትሪያቸው ያደገው ፈንድ ስለሚመደብላቸው መሆኑን ጠቅሰዋል። ከአፍሪካ አገራት እነ ናይጀሪያ ፈንድ ስለሚደረግላቸው ነው ፊልማቸው አድጎ አገራቸውን ያስተዋወቀው፤ በኢትዮጵያ ግን ይህ አልተለመደም። ባለሙያውም ሆነ መንግሥት በመተጋገዝ መሥራት አለባቸው። መንግሥት በሚያቋቁመው ዘርፍ ውስጥ ለሙያው ቅርበት ያላቸው ሰዎች መግባት አለባቸው ሲሉም አሳስበዋል።

የጥበብ ባለሙያዎች አቅም ፈጥረው ተወዳጅ ፊልም ቢያቀርቡ የመንግሥት ተቋማትም ተባባሪ እንደሚሆኑ መምህር ዳንኤል ይገልጻሉ። ለምሳሌ የፊልም ኢንዱስትሪው በተደጋጋሚ ሲወቀስ ይሰማል፤ ይህን የሚሰማ የመንግሥት ተቋምም ለፊልም ሥራ ተባባሪ ለመሆንና ለሚቀርብለት ጥያቄ ፈጣን ምላሽ ለመስጠት ወኔ አይኖረውም። ስለዚህ የፊልም ባለሙያው በሕብረት ሆኖ በመሥራት የፊልሙን አቅም ማሳየት እንዳለበት ያሳስባሉ። በግለሰብ ደረጃ ዓለም አቀፍ ሽልማት የሚያስገኝ ሥራ ሊሰራ ይችላል፤ ዳሩ ግን በጋራ የሚታይ ሥራ ካልተሰራ ውጤታማ አይሆንም ይላሉ።

እንደ አቶ ዳንኤል ገለጻ፤ ሥራዎች በባለሙያው መተጋገዝ በጋራ ካልተሰሩ ግለሰብ ላይ ሲንጠለጠሉ ትኩረታቸው ገንዘብ ለማስገኘት ብቻ ይሆናል። ስለዚህ ባለሙያው ከመንግሥት ለሚያገኘው ድጋፍም ሆነ የሚሰራውን የጥበብ ሥራ ደረጃ ለማስጠበቅ በጋራ ሊሰራ ይገባል።

ልክ እንደ ሕንጻና ሌሎች የሙያ ሥራዎች ሁሉ የጥበብ ሥራም ‹‹ስታንዳርድ›› ሊኖረው ይገባል ይላሉ መምህሩ። ለዚህ ደግሞ መፍትሔው የባለሙያው መተጋገዝና አብሮ መሥራት ነው። አለበለዚያ የተበላሸ ሥራ ለሕዝብ ሲቀርብ ተወቃሽ የሚሆነው አጠቃላይ ዘርፉ ነው ሲሉ ያስገነዝባሉ።

የጥበብ ባለሙያውም ተገቢውን ጥቅም የሚያገኘው በባለሙያ እይታ ደረጃውን የጠበቀ ሥራ ሲቀርብ ነው። አንድ ሕንጻ ከንድፉ ውጭ ዝንፍ ቢል እንደገና ይፈርሳል እንጂ ከንድፍ ውጭ አይሰራም፤ የፊልም ሥራ ግን ለ100 ብር ብሎ እንኳን ቢሰራው ዝም ሊባል ይችላል፤ ስለዚህ ዘርፉን ያስወቅሰዋል፤ እንዲህ አይነቱን አሰራር ለማስቀረት ባለሙያው በጋራ መሥራት አለበት ብለዋል።

በመንግሥት በኩልም፤ ልክ ለዘጋቢ ፊልሞችና ለሌሎች ሥራዎች ፈንድ እንደሚደረገው ሁሉ ለኪነ ጥበብ ዘርፉም ማድረግ እንዳለበት ያሳስባሉ። ለአገር የሚጠቅም ከሆነ የመንግሥት ድርጅቶች አዋጥተውም ቢሆን ድጋፍ ማድረግ እንዳለባቸው ነው ያስገነዘቡት፤ የአገር ጉዳይ የማይመለከተው የመንግሥት ተቋም የለም። ስለዚህ ዘርፉን ማሳደግ በዋናነት የመንግሥትና የባለሙያው ጥረት መሆኑን ተናግረዋል።

ለኢንዱስትሪው ማደግ ባለሙያውም ጥረት ማድረግ፤ መንግሥትም ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ አለባቸው እንላለን! ባለሙያው ምንም ሳይንቀሳቀስ መንግሥትን ብቻ ቢወቅስ ለውጥ አይመጣም፤ መንግሥትም የሚመጣለትን ጥያቄ ሁሉ ትኩረት ሳይሰጥ ቆይቶ ሲያስፈልጉት ብቻ ‹‹ኑ አግዙኝ›› ቢል ከተወቃሽነት አይድንም፤ ስለዚህ ተጋግዞ በመሥራት አገርንም ባለሙያውንም የሚጠቅም ሥራ ይሰራ!

# ልዩ ልዩ

## ዛሬም አሳሳቢው የአካል ጉዳተኝነትና ሰብአዊ መብቶች ጉዳይ

ግርማ መንግሥቴ

ሁሌም እንደሚባለው አካል ጉዳተኝነት ተፈጥሯዊ አይደለም። ድንገት መጥ እንጂ ለአንድ ሰው፣ በተለይ አካል ጉዳተኛ ይሆን ዘንድ የተሰጠው ችግር አይደለም። በዓለም አቀፍ ከአንድ ቢሊዮን በላይ አካል ጉዳተኞች፣ በኢትዮጵያ 20 ሚሊዮን የሚጠጉ ዜጎች ከተለያየ ዓይነት የአካል ጉዳት ጋር የመኖራቸው ምስጢር ይኸው እንጂ ሌላ አይደለም። ለዚህም ነው የሴቶች እና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ ከትናንት በስቲያ ከአዲስ ዘመን ጋር ባደረጉት ቆይታ ችግሩን በ«ማንኛውም ሰው ላይ ከውልደት እስከ ዕለተ ሞት ድረስ በማይክሮ ሰከንዶች ውስጥ የአካል ጉዳት ሊከሰት ይችላል። ክስተቱ በሰከንዶች ሊፈጠር የሚችል በመሆኑ ጉዳዩን የጋራ አድርጎ ከልብ መሥራት ያስፈልጋል፤ ጉዳዩ ለአካል ጉዳተኞች ብቻ ሊተውና ሊገፋ አይገባም» በማለት የገለፁት። ስለዚህ ምን ይደረግ?

በዓለማችን አንድን የሚገፋ የማይመስልን ችግር ከስሩ ፈንቅሎ ለመጣል ብቸኛው በሚመስል ደረጃ መፍትሄው መደራጀት ሆኖ ከተገኘ ሰንብቷል። በአገራችንም ከአንድ ብርቱ ሁለት መዳኒቱ የሚለው አባባልም የሚያሳየን ይህንኑ የመደራጀት አስፈላጊነትን ነው። በ25ኛው የአካል ጉዳተኞች ፌዴሬሽን የምሥረታ ክብረ በዓል ላይ የተገኙት ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬም ይህንኑ በሚያጠናክር መልኩ ነው የመደራጀትን አስፈላጊነት የተናገሩት።

እንደ ሚኒስትሯ አገላለፅ አካል ጉዳተኞች በተደራጀ መንገድ የሚያካሂዱት ትግል አድልዎ እና መገለልን እያስወገደ መጥቷል፤ በአካል ጉዳተኞች ላይ ሲደርሱ የነበሩት የመገለልና አድልዎ ተግባራት ስፍራቸውን ለእኩል ዕድል እየለቀቁ ይገኛሉ። ለዚህ ውጤት መገኘት አካል ጉዳተኞች በተደራጀ መንገድ መንቀሳቀሳቸው በመሆኑ ይበል የሚያሰኝ ነው። ተግባሩም ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባዋል።

ሌላውና ሊቀረፍ የሚገባው ችግር የአካታችነት ችግር ነው። እስካሁን ባለው አሠራርም ሆነ አተያይ በዓለማችን የአካታችነት ችግር በብዛት ይስተዋላል።


ፎቶ- ገበበ ገብሬ

የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች በአካቶ ፕሮግራም

የአካል ጉዳተኞችም ድምፅ «አልተካተትንምና ልንካተት ይገባዋል» የሚል ነው። ይህንን በተመለከተም በተደጋጋሚ የተለያዩ የሕግ ማዕቀፎች ሲዘጋጁ ቢታዩም ተግባራዊነት ላይ ግን ችግር መኖሩ አልቀረም። ወይም፣ የአፈፃፀም ችግር አለ። በዚሁ፣ «ጉዟችን ይቀጥላል» በሚል መሪ ሐሳብ በተከበረው በ25ኛው የአካል ጉዳተኞች ፌዴሬሽን የምሥረታ ክብረ በዓል ላይ የተገኙት ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ እንደሚሉት ለአካል ጉዳተኞች ቅድሚያ የሚሰጥ አካታችነት ያለው አሠራርም በየተቋማቱ ጎልቶ ሊወጣ፤ የአካል ጉዳተኞች መብት፣ ጥቅምና ተሳትፎ እንዲከበር የሚደረገው ጥረትም ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባዋል።

አካል ጉዳተኞች ለዘመናት ከተሳትፎና ተጠቃሚነት ተገፍተው ሊኖሩ እንደማይገባ፤ መብትና ጥቅሞቻቸውን ለማክበርም መንግሥታት፣ የአካል ጉዳተኛ ማኅበራትና አካል ጉዳተኞች፣ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችና ማኅበረሰቡ እየተሻሻሉ የመጡ ሕጎችን እየተገበሩ እንደሚገኙት ሁሉ ይህንንም አጠናክረው መቀጠል ያለባቸው መሆኑን፤ በጎጂ ልማድ፣ በተዛባ አመለካከት፣ በአግላይ ሕግጋትና በመልካም አስተዳደር እጦት የተነሳም አካል ጉዳተኞች ተጋፍጠውት የነበረው ችግር ውስብስብና ለዘመናት ትውልድ የተቀባበለው ዘርፈ ብዙ መከራ እየገፋ እዚህ ስለ መድረሳቸው፤ ይህ አስከፊ ገጽታ እንዲቀየርም በመንግሥታት፣ በአካል ጉዳተኛ ማኅበራትና በአካል ጉዳተኞች፣ በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችና በአጠቃላይም በማኅበረሰቡ በኩል እየተደረገ ባለው ጥረት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ተጨባጭ ለውጥ ማሳየት መጀመሩን እና የመሳሰሉት ይገኙባቸዋል።

ተሳትፎና አካታችነትን በተመለከተ አንድ ማሳያ ሊሆን የሚችል ተቋም መጥቀስ ይቻላል።

በበላይ ዘለቀ ቁ.2 ትምህርት ቤት ተገኝተን እንደተመለከትነው አካቶ ፕሮግራምን የያዘ በመሆኑ ለየት ብሎ አግኝተነው እንደ ነበር በስፋት የተነጋገርንበት ጉዳይ ነው። ከትምህርት ቤቱ ካገኘነው መረጃም መረዳት የቻልነው ትምህርት ቤቱ ከሙአለ ሕፃናት ጀምሮ እስከ 8ኛ ክፍል ድረስ፣ በሦስት ሳይክል የሚያስተምር ሲሆን፤ ለየት የሚያደርገው ከእነዚህ ሳይክሎች (ደረጃዎች?) በተጨማሪ «አካቶ»ንና ልዩ ፍላጎት ፕሮግራምን አካቶ የሚገኝ መሆኑን ነው።

እዚህ ላይ በላይ ዘለቀ ቁጥር 2ን እንደ ማሳያ እንጥቀስ እንጂ ሌሎች ትምህርት ቤቶች አይሰጡም እያልን አይደለም። እንደ አገር ካየነው ግን «አለ» ለማለት ያስቸግራል።

ይህ ፀሐፊ አሁን ያለበትን ሁኔታ ባያውቅም ባለፈው አመት «ኢትዮጵያ ሴንተር ፎር ዲሴቢሊቲ ኤንድ ዴቨሎፕመንት (ኢሲዲዲ) በኢትዮጵያ የመጀመሪያ ነው የተባለ እና ለአካል ጉዳተኞች መረጃ የሚሰጥ 6768 የነፃ ጥሪ ማዕከል» ማቋቋሙን፤ «የዚህ የመረጃ ማዕከል ዋና አላማ ከአካል ጉዳት ጋራ የተያያዙ አስፈላጊ በድምጽ የተዘጋጁ መረጃዎችን ለአካል ጉዳተኛው እና ለተቀረው ማኅበረሰብ ማቅረብ» መሆኑን፤ «አካል ጉዳተኞች ጥያቄ ቢኖራቸው ወይንም ማካፈል የሚፈልጉት ልምድ ካለ ድምጻቸውን ቀርፀው መላክ እንደሚችሉ»፤ «ከአገልግሎቶቹ መካከልም ስለ አካል ጉዳተኞች በኢትዮጵያ ውስጥ ያለን አዲስ መረጃ መግለጽ፣ ስለ አካል ጉዳተኛነት ጠቅላላ መረጃ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ስለ አካል ጉዳተኞች ያሉ ሕጎች፣ አካል ጉዳተኝነት ምን ማለት እንደሆነ፣ ከአካል ጉዳተኞች ጋር የሚሠሩ ምን ዓይነት ቋንቋ መጠቀም እንዳለባቸው የሚያስረዱ መረጃዎች መያዙ»፤ «ስለ አካቶ ጤና፣ ተደራሽ ስለሆኑ የጤና ተቋማት እና ስለ ጾታዊ ጥቃት፣ ስለ አካቶ ትምህርት፣ ስለ አካቶ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና፣ ስለ ሥራ እና ሥራ ገበያ፣ የሥራ ዕድሎች መረጃ» መስጠት የሚችል መሆኑ ወዘተ በድርጅቱ የሥራ ኃላፊዎች ተገልፆ እንደነበር ያስታውሳል።

ይህንን እዚህ መጥቀስ ያስፈለገበት አቢይ ምክንያት ይህንን መሰል ተቋማት በየዘርፉ ሊገነቡና ሊስፋፉ የሚገቡ መሆናቸውን ለመግለፅና አካል ጉዳተኞችም እንደማንኛውም ዜጋ ተጠቃሚ መሆን ያለባቸው መሆኑን ለመጠቆም ሲሆን፤ እንደ «የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ልማት ማዕከል» በመባል የሚታወቀው መንግሥታዊ ያልሆነ ተቋም"ና የመሳሰሉትንም ሳንረሳ፤ የአካል ጉዳተኞች መብት ጉዳይ የሌላ ሳይሆን የመሠረታዊ ሰብአዊ መብቶች ጉዳይ መሆኑንም በማስታወስ ነው።

# ዓለም አቀፍ

## የዩክሬኑ ጦርነት ባለፉት 50 ዓመታት ያልታየ የዋጋ ንረት እንደሚያስከትል ተገለጸ

በጋዜጣው ሪፖርተር

በጋዜጣው ሪፖርተር የዩክሬን ጦርነት ከአውሮፓውያኑ 1970ዎቹ ወዲህ በዓለማችን ታይቶ የማይታወቅ የሸቀጦች እጥረት ሊያስከትል እንደሚችል የዓለም ባንክ አሳሰቧል።

የዓለም ባንክ ባወጣው ትንበያ መሠረት የሩሲያና የዩክሬን ጦርነት በበርካታ ምርቶች ላይ የዋጋ ጭማሪ እያስከተለ ሲሆን፤ ከነዚህ መካከል በዋነኛነት የተፈጥሮ ጋዝ፣ ስንዴ እንዲሁም ጥጥ ይገኙበታል።

‹‹የዋጋ ጭማሪው ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ እና ሰብአዊ ጫናዎችን እያስከተለ ነው›› ብለዋል ሪፖርቱን ካዘጋጁት መካከል አንደኛው የሆኑት ፒተር ኔግል ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

አክለውም ‹‹በመላው ዓለም የሚገኙ ቤተሰቦች ጫናውን በደንብ እያስተዋሉት ነው። እኛን በጣም የሚያሳስበን ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች ጉዳይ ነው። ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች ናቸው ምግብ ለማግኘት ከፍተኛ ጉልበትና ገንዘብ የሚያወጡት። የዋጋ ንረት ተከሰተ ማለት እነዚህን ቤተሰቦች ነው በቀጥታ የሚመለከተው›› ብለዋል።

የኃይል አቅራቢ ድርጅቶች ዋጋ ከ50 በመቶ በላይ ጭማሪ ያሳየ ሲሆን ይህ ደግሞ ለድሃ ቤተሰቦችና አነስተኛ የንግድ ተቋማት መጥፎ ዜና ነው በማለት የዓለም ባንክ አመልክቷል።

ከፍተኛው የዋጋ ጭማሪ የሚኖረው አውሮፓ ውስጥ ሲሆን፤ በዚህም ምናልባት ዋጋዎች ከሁለት እጥፍ በላይ ጨምረው ልንመለከት እንችላለን። የዋጋ ንረቱ በሚቀጥለው የፈረንጆቹ ዓመት እንዲሁም በ2024 ቅናሽ እንደሚያሳይ ተገምቷል።

ነገር ግን ምንም እንኳን ቅናሽ ቢስተዋል ከዚህ በፊት ከነበሩት ዋጋዎች አንጻር እስከ 15 በመቶ የሚደርስ ጭማሪ ይኖረዋል ብሏል የዓለም ባንክ።

የነዳጅ ዋጋም ቢሆን ጭማሪ እያሳየ እስከ 2024 ድረስ ሊቀጥል እንደሚችል የተገመተ ሲሆን፤ ያልተጣራ ድፍድፍ በርሜል ነዳጅ በዚህ ዓመት እስከ 100 ዶላር ሊያወጣ ይችላል።

ይህ ደግሞ በከፍተኛ ሁኔታ የዋጋ ንረትን ያባብሰዋል። ሩሲያ ዓለማችን ከምትጠቀመው ነዳጅ 11 በመቶ የሚሆነውን ታቀርባለች።

ነገር ግን ጦርነቱ ቢቆም እንኳን ጦርነቱን ተከትሎ በርካታ ያደጉ አገራት ሩሲያ ላይ ማዕቀብ መጣላቸው እና ትልልቅ የአውሮፓና አሜሪካ ድርጅቶች ሩሲያን ጥለው መውጣታቸው ለወደፊቱ በርካታ መዘዞችን ይዘው ይመጣሉ።

በሌላ በኩል አውሮፓውያን ከሚጠቀሙት ጋዝ 40 በመቶ የሚሆነው ከሩሲያ ሲሆን፣ የሚመጣው 27 በመቶ የነዳጅ ፍላጎታቸውም ቢሆን የሚሟላው በሩሲያ ነው።

ይህ ደግሞ በተለይ በአውሮፓ የዋጋ ንረቱ ከዕለት ወደ ዕለት እንዲጨምርና እጥረት እንዲከሰትም እያደረገ ነው። የዓለም ባንክ እንደሚለው ከነዳጅና ጋዝ በተጨማሪ የምግቦች ዋጋም ቢሆን በእጅጉ ይጨምራል።

የተባበሩት መንግሥታትም ቢሆን በ60 ዓመታት ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ የምግቦች ዋጋ ንረት መከሰቱን አስታውቋል። የስንዴ ዋጋ የ42 በመቶ ጭማሪ ያሳየ ሲሆን ገብስም ቢሆን የ33 በመቶ ጭማሪ ታይቶበታል።

የዶሮ ምርቶች የ41 ነጥብ ስምንት በመቶ ጭማሪ እንዲሁም ሌሎች ጥራጥሬዎች የ29 ነጥብ ስምንት በመቶ የዋጋ ጭማሪ ተስተውሎባቸዋል።

እነዚህ ሁሉ ቁጥሮች የሚያሳዩት ደግሞ ሩሲያና ዩክሬን ምን ያህል ለዓለማችን ትልቅ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ አገራት እንደሆኑ ነው።

ከጦርነቱ በፊት ሁለቱ አገራት የዓለም ሕዝብ ከሚመገበው ስንዴ 28 ነጥብ ዘጠኝ በመቶ የሚሆነውን ያቀርቡ የነበረ ሲሆን፤ ዓለም ለማብሰል ይጠቀመው የነበረው የሱፍ ዘይትም ቢሆን 60 በመቶው የሚመጣው ከነዚሁ አገራት ነበር።



## ሩሲያ ለፖላንድ እና ቡልጋሪያ የጋዝ አቅርቦቷን አቋረጠች

በጋዜጣው ሪፖርተር

ሩሲያ ከዩክሬን ጦርነት ጋር በተያያዘ ከምዕራባውያን አገራት ጎን ተሰልፈው ለሚገኙት ፖላንድ እና ቡልጋሪያ ትልክ የነበረውን የጋዝ አቅርቦት አቋረጠች።

የሩሲያ ኢነርጂ ተቋም ጋዝፕሮም ሁለቱ አገራት ለሚቀርብላቸው ጋዝ በሩብል ክፍያ ለመክፈል ፍቃደኛ ስላልሆኑ የጋዝ አቅርቦቱ ተቋርጧል ብሏል። ቀደም ሲል የፖላንድና ቡልጋሪያ ጋዝ አከፋፋዮች ሩሲያ ጋዝ መላክ እንደምታቆም አስታውቃለች ብለው ነበር።

ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን «ወዳጅ» ያልሆኑ አገራት ለሚቀበሉት የሩሲያ ጋዝ በሩብል ክፍያ ይፈጽሙ ማለታቸው ይታወሳል። ይሁን እንጂ ፖላንድ እና ቡልጋሪያን ጨምሮ አውሮፓውያን አገራት ይህን እንደማይቀበሉ ከዚህ ቀደም ገልጸው እንደነበር ቢቢሲ ዘግቧል።

ሩሲያ ለምትልከው የጋዝ ምርት ክፍያው በመገበያያ ገንዘቧ እንዲከፈላት የምትፈልገው በምዕራባውያን ማዕቀብ የተዳከመውን ሩብል መገበያያ ገንዘቧን አቅም ለመጨመር ነው።

የሩሲያን ውሳኔ ተከትሎ ቡልጋሪያ ጋዝ የፖለቲካ መሣሪያ እየሆነ ነው በማለት የሞስኮን ውሳኔ ተቃውማለች።

ቡልጋሪያ የዚህን ወር የጋዝ ክፍያዋን ሙሉ በሙሉ መፈጸሟን በመግለጽ ጋዝፕሮም ኩባንያ ውሉን አልጠበቀም በማለት ከሳለች።

«በዚህ ጦርነት የተፈጥሮ ጋዝ የፖለቲካ እና ኢኮኖሚ መሣሪያ ሆኖ ጥቅም ላይ እየዋለ ነው» ሲሉ የቡልጋሪያ ኢነርጂ ሚኒስትር አሌክሳንደር ኒኮሎቭ ተናግረዋል።

ሚኒስትሩ የአውሮፓ ኅብረትን ምክረ ሐሳብ በመቀበል አገራቸው ከሩሲያ ለምትቀበለው ጋዝ በሩብል እንደማትከፍል አረጋግጠዋል። ፖላንድ በበኩሏ ያለ ሩሲያ ጋዝ ሕይወት ለማስቀጠል እሞክራለሁ ብላለች።

የፖላንድ ኃይል አቅራቢ ድርጅት ፒጂኤንአይጂ ወደ አገሪቱ ይገባ የነበረው የጋዝ አቅርቦት መቋረጡን አረጋግጧል። ኃይል አቅራቢ ድርጅቱ ከሚያከፋፍለው ጋዝ ግሚሱን ከሩሲያ ጋዝፕሮም ሲያገኝ የቆየ ቢሆንም ከሌሎች ምንጮች ጋዝ ለማግኘት እጥራለሁ ብሏል።

የፖላንድ ኃይል አቅራቢ ድርጅት 80 በመቶ የጋዝ ክምችት እንዳላቸው ገልጾ፣ ሞቃታማ ወራት እየተቃረቡ እንደመሆኑ የሰዎች የጋዝ ፍላጎት ይቀንሳል በማለት የሩሲያ ጋዝ አቅርቦት መቋረጥ ለአገሪቱ ከፍተኛ ስጋት እንደማይሆን ገልጿል፡፡

# ስፖርት





# ምርጥ አትሌቶችን የሚያፎካክረው ዳይመንድ ሊግ ሊጀመር ነው

ብርሃን ፈይሳ

ከዓመታዊው የአትሌቲክስ ውድድሮች መካከል አንዱ የሆነውና በአትሌቶች ዘንድ ትልቅ ግምት የሚሰጠው ዳይመንድ ሊግ ከሁለት ሳምንታት በኋላ ይጀመራል። በአውሮፓ፣ እስያ እና አፍሪካ ባሉ 14 የዓለም ከተሞች እየተዘዋወረ የሚደረገውና ከመላው ዓለም የተሰባሰቡ ዝነኛ አትሌቶችን የሚያሳትፈው ውድድሩ በኳታሯ ዶሃ ነው የሚጀመረው። አምስት ወራትን በሚሸፍነው በዚህ ውድድር ላይ ለ13 ጊዜያት በማሸነፍ ከፍተኛውን ነጥብ መሰብሰብ የቻለ አትሌት በዙሪኩ የመጨረሻው ውድድር የዳይመንድ አሸናፊ ይሆናል።

በቀናት ልዩነት በተለያዩ ከተሞች የሚደረገው የአንድ ቀን ውድድር ከኳታር ወደ በርሚንግሃም ተሻግሮ የሚደረግ ሲሆን፤ ሦስተኛው ደግሞ በአሜሪካዋ ዩጂን ይካሄዳል። አገሪቷ (አሜሪካ) ከአንድ ወር በኋላ በስፖርቱ ቁጥር አንድ የሆነውን የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና የምታዘጋጅ መሆኗ ይታወቃል። በመሆኑም በዳይመንድ ሊጉ ተካፋይ የሆኑ አትሌቶች እንዲሁም ስፖርቱን በበላይነት የሚመራው የዓለም አትሌቲክስ የአሜሪካንን ዝግጅት ለመመልከትና ለመፈተሽ የሚችልበትን ሁኔታ እንደሚያመቻችም ከወዲሁ ይጠበቃል።

ከዚያ በኋላም ምርጦቹ አትሌቶች በራባት፣ ሮም፣ ኦስሎ፣ ፓሪስ እና ስቶክሆልም ከተሞች በወጣላቸው መርሃ ግብር መሠረት ውድድራቸውን የሚቀጥሉ ይሆናል። ነገር ግን አገራት ምርጥ አትሌቶቻቸውን የሚያፋልሙበትና ለረጅም ጊዜ በዝግጅት ላይ የቆዩ አትሌቶች የዓለም ቁጥር አንድ አትሌትነት ክብርን ለመቀዳጀት ጥረት የሚያደርጉበት የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና የሚካሄድ በመሆኑ ዳመንድ ሊጉ ለአንድ ወር ያህል ተቋርጦ ይቆያል።

ከቻምፒዮናው መጠናቀቅ ስድስት ቀናት በኋላም ዳይመንድ ሊጉ ወደ እስያ አህጉር በማምራት ወደ ውድድር ይመለሳል። ሻንጋይ እአአ ከ2019 ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አዘጋጅነቷ በመመለስ ውድድሩን የምታስተናግድ መሆኑን የዓለም አትሌቲክስ በዘገባው አስነብቧል። ከስድስት ቀናት በኋላም ወደ አገሪቷ ሌላኛዋ ከተማ አስተናጋጅነቱን በማሸጋገር በአዲሲቷ የዳይመንድ ሊግ ውድድር አዘጋጅ ሺንዚን ይደረጋል። ውድድሩ በድጋሚ ወደ አውሮፓ ተመልሶም በሞናኮ፣ ሉዛን እና ብራሰልስ ቆይታውን በማድረግም በስዊዘርላንድ ዙሪክ መደምደሚያውን ያደርጋል።

በዚህ ውድድር ላይም ባለፈው ዓመት በተካሄደው የቶኪዮ ኦሊምፒክ ቻምፒዮን የሆኑ እንዲሁም በዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮናው ምርጥ ብቃታቸውን ያሳዩ አትሌቶች ተሳታፊ እንደሚሆኑበት ይጠበቃል። በተለይም ይህ ዓመት የዓለም ቻምፒዮና የሚካሄድበት እንደመሆኑ አትሌቶች አገራቸውን በመድረኩ ለመወከል እንዲያስችላቸው ያሉበትን አቋም በዳይመንድ ሊጉ ለማሳየት ይረዳቸዋል። ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ የዓለም ከዋክብት አትሌቶች በዳይመንድ ሊጉ እንደሚካፈሉ ማረጋገጣቸውን አዘጋጆቹ አመላክተዋል።

የዓለም አትሌቲክስ የዘንድሮው ዳይመንድ ሊግ አሸናፊ ይሆናሉ በሚል ተጠባቂ ካላቸው አትሌቶች መካከል ኢትዮጵያውያኑ ወጣት አትሌቶች ለተሰንበት ግደይ እና ሳሙኤል ተፈራ ተካተዋል። የኦሊምፒክ ነሐስ እና የዓለም ቻምፒዮና የብር ሜዳሊያ ባለቤቷ አትሌት ለተሰንበት፤ በምትታወቅበት የ5ሺ እና 10ሺ ሜትር እንዲሁም በግማሽ ማራቶን ርቀቶች የክብረወሰን ባለቤት መሆኗ ይታወቃል። ይሁንና በእነዚህ ርቀቶች ውድድር የማይካሄድ መሆኑን ተከትሎ የመም ውድድር በሆነው የአንድ ሰዓት ውድድር ተሳታፊ እንደምትሆን የውድድሩ አዘጋጆች አረጋግጠዋል።

የ1ሺ500 ሜትር ርቀት አትሌት የሆነው ሳሙኤል ተፈራ በዳይመንድ ሊጉ ስኬታማ ይሆናሉ በሚል ከፍተኛውን ቅድመ ግምት ካገኙት አትሌቶች መካከል አንዱ ሆኗል። አትሌቱ እአአ በ2018ቱ የበርሚንግሃም የዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና አሸናፊ በመሆን ወደ ምርጥ አትሌቶች ምድብ የተቀላቀለ ሲሆን፤ በቀጣዩ ዓመትም በርቀቱ የዓለም ክብረወሰን በማስመዝገብ ተስፋ የተጣለበት ወጣት መሆኑን ማስመስከሩ ይታወሳል።

በዚያው ዓመት በዶሃ የዓለም ቻምፒዮና አገሩን ቢወክልም በገጠመው ጉዳት ምክንያት ውድድሩን ለማቋረጥ ተገዷል። በቶኪዮው ኦሊምፒክም በተመሳሳይ ጉዳት የደረሰበት በመሆኑ እንደተጠበቀው ውጤታማ አልነበረም። በቅርቡ በቤልግሬድ በተካሄደው የቤት ውስጥ ቻምፒዮና ግን አትሌቱ ወደ ቀደመ አቋሙ መመለሱን በሚያረጋግጥ ሁኔታ የወርቅ ሜዳሊያውን ማጥለቅ ችሏል።

አትሌቱ በዚህ ምክንያት የዳይመንድ ሊግ አሸናፊነት ግምቱን ያገኘ ሲሆን፤ ከሌላኛው ስኮትላንዳዊ አትሌት ግን ጠንካራ ፉክክር ሊገጥመው እንደሚችል ነው የሚጠበቀው። ጆሽ ኬር የተሰኘው ይህ አትሌት በቶኪዮ ኦሊምፒክ የነሐስ ሜዳሊያ ባለቤት ነበር።




## የጨረታ ማስታወቂያ
## የጨረታ ቁጥር KMC/OT/003/2014 ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቂርቆስ ማኑፋክቸሪንግ ኮሌጅ በ2014 በጀት ዓመት የሚያስፈልገውን ቋሚ ዕቃዎች ማለትም ኮምፒውተር፣የአዳራሽ ወንበሮች ፣የካፌ እቃዎችና ጠረጴዛ ለመግዛት ይፈልጋል:: ስለሆነም በጨረታው መሳተፍ የሚፈልጉ የሀገር ውስጥ ህጋዊ ብቃት ያላቸው ተጫራቾች ከዚህ በታች የተመለከቱትን መመሪያዎች ማሟላት ይኖርባቸዋል::

**የጨረታው መስፈርት :-**

1. የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳር ኤጀንሲ ባዘጋጀው የዕቃና አገልግሎት አቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተካተቱ መሆን አለባቸው::
2. በዘርፉ የታደሰ ህጋዊ ንግድ ስራ ፈቃድ፣የምዝገባ የምስክር ወረቀት ፣የቫት/የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆኑ ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /ቲን/ ተመዝጋቢ የሆኑ አግባብነት ያለው የአቅራቢዎች የምዝገባ ምስክር ወረቀት ያለው::
3. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ 200/ሁለት መቶ ብር/ በመክፈል ከግዥ ክፍል ሰነድ መውሰድ ይችላሉ::
4. ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዳቸውን ይህ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ በፖስታ በማሸግ መወዳደር ይችላሉ::
5. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ 50,000.00/ሀምሳ ሺህ ብር) በባንክ የተረጋገጠ C.P.O ወይም በባንክ ዋስትና ለጨረታ ማስከበሪያ ማስያዝ ይኖርባቸዋል::
6. ተጫራቾች የሚያቀርቡት የጨረታ ሰነድ ፋይናሻል እና ቴክኒካል ሲሆን ለእያንዳንዱ አንድ አንድ ኮፒ በማድረግ ለየብቻ በማሸግ እያንዳንዱ ገጽ ላይ የድርጅቱ ማህተም ተደርጎ የጨረታ መመሪያው በሚያዘው መሰረት ቂርቆስ ማኑፋክቸሪንግ ኮሌጅ ፋይናንስ ቢሮ ቁ.05 በሚገኘው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ጋዜጣ ላይ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠር እስከ 11ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ማስገባት የሚኖርባችሁ ሲሆን ስርዝ ድልዝ እና ፍሉድ ተቀባይነት የለውም :
7. ጨረታው ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት 11ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ታሽጎ 4:30 በቂርቆስ ማኑፋክቸሪንግ ኮሌጅ ቅጥር ግቢ መሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው እና ታዛቢዎች በተገኙበት ጨረታው የሚከፈት ይሆናል ፡ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በመክፈቻው ቀን ባይገኙም የጨረታው መከፈት ስነ-ስርዓት አይስተጓጎልም::
8. ኮሌጁ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው :
9. ተጫራቾች ለሚያቀርቧቸው እቃዎች ናሙና ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው ::
10. ለጥቃቅንና አነስተኛ ተጫራቾች አምራች ድርጅት ካልሆናችሁ ከላይ የተዘረዘሩትን የጨረታ ማስከበሪያ ሲ.ፒ.ኦ ማስያዝ ይኖርባቸዋል :: የዋስትና ደብዳቤ ተቀባይነት አይኖረውም::

**ስበለጠ መረጃ-**

**አድራሻ፡-** ከቂርቆስ ቤተክርስቲያን ወደ ቄራ በሚወስደው አዲስ መንገድ ከቴሌ 200 ሜትር ወረድ ብሎ አርባ ምንጭ አሳ ቤት ፊትለፊት ነው::

ስልክ ቁጥር፡-011-4-70-57-22 ወይም 011-4-70-66-43

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቂርቆስ ማኑፋክቸሪንግ ኮሌጅ**



## የሂሳብ ኦዲት ጨረታ ማስታወቂያ

የጎተራ ሳይት ኮንዶሚኒየም ኃላ/የተ/የህ/ስራ/ማህበር የማህበሩን የ2011 እስከ 2014 ስድስተኛው ወር ድረስ ያለውን የማህበሩን የሂሳብ ኦዲት ባለሙያዎችን አወዳድሮ ለማሰራት ይፈልጋል፡፡

**ስለሆነም፡-**

1. የ2014 የታደሰ የሂሳብ ኦዲት ስራ የንግድ ፈቃድ ያለው
2. የተመሰከረለት የሂሳብ ኦዲት አዋቂነት ሰርተፍኬት ያለው
3. ከሶስት የሂሳብ አሰሪ ያላነሰ የሂሳብ ኦዲት መስራቱን ማረጋገጫ የስራ ልምድ የሚያብ
4. የተጨማሪ እሴት ታክስ የተመገበ
5. የዓመቱን ግብር መክፈሉን የሚያሳይ ክሊራንስ ማቅረብ የሚችል
6. ስራውን በአጠረ ጊዜ ው ጠናቶ ማቅረብ የሚችል ከላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ የሂሳብ ኦዲት አዋቂዎች ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሰባት ተከታታይ ቀናት ቅዳሜ እስከ 6:00 ጨምሮ ባለው ጊዜ ውስጥ በማህበሩ ጽ/ቤት በግንባር በመቅረብ ለጨረታ ማቅረቢያ የተዘጋጀውን ሰነድ ብር 100(አንድ መቶ ብር) በመክፈል መጫረትና ማቅረብ የምትችሉ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**ማሳሰቢያ**፡- የጨረታ ሰነዶቹ የሚከፈቱት በስምንተኛው የስራ ቀን በማህበሩ ጽ/ቤት 4፡00 ሰዓት ይሆናል፡ ጨረታው በሚከፈትበት ጊዜ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎች ባሉበት ይሆናል፡፡

የጨረታ ሰነዱ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ መቅረብ አለበት፡፡

**አድራሻ**:- አጎና ሲኒማ ጀርባ ጎተራ ኮንዶሚኒየም ግቢ ውስጥ

ስልክ ⇒ 0114 70 22 54 /0114 70 12 47

**የጎተራ ሳይት ኮንደሚኒየም ኃላ/የተ/የህ/ስራ/ማህበር**